# ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ።

(ክለሳ.1.20020507)

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ።

ምዕራፍ ፡ 1 ፤

1 ፤ በብንያም ፡ አገር ፡ በዐናቶት ፡ ከነበሩ ፡ ካህናት ፡ የኾነ ፡ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡ የኤርምያስ ፡ ቃል ።

2 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ በኢዮስያስ ፡ ዘመን ፡ በመንግሥቱ ፡ በዐሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መጣለት ።

3 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ ዘመን ፥ እስከይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ እስከኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ እስከ ፡ ሴዴቅያስ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ፍጻሜ ፥ ኢየሩሳሌም ፡ እስከተማረከችበት ፡ እስከ ፡ ዐምስተኛው ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ መጣ ።

4 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

5 ፤ በሆድ ፡ ሳልሠራኽ ፡ ዐውቄኻለኹ ፥ ከማሕፀንም ፡ ሳትወጣ ፡ ቀድሼኻለኹ ፥ ለአሕዛብም ፡ ነቢይ ፡ አድርጌኻለኹ ።

6 ፤ እኔም ፦ ወዮ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ እንሆ ፥ ብላቴና ፡ ነኝና ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ አላውቅም ፡ አልኹ ።

7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ወደምሰድኽ ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ትኼዳለኽና ፥ የማዝኽንም ፡ ኹሉ ፡ ትናገራለኽና ፦ ብላቴና ፡ ነኝ ፡ አትበል ።

8 ፤ እኔ ፡ አድንኽ ፡ ዘንድ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ ከፊታቸው ፡ አትፍራ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ አፌን ፡ ዳሰሰ ፥ እግዚአብሔርም ፦ እንሆ ፥ ቃሌን ፡ በአፍኽ ፡ ውስጥ ፡ አኑሬያለኹ ፤

10 ፤ እንሆ ፦ ትነቅልና ፡ ታፈርስ ፡ ዘንድ ፥ ታጠፋና ፡ ትገለብጥ ፡ ዘንድ ፥ ትሠራና ፡ ትተክል ፡ ዘንድ ፡ በአሕዛብና ፡ በመንግሥታት ፡ ላይ ፡ ዛሬ ፡ አድርጌኻለኹ ፡ አለኝ ።

11 ፤ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፦ ኤርምያስ ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ ታያለኽ ፥ እያለ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣ ። እኔም ፦ የለውዝ ፡ በትር ፡ አያለኹ ፡ አልኹ ።

12 ፤ እግዚአብሔርም ፦ እፈጽመው ፡ ዘንድ ፡ በቃሌ ፡ እተጋለኹና ፡ መልካም ፡ አይተኻል ፡ አለኝ ።

13 ፤ ኹለተኛም ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፦ ምን ፡ ታያለኽ ፥ እያለ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣ ። እኔም ፦ የሚፈላ ፡ አፍላል ፡ አያለኹ ፥ ፊቱም ፡ ከሰሜን ፡ ወገን ፡ ነው ፡ አልኹ ።

14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ከሰሜን ፡ ወገን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በምድሪቱ ፡ በተቀመጡ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይገለጣል ።

15 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ በሰሜን ፡ ያሉትን ፡ የመንግሥታትን ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ እጠራለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እነርሱም ፡ ይመጣሉ ፡ እያንዳንዳቸውም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ በዙሪያዋ ፡ በቅጥሯ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ዙፋናቸውን ፡ ያስቀምጣሉ ።

16 ፤ ስለ ፡ ክፋታቸውም ፡ ኹሉ ፡ እኔን ፡ ስለ ፡ ተዉ ፥ ለሌላዎችም ፡ አማልክት ፡ ስላጠኑ ፥ ለእጃቸውም ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ሰገዱ ፥ ፍርዴን ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እናገራለኹ ።

17 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ወገብኽን ፡ ታጠቅ ፥ ተነሥም ፥ ያዘዝኹኽም ፡ ኹሉ ፡ ንገራቸው ፤ በፊታቸው ፡ እንዳላስፈራኽ ፡ አትፍራቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

18 ፤ እንሆ ፥ በምድሪቱ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ በአለቃዎቿና ፡ በካህናቷ ፡ ላይ ፡ በምድሪቱም ፡ ሕዝብ ፡
ላይ ፡ እንደ ፡ ተመሸገ ፡ ከተማ ፡ እንደ ፡ ብረትም ፡ ዐምድ ፡ እንደ ፡ ናስም ፡ ቅጥር ፡ ዛሬ ፡ አድርጌኻለኹ ።

19 ፤ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይዋጋሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አድንኽ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ ድል ፡ አይነሡኽም ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ።

## ___________________ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። ___________________

ምዕራፍ ፡ 2 ፤

1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

2 ፤ ኺድ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ዦሮ ፡ ጩኽ ፥ እንዲህም ፡ በል ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የብላቴንነትሽን ፡
ምሕረት ፡ የታጨሽበትንም ፡ ፍቅር ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ ዘር ፡ ባልተዘራበት ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ተከተልሽኝ ፡ ዐስቤያለኹ ።

3 ፤ እስራኤል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ነበረ ፥ የቡቃያውም ፡ በኵራት ፡ ነበረ ፤ የበሉት ፡ እንደ ፡ በደለኛዎች ፡
ይቈጠራሉ ፥ ክፉም ፡ ነገር ፡ ያገኛቸዋል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

4 ፤ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

5 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አባቶቻችኹ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ የራቁ ፥ ከንቱነትንም ፡ የተከተሉ ፥ ከንቱም ፡ የኾኑ ፡
ምን ፡ ክፋት ፡ አግኝተውብኝ ፡ ነው ፧

6 ፤ እነርሱም ፦ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣን ፥ በምድረ ፡ በዳም ፡ በባድማ ፡ ጕድጓድም ፡ ባለበት ፡ ምድር ፥ በውሃ ፡
ጥምና ፡ በሞት ፡ ጥላ ፡ ምድር ፥ ማንም ፡ በማያልፍበትና ፡ ማንም ፡ በማይቀመጥበት ፡ ምድር ፡ የመራን ፡ እግዚአብሔር ፡
ወዴት ፡ አለ ፧ አላሉም ።

7 ፤ ፍሬዋንና ፡ በረከቷንም ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ፍሬያማ ፡ ምድር ፡ አገባኋችኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በገባችኹ ፡ ጊዜ ፡
ምድሬን ፡ አረከሳችኹ ፥ ርስቴንም ፡ አጐሳቈላችኹ ።

8 ፤ ካህናቱም ፦ እግዚአብሔር ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ አላሉም ፥ ባለአሪቶቹም ፡ አላወቁኝም ፤ ገዢዎችም ፡
ዐመፁብኝ ፥ ነቢያትም ፡ በበዓል ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ፥ የማይረባንም ፡ ነገር ፡ ተከተሉ ።

9 ፤ ስለዚህ ፥ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እከራከራለኹ ፥ ከልጆቻችኹም ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ እከራከራለኹ ።

10 ፤ ወደኪቲም ፡ ደሴቶች ፡ ዕለፉና ፡ ተመልከቱ ፥ ወደ ፡ ቄዳርም ፡ ላኩና ፡ እጅግ ፡ መርምሩ ፥ እንደዚህም ፡ ያለ ፡ ነገር ፡
ኾኖ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እዩ ።

11 ፤ በእውኑ ፡ አማልክት ፡ ያልኾኑትን ፡ አማልክቱን ፡ የለወጣቸው ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ አለን ፧ ነገር ፡ ግን ፡ ሕዝቤ ፡
ክብሩን ፡ ለማይረባ ፡ ነገር ፡ ለወጠ ።

12 ፤ ሰማያት ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ተደነቁ ፥ እጅግም ፡ ደንግጡና ፡ ተንቀጥቀጡ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

13 ፤ ሕዝቤ ፡ ኹለቱን ፡ ክፉ ፡ ነገሮች ፡ አድርገዋልና ፤ እኔን ፡ የሕያውን ፡ ውሃ ፡ምንጭ ፡ ትተውኛል ፥ የተቀደዱትንም ፡
ጕድጓዶች ፥ ውሃውን ፡ ይይዙ ፡ ዘንድ ፡ የማይችሉትን ፡ ጕድጓዶች ፥ ለራሳቸው ፡ ቈፍረዋል ።

14 ፤ በእውኑ ፡ እስራኤል ፡ ባሪያ ፡ ነውን ፧ ወይስ ፡ የቤት ፡ ውላጅ ፡ ነውን ፧ ስለ ፡ ምን ፡ ብዝበዛ ፡ ኾነ ፧

15 ፤ የአንበሳ ፡ ደቦሎች ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አገሡ ፥ ድምፃቸውንም ፡ ሰጡ ፤ ምድሩንም ፡ ባድማ ፡ አደረጉ ፥ ከተማዎቹም ፡
ተቃጠሉ ፡ የሚቀመጥባቸውም ፡ የለም ።

16 ፤ የሜምፎስና ፡ የጣፍናስ ፡ ልጆች ፡ አስነወሩሽ ፡ አላገጡብሽም ።

17 ፤ ይህ ፡ ኹሉ ፡ የኾነብሽ ፡ እኔን ፡ ስለ ፡ ተውሽ ፡ አይደለምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክሽ ።

18 ፤ አኹንስ ፡ የሺሖርን ፡ ውሃ ፡ ትጠጪ ፡ ዘንድ ፡ በግብጽ ፡ መንገድ ፡ ምን ፡ ጕዳይ ፡ አለሽ ፧ የኤፍራጥስንም ፡ ውሃ ፡
ትጠጪ ፡ ዘንድ ፡ በአሶር ፡ መንገድ ፡ ምን ፡ ጕዳይ ፡ አለሽ ፧

19 ፤ ክፋትሽ ፡ ይገሥጽሻል ፡ ክዳትሽም ፡ ይዘልፍሻል ፤ አምላክሽንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ የተውሽ ፡ እኔንም ፡ መፍራት ፡



www.ethiopianorthodox.org

የሌለብሽ ፡ ክፉና ፡ መራራ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዕወቂ ፥ ተመልከቺ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

20 ፤ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ቀንበርሽን ፡ ሰብሬያለኹ ፡ እስራትሽንም ፡ ቈርጫለኹ ፤ አንቺም ፦ አላገለግልም ፡ አልሽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከፍ ፡ ባለው ፡ ኰረብታ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከለምለምም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ለማመንዘር ፡ ተጋደምሽ ።

21 ፤ እኔ ፡ የተመረጠች ፡ ወይን ፡ ፍጹምም ፡ እውነተኛ ፡ ዘር ፡ አድርጌ ፡ ተክዬሽ ፡ ነበር ፤ አንቺ ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ የእንግዳ ፡ ወይን ፡ ግንድ ፡ ኾነሽ ፡ እንዴት ፡ ተለወጥሽብኝ ፧

22 ፤ በእንዶድ ፡ ብትታጠቢም ፥ ለራስሽም ፡ ሳሙና ፡ ብታበዢ ፥ በእኔ ፡ ፊት ፡ በኀጢአትሽ ፡ ረክሰሻል ፡ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

23 ፤ አንቺስ ፦ አልረከስኹም ፥ በዓሊምንም ፡ አልተከተልኹም ፡ እንዴት ፡ ትያለሽ ፧ በቈላ ፡ ያለውን ፡ መንገድሽን ፡ ተመልከቺ ፥ ያደረግሽውንም ፡ ዕወቂ ፤ በመንገድም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተለቀቀች ፡ እንደ ፡ ፈጣን ፡ ግመል ፡ ኾነሻል ፤

24 ፤ በምኞቷ ፡ ነፋስን ፡ እንደምታሸት ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንደ ፡ ለመደች ፡ እንደ ፡ ሜዳ ፡ አህያ ፡ ነሽ ፤ ከምኞቷ ፡ የሚመልሳት ፡ ማን ፡ ነው ፧ የሚሿት ፡ ኹሉ ፡ አይደክሙም ፥ በወራቷ ፡ ያገኟታል ።

25 ፤ እግርሽን ፡ ከሻካራ ፡ መንገድ ፡ ጕረሮሽንም ፡ ከውሃ ፡ ጥም ፡ ከልክዪ ፤ አንቺ ፡ ግን ፦ እጨክናለኹ ፥ እንግዶዎችን ፡ ወድጃለኹና ፥ እከተላቸዋለኹም ፡ አልሽ ።

26 ፤ ሌባ ፡ በተያዘ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚያፍር ፡ እንዲሁ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፥ እነርሱና ፡ ንጉሦቻቸውም ፡ አለቃዎቻቸውም ፡ ካህናታቸውም ፡ ነቢያታቸውም ፡ ያፍራሉ ።

27 ፤ ግንዱን ፦ አንተ ፡ አባቴ ፡ ነኽ ፤ ድንጋዩንም ፦ አንተ ፡ ወለድኸኝ ፡ ይላሉ ፤ ፊታቸውንም ፡ ሳይኾን ፡ ዠርባቸውን ፡ ሰጡኝ ፥ በመከራቸው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፦ ተነሥተኽ ፡ አድነን ፡ ይላሉ ።

28 ፤ ለአንተ ፡ የሠራኻቸው ፡ አማልክትኽ ፡ ወዴት ፡ ናቸው ፧ ይሁዳ ፡ ሆይ ፥ አማልክትኽ ፡ እንደ ፡ ከተማዎችኽ ፡ ቍጥር ፡ እንዲሁ ፡ ናቸውና ፥ ይነሡ ፡ በመከራኽም ፡ ጊዜ ፡ ያድኑኽ ።

29 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የምትከራከሩ ፡ ለምንድር ፡ ነው ፧ ኹላችኹ ፡ ዐምፃችኹብኛል ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

30 ፤ ልጆቻችኹን ፡ በከንቱ ፡ ቀሥፌአቸዋለኹ ፤ ተግሣጽን ፡ አልተቀበሉም ፤ ሰይፋችኹ ፡ እንደሚሰብር ፡ አንበሳ ፡ ነቢያታችኹን ፡ በልቷል ።

31 ፤ ትውልድ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ተመልከቱ ፦ በእውኑ ፡ ለእስራኤል ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወይስ ፡ የጨለመች ፡ ምድር ፡ ኾንኹባትን ፧ ሕዝቤስ ፡ ስለ ፡ ምን ፦ እኛ ፡ ፈርጥጠናል ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ወዳንተ ፡ አንመለስም ፡ ይላል ፧

32 ፤ በእውኑ ፡ ቈንጆ ፡ ጌጧን ፡ ወይስ ፡ ሙሽራ ፡ ዝርግፍ ፡ ጌጧን ፡ ትረሳለችን ፧ ሕዝቤ ፡ ግን ፡ የማይቈጠር ፡ ወራት ፡ ረስቶኛል ።

33 ፤ ፍቅርን ፡ ለመሻት ፡ መንገድሽን ፡ እንዴት ፡ ታቀኚለሽ! ስለዚህ ፡ ለክፉዎች ፡ ሴቶች ፡ እንኳ ፡ መንገድሽን ፡ አስተምረሻል ።

34 ፤ በእጆችሽም ፡ የንጹሓን ፡ ድኻዎች ፡ ደም ፡ ተገኝቷል ፤ በእነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በግልጥ ፡ አገኘኹት ፡ እንጂ ፡ በስውር ፡ ፈልጌ ፡ አላገኘኹትም ።

35 ፤ አንቺ ፡ ግን ፦ ንጹሕ ፡ ነኝ ፤ በእውነት ፡ ቍጣው ፡ ከእኔ ፡ ተመልሷል ፡ አልሽ ። እንሆ ፦ ኀጢአት ፡ አልሠራኹም ፡ ብለሻልና ፥ በፍርድ ፡ እከስሻለኹ ።

36 ፤ መንገድሽን ፡ ትለውጪ ፡ ዘንድ ፡ ለምን ፡ እጅግ ፡ ትሮጫለሽ ፧ አሶር ፡ እንዳሳፈረሽ ፡ ግብጽ ፡ ያሳፍርሻል ።

37 ፤ እግዚአብሔር ፡ የታመንሽባቸውን ፡ ጥሏልና ፥ በእነርሱም ፡ አይከናወንልሽምና ፡ እጅሽን ፡ በራስሽ ፡ ላይ ፡ አድርገሽ ፡ ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ትወጫለሽ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ 3 ፤

1 ፤ በሰው ፡ ዘንድ ፦ ሰው ፡ ሚስቱን ፡ ቢፈታ ፥ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ ኼዳ ፡ ሌላ ፡ ወንድ ፡ ብታገባ ፥ በእውኑ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡
ርሱ ፡ ትመለሳለችን ፧ ያች ፡ ሴት ፡ እጅግ ፡ የረከሰች ፡ አይደለችምን ፧ ይባላል ። አንቺ ፡ ከብዙ ፡ ውሽማዎች ፡ ጋራ ፡
አመንዝረሻል ፥ ወደ ፡ እኔም ፡ ትመለሻለሽን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

2 ፤ ዐይንሽን ፡ አንሥተሽ ፡ ወደ ፡ ወናዎች ፡ ኰረብታዎች ፡ ተመልከቺ ፤ ያልተጋደምሽበት ፡ ስፍራ ፡ ወዴት ፡
አለ ፧ ዐረባዊ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንደሚቀመጥ ፡ አንቺ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠሽ ፡ ትጠብቂያቸው ፡
ነበር ፤ በግልሙትናሽና ፡ በኀጢአትሽ ፡ ምድሪቱን ፡ አረከሽ ።

3 ፤ ስለዚህ ፥ ካፊያ ፡ ተከለከለ ፥ የኋለኛውም ፡ ዝናብ ፡ ጠፋ ፤ የጋለሞታም ፡ ሴት ፡ ፊት ፡ ነበረብሽ ፥ ታፍሪም ፡ ዘንድ ፡
እንቢ ፡ ብለሻል ።

4 ፤ አኹንም ፦ አንተ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፥ የብላቴንነቴ ፡ ወዳጅ ፡ ነኽ ፡ ብለሽ ፡ አልጮኽሺልኝምን ፧ ለዘለዓለም ፡
ይቈጣልን ፧

5 ፤ እስከ ፡ ፍጻሜስ ፡ ድረስ ፡ ይጠብቀዋልን ፧ እንሆ ፥ እንዲህ ፡ ብለሽ ፡ ተናገርሽ ፥ እንደ ፡ ተቻለሽም ፡ መጠን ፡ ክፉን ፡
ነገር ፡ አደረግሽ ።

6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በንጉሡ ፡ በኢዮስያስ ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ከዳተኛዪቱ ፡ እስራኤል ፡ ያደረገችውን ፡
አየኽን ፧ ወደረዘመው ፡ ተራራ ፡ ኹሉ ፡ ከለመለመ ፡ ዛፍም ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ኼደች ፡ በዚያም ፡ ጋለሞተች ።

7 ፤ ይህንም ፡ ኹሉ ፡ ካደረገች ፡ በኋላ ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ትመለሳለች ፡ ብዬ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡
ግን ፥ አልተመለሰችም ፤ አታላይ ፡ እኅቷም ፡ ይሁዳ ፡ አየች ።

8 ፤ ከዳተኛዪቱም ፡ እስራኤል ፡ ስላመነዘረች ፡ ስለዚህ ፡ ፈትቻታለኹ ፡ የፍቺንም ፡ ወረቀት ፡ ሰጥቻታለኹ ፤ አታላይ ፡
እኅቷ ፡ ይሁዳ ፡ ግን ፡ እንዳልፈራች ፡ ርሷም ፡ ደግሞ ፡ ኼዳ ፡ እንደ ፡ ጋለሞተች ፡ አየኹ ።

9 ፤ በግልሙትናዋም ፡ በመቅለሏም ፡ ምድሪቱ ፡ ረከሰች ፤ ርሷም ፡ ከድንጋይና ፡ ከግንድ ፡ ጋራ ፡ አመነዘረች ።

10 ፤ በዚህም ፡ ኹሉ ፡ አታላዪቱ ፡ ይሁዳ ፡ በሐሰት ፡ እንጂ ፡ በፍጹም ፡ ልቧ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አልተመለሰችም ።

11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ከአታላዪቱ ፡ ከይሁዳ ፡ ይልቅ ፡ ከዳተኛዪቱ ፡ እስራኤል ፡ ጸደቀች ።

12 ፤ ኺድና ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ተናገር ፥ እንዲህም ፡ በል ፦ ከዳተኛዪቱ ፡ እስራኤል ፡
ሆይ ፥ ተመለሺ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ መሓሪ ፡ ነኝና ፥ ለዘለዓለምም ፡ አልቈጣምና ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ፊቴን ፡
አላደርግም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

13 ፤ በአምላክሽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ እንዳመፅሽ ፥ መንገድሽንም ፡ ከለመለመ ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ለእንግዳዎች ፡
እንደ ፡ ዘረጋሽ ፥ ቃሌንም ፡ እንዳልሰማሽ ፡ ኀጢአትሽን ፡ ብቻ ፡ ዕወቂ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

14 ፤ ከዳተኛዎች ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ባላችኹ ፡ ነኝና ፡ ተመለሱ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ አንዱንም ፡ ከአንዲት ፡
ከተማ ፡ ኹለቱንም ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ እወስዳችኋለኹ ፥ ወደ ፡ ጽዮንም ፡ አመጣችኋለኹ ፤

15 ፤ እንደ ፡ ልቤም ፡ በግ ፡ ጠባቂዎችን ፡ እሰጣችኋለኹ ፥ በዕውቀትና ፡ በማስተዋልም ፡ ይጠብቋችኋል ።

16 ፤ በበዛችኹም ፡ ጊዜ ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ በረባችኹ ፡ ጊዜ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ በዚያ ፡
ዘመን ፦ የእግዚአብሔር ፡ የቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ታቦት ፡ ብለው ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይጠሩም ፤ ልብ ፡
አያደርጉትም ፥ አያስቡትምም ፥ አይሹትምም ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ አይደረግም ።

17 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዙፋን ፡ ብለው ፡ ይጠሯታል ፥ አሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡
ይሰበሰባሉ ፤ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ክፉውን ፡ እልከኛ ፡ ልባቸውን ፡ ተከትለው ፡ አይኼዱም ።

18 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ ወደእስራኤል ፡ ቤት ፡ ይኼዳል ፤ በአንድም ፡ ኾነው ፡ ከሰሜን ፡ ምድር ፡ ርስት ፡
አድርጌ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ወደሰጠኹት ፡ ምድር ፡ ይመጣሉ ።

19 ፤ እኔ ፡ ግን ፦ ከወንዶች ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ እንዴት ፡ አደርግሻለኹ ፧ ያማረችውንስ ፡ ምድር ፡ የከበረችውን ፡

http://www.gzamargna.net

www.ethiopianorthodox.org

የአሕዛብን ፡ ሰራዊት ፡ ርስት ፡ እንዴት ፡ እሰጥሻለኹ ፡ ብዬ ፡ ነበር ። ደግሞ ፦ አባቴ ፡ ብለሽ ፡ ትጠሪኛለሽ ፥ እኔንም ፡
ከመከተል ፡ አትመለሽም ፡ ብዬ ፡ ነበር ።

20 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ሚስት ፡ ባሏን ፡ እንደምታታልል ፡ እንዲሁ ፡ አታለላችኹኝ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

21 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መንገዳቸውን ፡ አጣመዋልና ፥ አምላካቸውንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ረስተዋልና ፥ በወናዎች ፡
ኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ የልመናቸውና ፡ ልቅሷቸው ፡ ድምፅ ፡ ተሰማ ።

22 ፤ ከዳተኛዎች ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ተመለሱ ፥ ከዳተኛነታችኹንም ፡ እፈውሳለኹ ። እንሆ ፥ አንተ ፡ አምላካችን ፡
እግዚአብሔር ፡ ነኽና ፥ ወደንተ ፡ እንመጣለን ።

23 ፤ በእውነት ፡ የኰረብታዎችና ፡ የተራራዎች ፡ ፍጅት ፡ ከንቱ ፡ ናት ፤ በእውነት ፡ የእስራኤል ፡ መዳን ፡ በአምላካችን ፡
በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከትንሽነታችን ፡ ዠምሮ ፡ የአባቶቻችን ፡ ድካም ፥ በጎቻቸውንና ፡ ላሞቻቸውን ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡
ልጆቻቸውንም ፥ ዕፍረት ፡ በልቶባቸዋል ።

25 ፤ ከትንሽነታችን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እኛና ፡ አባቶቻችን ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡
ኀጢአት ፡ ሠርተናልና ፥ የአምላካችንንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰማንምና ፡ በዕፍረታችን ፡
እንጋደም ፥ ውርደታችንም ፡ ይክደነን ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ምዕራፍ ፡ 4 ፤

1 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ብትመለስ ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለስ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ርኵሰትኽንም ፡ ከፊቴ ፡
ብታስወግድ ፥ ባትናወጥም ፥

2 ፤ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ብለኽም ፡ በእውነትና ፡ በቅንነት ፡ በጽድቅም ፡ ብትምል ፥ አሕዛብ ፡ በርሱ ፡ ይባረካሉ ፡
በርሱም ፡ ይመካሉ ።

3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለይሁዳና ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ጥጋቱን ፡ ዕርሻ ፡ ዕረሱ ፥ በሾኽም ፡ ላይ ፡
አትዝሩ ።

4 ፤ እናንተም ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ ስለሠራችኹ ፡ ክፋት ፡ ቍጣዬ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡
እንዳይወጣ ፡ የሚያጠፋውም ፡ ሳይኖር ፡ እንዳያቃጥል ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ተገረዙ ፥ የልባችኹንም ፡ ሸለፈት ፡ አስወግዱ ።

5 ፤ በይሁዳ ፡ ዘንድ ፡ ተናገሩ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ላይ ፡ አውሩና ፦ በአገሪቱ ፡ ላይ ፡ መለከት ፡ ንፉ ፡
በሉ ፤ ጮኻችኹም ፦ ኹላችኹ ፡ ተሰብሰቡ ፡ ወደተመሸጉትም ፡ ከተማዎች ፡ እንግባ ፡ በሉ ።

6 ፤ ከሰሜን ፡ ክፉ ፡ ነገርንና ፡ ጽኑ ፡ ጥፋትን ፡ አመጣለኹና ፡ ወደ ፡ ጽዮን ፡ ዐላማን ፡ አንሡ ፤ ሽሹ ፥ አትዘግዩ ።

7 ፤ አንበሳ ፡ ከጭፍቅ ፡ ዱር ፡ ወጥቷል ፥ አሕዛብንም ፡ የሚዘርፍ ፡ ተነሥቷል ፤ ምድርሽን ፡ ባድማ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡
ከስፍራው ፡ ወጥቷል ፥ ከተማዎችሽም ፡ ሰው ፡ የሌለባቸው ፡ ፍርስራሾች ፡ ይኾናሉ ።

8 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ አልተመለሰምና ፡ ማቅ ፡ ልበሱ ፥ አልቅሱም ፡ ዋይም ፡ በሉ ።

9 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የንጉሡና ፡ የመኳንንቱ ፡ ልብ ፡ ይጠፋል ፥ ካህናቱም ፡ ይደነቃሉ ፡
ነቢያቱም ፡ ይደነግጣሉ ።

10 ፤ እኔም ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ወዮ ፥ አንተ ፡ ሰይፍ ፡ እስከ ፡ ነፍስ ፡ ድረስ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፦ ሰላም ፡
ይኾንላችኋል ፡ ብለኽ ፡ ይህን ፡ ሕዝብና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ እጅግ ፡ አታለልኽ ፡ አልኹ ።

11 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብና ፡ ለኢየሩሳሌም ፦ ለማበጠር ፡ ወይም ፡ ለማጥራት ፡ ሳይኾን ፡ የሚያቃጥል ፡ ነፋስ ፡
በምድረ ፡ በዳ ፡ ካሉ ፡ ከወናዎች ፡ ኰረብታዎች ፡ ወደወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ይመጣል ፤

12 ፤ ስለ ፡ እኔ ፡ ጽኑ ፡ የኾነ ፡ ነፋስ ፡ ከነዚህ ፡ ይመጣል ፡ ይባላል ። አኹንም ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ፍርዴን ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡
እናገራለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

13 ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ ደመና ፡ ይወጣል ፥ ሠረገላዎቹም ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፤ ፈረሶቹም ፡ ከንስር ፡ ይልቅ ፡ ፈጣኖች ፡ ናቸው ። ጠፍተናልና ፥ ወዮልን ።

14 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ትድኚ ፡ ዘንድ ፡ ልብሽን ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ዕጠቢ ። ክፉ ፡ ዐሳብ ፡ የሚኖርብሽ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነው ፧

15 ፤ የተናጋሪ ፡ ድምፅ ፡ ከዳን ፡ ዘንድ ፡ ይናገራልና ፥ ከኤፍሬምም ፡ ኰረብታዎች ፡ መከራን ፡ ያወራልና ።

16 ፤ ለአሕዛብ ፡ አሰሙና ፦ እንሆ ፥ ጠባቂዎች ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ይመጣሉ ፤ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ላይ ፡ ይጮኻሉ ፡ ብላችኹ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ አውሩ ።

17 ፤ በእኔ ፡ ላይ ፡ ዐመፀኛ ፡ ኾናለችና ፡ በዙሪያዋ ፡ ከበው ፡ እንደ ፡ ዕርሻ ፡ ጠባቂዎች ፡ ኾነውባታል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

18 ፤ መንገድሽና ፡ ሥራሽ ፡ ይህን ፡ አድርጎብሻል ፤ ይህ ፡ ክፋትሽ ፡ መራር ፡ ነው ፥ ወደ ፡ ልብሽም ፡ ደርሷል ።

19 ፤ አንገቴ! አንገቴ! ልቤ ፡ በጣም ፡ ታሟል ፥ በውስጤም ፡ ልቤ ፡ ታውኮብኛል ፤ ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ የመለከትን ፡ ድምፅና ፡ የሰልፍን ፡ ውካታ ፡ ሰምተሻልና ፥ ዝም ፡ እል ፡ ዘንድ ፡ አልችልም ።

20 ፤ መከራ ፡ በመከራ ፡ ላይ ፡ ተጠርቷል ፤ ምድርም ፡ ኹሉ ፡ ተበዝብዛለችና ፤ በድንገትም ፡ ድንኳኔ ፡ በቅጽበት ፡ ዐይንም ፡ መጋረጃዎቼ ፡ ጠፉ ።

21 ፤ ዐላማውን ፡ የምመለከት ፥ የመለከቱንስ ፡ ድምፅ ፡ የምሰማ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧

22 ፤ ሕዝቤ ፡ ሰንፈዋልና ፥ አላወቁኝም ፤ ሰነፎች ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፥ ማስተዋልም ፡ የላቸውም ፤ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ለማድረግ ፡ ብልኀተኛዎች ፡ ናቸው ፥ በጎ ፡ ነገርን ፡ ማድረግ ፡ ግን ፡ አያውቁም ።

23 ፤ ምድሪቱን ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፥ ባዶ ፡ ነበረች ፡ አንዳችም ፡ አልነበረባትም ፤ ሰማያትንም ፡ አየኹ ፥ ብርሃንም ፡ አልነበረባቸውም ።

24 ፤ ተራራዎችን ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፥ ተንቀጠቀጡ ፥ ኰረብታዎችም ፡ ኹሉ ፡ ተናወጡ ።

25 ፤ አየኹ ፥ እንሆም ፥ ሰው ፡ አልነበረም ፥ የሰማይም ፡ ወፎች ፡ ኹሉ ፡ ሸሽተው ፡ ነበር ።

26 ፤ አየኹ ፥ እንሆም ፥ ፍሬያማ ፡ ዕርሻ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኾነች ፥ ከተማዎችም ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ከጽኑ ፡ ቍጣው ፡ የተነሣ ፡ ፈርሰው ፡ ነበር ።

27 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ባድማ ፡ ትኾናለች ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ፈጽሜ ፡ አላጠፋትም ።

28 ፤ ስለዚህ ፥ ምድር ፡ ታለቅሳለች ፥ በላይም ፡ ሰማይ ፡ ይጠቍራል ፤ ተናግሬያለኹና ፥ ዐስቤያለኹም ፤ አልጸጸትም ፡ ከርሱም ፡ አልመለስም ።

29 ፤ ከፈረሰኛዎችና ፡ ከቀስተኛዎች ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ከተማ ፡ ኹሉ ፡ ሸሽታለች ፤ ወደችፍግ ፡ ዱርም ፡ ይገባሉ ፡ በቋጥኝ ፡ ላይም ፡ ይወጣሉ ፤ ከተማ ፡ ኹሉ ፡ ተለቅቃለች ፡ የሚቀመጥባትም ፡ ሰው ፡ የለም ።

30 ፤ አንቺም ፡ የተበዘበዝሽ ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ ታደርጊያለሽ ፧ ቀይ ፡ በለበስሽ ፡ ጊዜ ፥ በወርቅ ፡ አንባርም ፡ ባጌጥሽ ፡ ጊዜ ፥ ዐይንሽንም ፡ በኵል ፡ በተኳልሽ ፡ ጊዜ ፥ በከንቱ ፡ ታጌጫለሽ ፤ ውሽማዎችሽ ፡ አቃለሉሽ ፥ ነፍስሽን ፡ ይሿታል ።

31 ፤ እንደምታምጥ ፡ የበኵሯንም ፡ እንደምትወልድ ፡ ሴት ፡ ድምፅ ፡ ሰምቻለኹና ፤ የጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ድምፅ ፡ በድካም ፡ ይሰልላል ፥ እጆቿንም ፡ ትዘረጋለችና ፦ ተገድለው ፡ ከሞቱት ፡ የተነሣ ፡ ነፍሴ ፡ ዝላለችና ፡ ወዮልኝ! አለች ።

__________________ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 5 ፤

1 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ መንገድ ፡ እየተመላለሳችኹ ፡ ሩጡ ፥ ተመልከቱም ፥ ዕወቁም ፥ በአደባባይዋም ፡ ፈልጉ ፤ ፍርድን ፡ የሚያደርገውን ፡ እውነትንም ፡ የሚሻውን ፡ ሰው ፡ ታገኙ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይቅር ፡ እላታለኹ ።

2 ፤ እነርሱም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ቢሉ ፡ የሚምሉት ፡ በሐሰት ፡ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

3 ፤ አቤቱ ፥ ዐይንኽ ፡ እውነትን ፡ የምትመለከት ፡ አይደለችምን ፨ አንተ ፡ ቀሥፈኻቸዋል ፥ ነገር ፡
ግን ፥ አላዘኑም ፥ ቀጥቀጠኻቸውማል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ተግሣጽን ፡ እንቢ ፡ አሉ ፤ ፊታቸውን ፡ ከድንጋይ ፡ ይልቅ ፡
አጠንክረዋል ፤ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አሉ ።

4 ፤ እኔም ፦ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድና ፡ የአምላካቸውን ፡ ሕግ ፡ አላወቁምና ፡ እነዚህ ፡ በእውነት ፡ ድኻዎችና ፡
ሰነፎች ፡ ናቸው ፤

5 ፤ ወደ ፡ ታላላቆቹ ፡ እኼዳለኹ ፡ እናገራቸውማለኹ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መንገንድና ፡ የአምላካቸውን ፡ ሕግ ፡
ያውቃሉና ፡ አልኹ ። እነዚህ ፡ ግን ፡ ቀንበሩን ፡ በአንድነት ፡ ሰብረዋል ፥ እስራቱንም ፡ ቈርጠዋል ።

6 ፤ ስለዚህ ፥ ኀጢአታቸው ፡ በዝቷልና ፥ የክዳታቸውም ፡ ብዛት ፡ ጸንቷልና ፤ ስለዚህ ፥ አንበሳ ፡ ከዱር ፡ ወጥቶ ፡
ይሰብራቸዋል ፥ የበረሓም ፡ ተኵላ ፡ ያጠፋቸዋል ፥ ነብርም ፡ በከተማዎቻቸው ፡ ላይ ፡ ይተጋል ፥ ከዚያም ፡ የሚወጣ ፡
ኹሉ ፡ ይነጠቃል ።

7 ፤ በእነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ይቅር ፡ የምልሽ ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ነው ፨ ልጆችሽ ፡ ትተውኛል ፡ አማልክትም ፡ ባልኾኑ ፡
ምለዋል ፤ ካጠገብ኿ቸውም ፡ በኋላ ፡ አመነዘሩ ፡ በጋለሞታዎቹም ፡ ቤት ፡ ተሰበሰቡ ።

8 ፤ እንደ ፡ ተቀለቡ ፡ ፈረሶች ፡ ኾኑ ፤ እያንዳንዳቸውም ፡ ከባልንጀራዎቻቸው ፡ ሚስቶች ፡ ኋላ ፡ አሽካኩ ።

9 ፤ በእውኑ ፡ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ አልቀሥፍምን ፨ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነፍሴስ ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡
አትበቀልምን ፨

10 ፤ ወደ ፡ ቅጥሯ ፡ ወጥታችኹ ፡ አፍርሱ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ፈጽማችኹ ፡ አታጥፉ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ አይደሉምና ፡
ቅርንጫፏን ፡ ውሰዱ ።

11 ፤ የእስራኤል ፡ ቤትና ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ወንጅለዋል ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

12 ፤ እነርሱም ፦ ርሱ ፡ አይደለም ፥ ክፉ ፡ ነገርም ፡ አይመጣብንም ፡ ሰይፍንና ፡ ራብንም ፡ አናይም ፤ ነቢያትም ፡ ነፋስ ፡
ይኾናሉ ፥

13 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ የለም ፥ እንዲህም ፡ ይደረግባቸዋል ፡ ብለው ፡ እግዚአብሔርን ፡
ክደዋል ።

14 ፤ ስለዚህም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዚህ ፡ ቃል ፡ ተናግራች኿ልና ፥ እንሆ ፥ በአፍኽ ፡
ውስጥ ፡ ቃሌን ፡ እሳት ፡ ይህንም ፡ ሕዝብ ፡ ዕንጨት ፡ አደርጋለኹ ፥ ትበላቸውማለች ።

15 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ ሕዝብን ፡ ከሩቅ ፡ አመጣባች኿ለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ኀያል ፡ ጥንታዊ ፡
ሕዝብ ፡ ነው ፥ ቋንቋቸውንም ፡ የማታውቀው ፡ የሚናገሩትንም ፡ የማታስተውለው ፡ ሕዝብ ፡ ነው ።

16 ፤ የፍላጻቸውም ፡ ሰገባ ፡ እንደ ፡ ተከፈተ ፡ መቃብር ፡ ነው ፥ ኹሉም ፡ ኀያላን ፡ ናቸው ።

17 ፤ መከርኽንና ፡ እንጀራኽን ፡ ይበላሉ ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችኽንም ፡ ይበሏቸዋል ፤ በጎችኽንና ፡ ላሞችኽንም ፡
ይበላሉ ፤ ወይንኽንና ፡ በለስኽንም ፡ ይበላሉ ፤ የምትታመናቸውን ፡ የተመሸጉ ፡ ከተማዎችን ፡ በሰይፍ ፡ ይደበድባሉ ።

18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዚያ ፡ ዘመን ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ፈጽሜ ፡ አላጠፋችኹም ።

19 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ እናንተ ፦ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ምን ፡
አደረገብን ፨ ብትሉ ፥ አንተ ፦ እንደ ፡ ተዋችኹኝ ፡ በአገራችኹም ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ እንዳመለካችኹ ፥ እንዲሁ ፡
ለእናንተ ፡ ባልኾነ ፡ አገር ፡ ለሌላዎች ፡ ሰዎች ፡ ትገዛላችኹ ፡ ትላቸዋለኽ ።

20 ፤ ይህን ፡ በያዕቆብ ፡ ቤት ፡ አውሩ ፥ በይሁዳም ፡ አሰሙ ።

21 ፤ እናንተ ፡ ሰነፎች ፡ ልበ ፡ ቢሶች ፥ ዐይን ፡ እያላችኹ ፡ የማታዩ ፥ ዦሮም ፡ እያላችኹ ፡ የማትሰሙ ፡ ሕዝብ ፡
ሆይ ፥ ይህን ፡ ስሙ ።

22 ፤ በእውኑ ፡ እኔን ፡ አትፈሩምን ፨ ከፊቴስ ፡ አትደነግጡምን ፨ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እንዳያልፍ ፡ አሸዋን ፡
በዘለዓለም ፡ ትእዛዝ ፡ ለባሕር ፡ ዳርቻ ፡ አድርጌያለኹ ፤ ሞገዱም ፡ ቢናወጥ ፡ አያሸንፍም ፥ ቢጮኽም ፡ አያልፍበትም ።

http://www.gzamargna.net

www.ethiopianorthodox.org

23 ፤ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ የሸፈተና ፡ ያመፀ ፡ ልብ ፡ አላቸው ፤ ዐምፀዋል ፥ ኼደውማል ።

24 ፤ በልባቸውም ፦ የፊተኛውንና ፡ የኋለኛውን ፡ ዝናብ ፡ በጊዜው ፡ የሚሰጠውን ፥ ለመከርም ፡ የተመደቡትን ፡
ወራት ፡ የሚጠብቅልንን ፡ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንፍራ ፡ አላሉም ።

25 ፤ በደላችኹ ፡ እነዚህን ፡ አስቀርታለች ፥ ኀጢአታችኹም ፡ መልካምን ፡ ነገር ፡ ከለከለቻችኹ ።

26 ፤ በሕዝቤ ፡ መካከል ፡ ክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ ተገኝተዋል ፤ እንደ ፡ አጥማጆችም ፡ ያደባሉ ፥ ወጥመድንም ፡ ይዘረጋሉ ፡
ሰዎችንም ፡ ያጠምዳሉ ።

27 ፤ ቀፎ ፡ ወፎችን ፡ እንደሚሞላ ፥ እንዲሁ ፡ ቤታቸው ፡ ሽንገላን ፡ ሞልታለች ፤ እንዲሁም ፡ ከብረዋል ፡ ባለጠጋዎችም ፡
ኾነዋል ።

28 ፤ ወፍረዋል ፡ ሰብተውማል ፥ ክፉታቸውንም ፡ ያለልክ ፡ አብዝተዋል ፤ የድኻ ፡ አደጎች ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ እንዲኾን ፡
አልተሟገቱላቸውም ፥ የችግረኛዎችንም ፡ ፍርድ ፡ አልፈረዱላቸውም ።

29 ፤ በእውኑ ፡ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ አልቀሥፍምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነፍሴስ ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡
አትበቀልምን ፧

30 ፤ የምታስደንቅና ፡ የምታስደነግጥ ፡ ነገር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኾናለች ፤

31 ፤ ነቢያት ፡ በሐሰት ፡ ትንቢት ፡ ይናገራሉ ፥ ካህናትም ፡ በእነዚህ ፡ እጅ ፡ ይገዛሉ ፥ ሕዝቤም ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡
ይወዳሉ ፤ በፍጻሜውስ ፡ ምን ፡ ታደርጋላችኹ ፧

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ምዕራፍ ፡ 6 ፤

1 ፤ እናንተ ፡ የብንያም ፡ ልጆች ፥ ክፉ ፡ ነገር ፡ ታላቅም ፡ ጥፋት ፡ ከሰሜን ፡ ይጐበኛልና ፥ ከኢየሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡
ሽሹ ፥ በቴቁሔ ፡ መለከቱን ፡ ንፉ ፥ በቤትሐካሪም ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ አንሡ ።

2 ፤ የተዋበችውንና ፡ የተሰባቀለችውን ፡ የጽዮንን ፡ ልጅ ፡ አጐሰቍላለኹ ።

3 ፤ እረኛዎችና ፡ መንጋዎቻቸው ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ይመጣሉ ፥ በዙሪያዋም ፡ ድንኳኖቻቸውን ፡
ይተክሉባታል ፥ እያንዳንዱም ፡ በስፍራው ፡ መንጋውን ፡ ያሰማራል ።

4 ፤ በርሷ ፡ ላይ ፡ ሰልፍ ፡ አዘጋጁ ፥ ተነሡ ፥ በቀትርም ፡ እንውጣ ። ቀኑ ፡ መሽቷልና ፥ የማታውም ፡ ጥላ ፡
ረዝሟልና ፥ ወዮልን ።

5 ፤ ተነሡ ፡ በሌሊትም ፡ እንውጣ ፥ አዳራሾቿንም ፡ እናፍርስ ።

6 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ዛፎቿን ፡ ቍረጡ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ላይ ፡ ዐፈርን ፡
ደልድሉ ፤ ይህች ፡ ከተማ ፡ የምትቀሥፍ ፡ ናት ፤ መካከሏ ፡ ኹሉ ፡ ግፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

7 ፤ በጕድጓድ ፡ ውሃ ፡ እንደሚፈልቅ ፥ እንዲሁ ፡ ክፋቷ ፡ ከርሷ ፡ ዘንድ ፡ ይፈልቃል ፤ ግፍና ፡ ቅሚያ ፡ በርሷ ፡ ዘንድ ፡
ይሰማል ፥ ደዌና ፡ ቍስልም ፡ ኹልጊዜ ፡ በፊቴ ፡ አለ ።

8 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ነፍሴ ፡ ከአንቺ ፡ እንዳትለይ ፥ አንቺንም ፡ ባድማና ፡ ወና ፡ እንዳላደርግሽ ፥ ተግሣጽን ፡ ተቀበዪ ።

9 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰው ፡ ወይኑን ፡ እንደሚቃርም ፥ እንዲሁ ፡ ከእስራኤል ፡ የቀሩትን ፡ ፈጽሞ ፡
ይቃርሟቸዋል ፤ እጅኽንም ፡ እንደ ፡ ለቃሚ ፡ ወደ ፡ እንቅብ ፡ ዘርጋ ።

10 ፤ ይሰሙኝስ ፡ ዘንድ ፡ ለማን ፡ እናገራለኹ ፧ ለማንስ ፡ አስጠነቅቃለኹ ፧ እንሆ ፥ ጆሮቻቸው ፡ ያልተገረዘች ፡ ናት ፡
ለመስማትም ፡ አይችሉም ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ለስድብ ፡ ኾኖባቸዋል ፥ ደስም ፡ አያሠኛቸውም ።

11 ፤ ስለዚህ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ተሞልቻለኹ ፤ ከመታገሥ ፡ ደክሜያለኹ ፤ በሜዳ ፡ በሕፃናት ፡ ላይ ፡
በጕልማሳዎችም ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ በአንድነት ፡ አፍስሰው ፤ ባል ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ ሽማግሌውም ፡ ከጐበዙ ፡ ጋራ ፡
ይያያዛልና ።



www.ethiopianorthodox.org

12 ፤ እጄን ፡ በምድር ፡ በሚኖሩ ፡ ላይ ፡ እዘረጋለኹና ፥ ቤቶቻቸው ፡ ዕርሻዎቻቸውም ፡ ሴቶቻቸውም ፡ በአንድነት ፡
ለሌላዎች ፡ ይኾናሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

13 ፤ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ዅሉ ፡ ሥሥትን ፡ ያስባሉና ፥ ከነቢዩም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ካህኑ ፡ ድረስ ፡
ዅሉ ፡ በተንኰል ፡ ያደርጋሉና ።

14 ፤ የሕዝቤንም ፡ ስብራት ፡ በጥቂቱ ፡ ይፈውሳሉ ፤ ሰላም ፡ ሳይኾን ፦ ሰላም ፡ ሰላም ፡ ይላሉ ።

15 ፤ ርኩስን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ ዐፍረዋልን ፧ ምንም ፡ አላፈሩም ፥ ዕፍረትንም ፡ አላወቁም ፤ ስለዚህ ፥ ከሚወድቁ ፡
ጋራ ፡ ይወድቃሉ ፤ በጐበኘኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ይዋረዳሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

16 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ቁሙ ፡ ተመልከቱም ፥ የቀደመችውንም ፡ መንገድ ፡
ጠይቁ ፤ መልካሚቱ ፡ መንገድ ፡ ወዴት ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ዕወቁ ፥ በርሷም ፡ ላይ ፡ ኺዱ ፥ ለነፍሳችኹም ፡ ዕረፍት ፡
ታገኛላችኹ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፦ አንኼድባትም ፡ አሉ ።

17 ፤ እኔም ፦ የመለከቱን ፡ ድምፅ ፡ አድምጡ ፡ ብዬ ፡ ጠባቂዎችን ፡ ሾምኹባችኹ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፦ አናደምጥም ፡
አሉ ።

18 ፤ አሕዛብ ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ ስሙ ፤ ማኅበር ፡ ሆይ ፥ እነዚያ ፡ የሚያገኛቸውን ፡ ዕወቁ ።

19 ፤ ምድር ፡ ሆይ ፥ ስሚ ፤ እንሆ ፥ ቃሌን ፡ ስላልሰሙ ፥ ሕጌንም ፡ ስለ ፡ ጣሉ ፥ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ የዐሳባቸውን ፡
ፍሬ ፥ ክፉን ፡ ነገር ፡ አመጣባቸዋለኹ ።

20 ፤ ስለ ፡ ምንስ ፡ ከሳባ ፡ ዕጣንን ፥ ከሩቅም ፡ አገር ፡ ቀረፋን ፡ ታቀርቡልኛላችኹ ፧ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕታችኹን ፡
አልቀበለውም ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕታችኹም ፡ ደስ ፡ አያሠኘኝም ።

21 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ከዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ ዕንቅፋቶችን ፡ አደርጋለኹ ፤ አባቶችና ፡
ልጆች ፡ በአንድነት ፡ ይሰናከሉባቸዋል ፥ ጎረቤትና ፡ ባልንጀራም ፡ ይጠፋሉ ።

22 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ሕዝብ ፡ ከሰሜን ፡ አገር ፡ ይመጣል ፥ ታላቅ ፡ ሕዝብም ፡ ከምድር ፡
ዳርቻ ፡ ይነሣል ።

23 ፤ ቀስትንና ፡ ጦርን ፡ ይይዛሉ ፤ ጨካኞች ፡ ናቸው ፥ ምሕረትንም ፡ አያደርጉም ፤ ድምፃቸው ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡
ይተማል ፥ በፈረሶችም ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ ፤ የጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ለሰልፍ ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ሰው ፡
እያንዳንዳቸው ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ተሰለፉ ።

24 ፤ ወሬውን ፡ ሰምተናል ፥ እጃችን ፡ ደክማለች ፤ ምጥ ፡ ወላድን ፡ ሴት ፡ እንደሚይዛት ፡ ጭንቀት ፡ ይዞናል ።

25 ፤ የጠላት ፡ ሰይፍና ፡ ድንጋጤ ፡ ከበዋችኋልና ፥ ወደ ፡ ሜዳ ፡ አትውጡ ፡ በምንገድም ፡ ላይ ፡ አትኺዱ ።

26 ፤ የሕዝቤ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ማቅ ፡ ልበሺ ፡ በዐመድም ፡ ውስጥ ፡ ተንከባለዪ ፤ አጥፊ ፡ በላያችን ፡ በድንገት ፡
ይመጣብናልና ፥ ለአንድያ ፡ ልጅ ፡ እንደሚደረግ ፡ ልቅሶ ፥ መራራ ፡ ልቅሶ ፡ አልቅሺ ።

27 ፤ መንገዳቸውን ፡ እንድታውቅና ፡ እንድትፈትን ፡ በሕዝቤ ፡ መካከል ፡ ፈታኝ ፡ አድርጌኻለኹ ።

28 ፤ እነርሱ ፡ ዅሉ ፡ እጅግ ፡ ዐመፀኞች ፡ ናቸው ፤ በጠማማነት ፡ ይኼዳሉ ፤ ናስና ፡ ብረት ፡ ናቸው ፤ ዅሉ ፡
ርኵሰትን ፡ ያደርጋሉ ።

29 ፤ ወናፍ ፡ አናፋ ፡ ርሳሱም ፡ በእሳት ፡ ቀለጠ ፤ አንጥረኛውም ፡ መልሶ ፡ በከንቱ ፡ ያቀልጠዋል ፤ ኀጢአተኞች ፡
አልተወገዱም ።

30 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጥሏቸዋልና ፥ የተጣለ ፡ ብር ፡ ብለው ፡ ይጠሯቸዋል ።

__________________ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 7 ፤

1 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦



www.ethiopianorthodox.org

2 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በር ፡ ቁም ፥ ይህንም ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ተናገር ፦ እግዚአብሔርን ፡ ልታመልኩ ፡
በእነዚህ ፡ በሮች ፡ የምትገቡ ፡ ከይሁዳ ፡ ያላችኹ ፡ ዅሉ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

3 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ መንገዳችኹንና ፡ ሥራችኹን ፡ አሳምሩ ፡ በዚህም ፡ ስፍራ ፡
አሳድራችኋለኹ ።

4 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፥ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፥ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እያላችኹ ፡
በሐሰት ፡ ቃል ፡ አትታመኑ ።

5 ፤ መንገዳችኹንና ፡ ሥራችኹን ፡ ፈጽማችኹ ፡ ብታሳምሩ ፥ በሰውና ፡ በጎረቤቱ ፡ መካከል ፡ ቅን ፡ ፍርድ ፡ ብትፈርዱ ፥

6 ፤ መጻተኛውንና ፡ ድኻ ፡ አደጉን ፡ መበለቲቱንም ፡ ባትገፉ ፥ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ንጹሕ ፡ ደምን ፡ ባታፈሱ ፥ ክፉም ፡
ሊኾንባችኹ ፡ እንግዳዎችን ፡ አማልክት ፡ ባትከተሉ ፥

7 ፤ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ በሰጠኋቸው ፡ ምድር ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ አሳድራችኋለኹ ።

8 ፤ እንሆ ፥ በማትረቡበት ፡ በሐሰት ፡ ቃል ፡ ታምናችኋል ።

9 ፤ ትሰርቃላችኹ ፥ ትገድላላችኹ ፥ ታመነዝራላችኹ ፥ በሐሰትም ፡ ትምላላችኹ ፥ ለበዓልም ፡
ታጥናላችኹ ፥ የማታውቋቸውንም ፡ እንግዳዎች ፡ አማልክት ፡ ትከተላላችኹ ፤

10 ፤ መጣችኹም ፥ ስሜም ፡ በተጠራበት ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ በፊቴ ፡ ቆማችኹ ፦ ይህን ፡ አስጸያፊ ፡ የኾነ ፡ ነገርን ፡ ዅሉ ፡
አላደረግንም ፡ አላችኹ ።

11 ፤ ይህስ ፡ ስሜ ፡ የተጠራበት ፡ ቤት ፡ በዐይናችኹ ፡ የሌቦች ፡ ዋሻ ፡ ኾኗልን ፧ እንሆ ፥ እኔ ፡ አይቻለኹ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ።

12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ስሜን ፡ ወዳሳደርኹበት ፡ በሴሎ ፡ ወደነበረው ፡ ስፍራዬ ፡ ኺዱ ፥ ከሕዝቤም ፡
ከእስራኤል ፡ ክፋት ፡ የተነሣ ፡ ያደረግኹበትን ፡ እዩ ።

13 ፤ አኹንም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ ስላደረጋችኹ ፥ በማለዳም ፡ ተነሥቼ ፡ በተናገርኋችኹ ፡ ጊዜ ፡
ስላልሰማችኹ ፥ በጠራኋችኹም ፡ ጊዜ ፡ ስላልመለሳችኹ ፥

14 ፤ ስለዚህ ፥ በሴሎ ፡ እንዳደረግኹ ፡ እንዲሁ ፥ ስሜ ፡ በተጠራበት ፥ በምትታመኑበት ፡ ቤት ፥ ለእናንተና ፡
ለአባቶቻችኹም ፡ በሰጠኋችኹ ፡ ስፍራ ፡ አደርጋለኹ ።

15 ፤ የኤፍሬምንም ፡ ዘር ፡ ዅሉ ፥ ወንድሞቻችኹን ፡ ዅሉ ፡ እንደ ፡ ጣልኹ ፥ እንዲሁ ፡ ከፊቴ ፡ እጥላችኋለኹ ።

16 ፤ እንግዲህም ፡ አልሰማኽምና ፡ ስለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አትጸልይ ፡ ስለ ፡ እነርሱም ፡ ልመናና ፡ ጸሎት ፡
አታድርግ ፤ አትማልድላቸው ።

17 ፤ እነርሱስ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉትን ፡ አታይምን ፧

18 ፤ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፥ ለሰማይ ፡ ንግሥት ፡ ዕንጐቻ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ለሌላዎችም ፡ አማልክት ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባን ፡
እንዲያፈሱ ፡ ልጆች ፡ ዕንጨት ፡ ይሰበስባሉ ፥ አባቶችም ፡ እሳት ፡ ያነዳሉ ፥ ሴቶችም ፡ ዱቄት ፡ ይለውሳሉ ።

19 ፤ እኔን ፡ ያስቈጣሉን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ለፊታቸውስ ፡ ዕፍረት ፡ አይደለምን ፧

20 ፤ እንግዲህም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ቍጣዬና ፡ መዓቴ ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፥ በሰውና ፡
በእንስሳ ፡ ላይ ፥ በዱር ፡ ዛፎችና ፡ በምድር ፡ ፍሬ ፡ ላይ ፡ ይፈሳል ፤ ይነዳል ፥ አይጠፋምም ።

21 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለሌላ ፡ መሥዋዕታችኹ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕታችኹን ፡
ጨምሩ ፥ ሥጋውንም ፡ ብሉ ።

22 ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ባወጣኋችኹ ፡ ቀን ፡ ስለሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕት ፡ ለአባቶቻችኹ ፡
አልተናገርኹምና ፥ አላዘዝኋቸውምም ።

23 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ ቃሌን ፡ ስሙ ፥ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናችኋለኹ ፡ እናንተም ፡ ሕዝብ ፡ ትኾኑኛላችኹ ፤ መልካምም ፡



www.ethiopianorthodox.org

ይኾንላችኹ ፡ ዘንድ ፡ ባዘዝኋችኹ ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ኺዱ ፡ ብዬ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አዘዝኋቸው ።

24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በክፉ ፡ ልባቸው ፡ ዐሳብና ፡ እልከኝነት ፡ ኼዱ ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ ሳይኾን ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ኼዱ ፡
እንጂ ፡ አልሰሙም ፡ ጆሯቸውንም ፡ አላዘነበሉም ።

25 ፤ አባቶቻችኹ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከወጡበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፥ በየዕለቱ ፡ እየማለድኹ ፡
ባሪያዎቼን ፡ ነቢያትን ፡ ኹሉ ፡ ልኬባችኹ ፡ ነበር ።

26 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዐንገታቸውን ፡ አደነደኑ ፡ እንጂ ፡ አልሰሙኝም ፡ ጆሯቸውንም ፡ አላዘነበሉም ፤ አባቶቻቸውም ፡
ካደረጉት ፡ ይልቅ ፡ የባሰ ፡ አደረጉ ።

27 ፤ በዚህም ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ትነግራቸዋለኽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አይሰሙኽም ፤ ትጠራቸውማለኽ ፥ ነገር ፡
ግን ፥ አይመልሱልኽም ።

28 ፤ አንተም ፦ የአምላኩን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ያልሰማ ፥ ተግሣጽንም ፡ ያልተቀበለ ፡ ሕዝብ ፡ ይህ ፡
ነው ፤ እውነት ፡ ጠፍቷል ፡ ከአፋቸውም ፡ ተቈርጧል ፡ ትላቸዋለኽ ።

29 ፤ እግዚአብሔር ፡ የቍጣውን ፡ ትውልድ ፡ ጥሏልና ፥ ትቶታልምና ፡ ጠጕርሽን ፡ ቍረጪ ፥ ጣዪውም ፥ በወናዎች ፡
ኰረብታዎችም ፡ ላይ ፡ አሙሺ ።

30 ፤ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ በፊቴ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ሠርተዋል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ያረክሱትም ፡ ዘንድ ፡ ስሜ ፡
በተጠራበት ፡ ቤት ፡ ርኵሰታቸውን ፡ አኑረዋል ።

31 ፤ እኔም ፡ ያላዘዝኹትንና ፡ በልቤ ፡ ያላሰብኹትን ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉ ፡ ዘንድ ፡
በሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ያለችውን ፡ የቶፌትን ፡ መስገጃዎች ፡ ሠረተዋል ።

32 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ ስፍራ ፡ ከማጣት ፡ የተነሣ ፡ በቶፌት ፡ ይቀበራሉና ፡ የዕርድ ፡ ሸለቆ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ቶፌት ፡
ወይም ፡ የሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ዳግመኛ ፡ የማይባልበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

33 ፤ የዚህም ፡ ሕዝብ ፡ ሬሳ ፡ ለሰማይ ፡ ወፎችና ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ መብል ፡ ይኾናል ፥ የሚያስፈራራቸውም ፡ የለም ።

34 ፤ ምድሪቱም ፡ ባድማ ፡ ትኾናለችና ፡ ከይሁዳ ፡ ከተማዎችና ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ የእልልታን ፡ ድምፅና ፡
የደስታን ፡ ድምፅ ፥ የወንድ ፡ ሙሽራን ፡ ድምፅና ፡ የሴት ፡ ሙሽራን ፡ ድምፅ ፡ አጠፋለኹ ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ምዕራፍ ፡ 8 ፤

1 ፤ በዚያን ፡ ዘመን ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የይሁዳን ፡ ነገሥታት ፡ ዐጥንትና ፡ የመኳንንቶቹን ፡ ዐጥንት ፥ የካህናቱን ፡
ዐጥንትና ፡ የነቢያቱን ፡ ዐጥንት ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ ሰዎች ፡ ዐጥንት ፡ ከመቃብራቸው ፡ ያወጣሉ ።

2 ፤ በወደዷቸውና ፡ ባመለኳቸው ፥ በተከተሏቸውና ፡ በፈለጓቸው ፥ በሰገዱላቸውም ፡ በፀሓይና ፡ በጨረቃ ፡ በሰማይም ፡
ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ይዘረጓቸዋል ፤ አያከማቿቸውም ፡ አይቀብሯቸውምም ፥ በምድርም ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡
ይኾናሉ ።

3 ፤ እኔም ፡ ባሳደድኋቸው ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ የቀሩ ፥ ከዚች ፡ ክፉ ፡ ወገን ፡ የተረፉ ፡ ቅሬታዎች ፡ ኹሉ ፥ ከሕይወት ፡
ይልቅ ፡ ሞትን ፡ ይመርጣሉ ።

4 ፤ እንዲህም ፡ ትላቸዋለኽ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የወደቁ ፡ አይነሡምን ፧ የሳተስ ፡ አይመለስምን ፧

5 ፤ እንግዲህ ፡ ይህ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሕዝብ ፡ ዘወትር ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ይመለሳል ፧ ተንኰልን ፡ ይዟል ፡
ሊመለስም ፡ እንቢ ፡ ብሏል ።

6 ፤ አደመጥኹ ፡ ሰማኹም ፤ ቅንን ፡ ነገር ፡ አልተናገሩም ፤ ማናቸውንም ፦ ምን ፡ አድርጌያለኹ ፧ ብሎ ፡ ከክፋቱ ፡
ንስሓ ፡ የገባ ፡ የለም ፤ ወደ ፡ ሰልፍም ፡ እንደሚሮጥ ፡ ፈረስ ፡ እያንዳንዱ ፡ በየመንገዱ ፡ ይኼዳል ።

7 ፤ ሽመላ ፡ በሰማይ ፡ ጊዜዋን ፡ ዐውቃለች ፤ ዋኖስና ፡ ጨረባ ፡ ዋልያም ፡ የመምጣታቸውን ፡ ጊዜ ፡ ይጠብቃሉ ፤ ሕዝቤ ፡
ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፍርድ ፡ አላወቁም ።



www.ethiopianorthodox.org

8 ፤ እናንተስ ። ጥበበኛዎች ፡ ነን ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ሕግ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ እንዴት ፡ ትላላችኹ ፧ እንሆ ፥ የጸሓፊ ፡ ብርዕ ፡ ሐሰተኛ ፡ ነው ፥ በሐሰትም ፡ አድርጓል ።

9 ፤ ጥበበኛዎች ፡ ዐፍረዋል ፥ ደንግጠውማል ፥ ተማርከውማል ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ጥለዋል ፤ ምን ፡ ዐይነት ፡ ጥበብ ፡ አላቸው ፧

10 ፤ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ዅሉ ፡ ሥሥትን ፡ ያስባሉና ፥ ከነቢዩም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ካህኑ ፡ ድረስ ፡ ዅሉ ፡ በተንኰል ፡ ያደርጋሉና ፡ ስለዚህ ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ ለሌላዎች ፥ ዕርሻቸውንም ፡ ለሚወርሱባቸው ፡ እሰጣለኹ ።

11 ፤ የሕዝቤንም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ስብራት ፡ በጥቂቱ ፡ ይፈውሳሉ ፤ ሰላም ፡ ሳይኾን ፦ ሰለም ፡ ሰላም ፡ ይላሉ ።

12 ፤ አስጸያፊ ፡ ነገርን ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ ዐፍረዋልን ፧ ምንም ፡ አላፈሩም ፥ ዕፍረትንም ፡ አላወቁም ፤ ስለዚህ ፥ ከሚወድቁ ፡ ጋራ ፡ ይወድቃሉ ፤ በጐበኘኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ይዋረዳሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

13 ፤ ፈጽሜ ፡ አጠፋችኋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ በወይን ፡ ላይ ፡ ፍሬ ፥ በበለስ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ በለስ ፡ አይኾንም ፥ ቅጠልም ፡ ይረግፋል ፤ የሚያልፉባቸውንም ፡ ሰጠኋቸው ።

14 ፤ ዝም ፡ ብለን ፡ ለምን ፡ እንቀመጣለን ፧ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ በደልን ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ አጥፍቶናልና ፥ የሐሞትንም ፡ ውሃ ፡ አጠጥቶናልና ፥ ተሰብሰባችኹ ፡ ወደተመሸጉ ፡ ከተማዎች ፡ እንግባ ፥ በዚያም ፡ እንጥፋ ።

15 ፤ ሰላምን ፡ በተስፋ ፡ ተጠባበቅን ፥ መልካምም ፡ አልተገኘም ፤ መጠገንን ፡ በተስፋ ፡ ተጠባበቅን ፥ እንሆም ፥ ድንጋጤ ፡ ኾነ ።

16 ፤ የፈረሰኛዎቹ ፡ ድምፅ ፡ ከዳን ፡ ተሰማ ፤ ከዐርበኛዎች ፡ ፈረሶች ፡ ማሽካካት ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ዅሉ ፡ ተንቀጠቀጠች ፤ መጡም ፡ ምድሪቱንና ፡ በርሷም ፡ ያለውን ፡ ዅሉ ፥ ከተማዪቱንና ፡ የተቀመጡባትንም ፡ በሉ ።

17 ፤ እንሆ ፥ አስማት ፡ የማይከለክላቸውን ፡ እባቦችንና ፡ እፍኝቶችን ፡ እሰድባችኋለኹ ፤ እነርሱም ፡ ይነድፏችኋል ።

18 ፤ ሐዘኔ ፡ የማይጽናና ፡ ነው ፥ ልቤም ፡ በውስጤ ፡ ደክሟል ።

19 ፤ እንሆ ፦ እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ የለምን ፧ ወይስ ፡ ንጉሧ ፡ በርሷ ፡ ዘንድ ፡ የለምን ፧ የሚል ፡ የወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ጩኸት ፡ ድምፅ ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ተሰማ ። በተቀረጹ ፡ ምስሎቻቸውና ፡ በባዕድ ፡ ከንቱነትስ ፡ ያስቈጡኝ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

20 ፤ መከሩ ፡ ዐልፏል ፥ በጋው ፡ ኼዷል ፥ እኛም ፡ አልዳንም ።

21 ፤ በሕዝቤ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ስብራት ፡ እኔ ፡ ተሰብሬያለኹ ፡ ጠቍሬማለኹ ፤ አድናቆትም ፡ ይዞኛል ።

22 ፤ በገለዓድ ፡ የሚቀባ ፡ መድኀኒት ፡ የለምን ፧ ወይስ ፡ በዚያ ፡ ሐኪም ፡ የለምን ፧ የወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ፈውስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልኾነም ፧

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ምዕራፍ ፡ 9 ፤

1 ፤ ተወግተው ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ስለሕዝቤ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሰዎች ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ አለቅስ ፡ ዘንድ ፡ ራሴ ፡ ውሃ ፥ ዐይኔም ፡ የእንባ ፡ ምንጭ ፡ በኾነልኝ!

2 ፤ ዅሉም ፡ አመንዝራዎች ፥ የአታላዮች ፡ ጉባኤ ፡ ናቸውና ፥ ሕዝቤን ፡ እተዋቸው ፡ ዘንድ ፡ ከነርሱም ፡ እለይ ፡ ዘንድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የመንገደኛዎች ፡ ማደሪያን ፡ ማን ፡ በሰጠኝ ፧

3 ፤ ምላሳቸውን ፡ ስለ ፡ ሐሰት ፡ እንደ ፡ ቀስት ፡ ገተሩ ፤ በምድር ፡ በረቱ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ለእውነት ፡ አይደለም ፤ ከክፋት ፡ ወደ ፡ ክፋት ፡ ይኼዳሉና ፡ እኔንም ፡ አላወቁምና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

4 ፤ ወንድምም ፡ ዅሉ ፡ ያሰናክላልና ፥ ባልንጀራም ፡ ዅሉ ፡ ያማልና ፥ እናንተ ፡ ዅሉ ፡ ከባልንጀራዎቻችኹ ፡ ተጠንቀቁ ፥ በወንድሞቻችኹም ፡ አትታመኑ ።



www.ethiopianorthodox.org

5 ፤ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ ባልንጀራውን ፡ ያታልላል ፣ በእውነትም ፡ አይናገርም ፤ ሐሰትን ፡ መናገርንም ፡ ምላሳቸው ፡
ተምሯል ፣ ክፉንም ፡ ለማድረግ ፡ ይደክማሉ ።

6 ፤ ማደሪያኽ ፡ በሽንገላ ፡ መካከል ፡ ነው ፣ ከሽንገላም ፡ የተነሣ ፡ እኔን ፡ ያውቁኝ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ብለዋል ፣ ይላል ፡
እግዚአብሔር ።

7 ፤ ስለዚህ ፣ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፣ አቀልጣቸዋለኹ ፡ እፈትናቸውማለኹ ፤ ስለሕዝቤ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡
ክፋት ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ የማደርገው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

8 ፤ ምላሳቸው ፡ የተሳለ ፡ ፍላጻ ፡ ነው ፤ ሽንገላን ፡ ይናገራሉ ፡ ሰው ፡ ከባልንጀራው ፡ ጋራ ፡ በሰላም ፡ ይናገራል ፣ በልቡ ፡
ግን ፡ ያደባበታል ።

9 ፤ በእውኑ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አልቀሥፍምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነፍሴስ ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡
አትበቀልምን ፧

10 ፤ ለተራራዎች ፡ ልቅሶን ፡ ለምድረ ፡ በዳ ፡ ማሰማሪያዎችም ፡ ዋይታን ፡ አነሣለኹ ፣ ሰው ፡ እንዳያልፍባቸው ፡ በእሳት ፡
ተቃጥለዋልና ። ሰዎችም ፡ የከብቱን ፡ ድምፅ ፡ አይሰሙም ፤ ከሰማይ ፡ ወፎች ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ድረስ ፡
ሸሽተው ፡ ኼደዋል ።

11 ፤ ኢየሩሳሌምንም ፡ የፍርስራሽ ፡ ክምር ፡ የቀበሮም ፡ ማደሪያ ፡ አደርጋታለኹ ፣ የይሁዳንም ፡ ከተማዎች ፡ ሰው ፡
የማይቀመጥባት ፡ ባድማ ፡ አደርጋቸዋለኹ ።

12 ፤ ይህን ፡ የሚያስተውል ፡ ጠቢብ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ፧ ያወራስ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ለማን ፡
ተናገረ ፧ ሰው ፡ እንዳያልፍባት ፡ ምድርስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ጠፋች ፣ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተቃጠለች ፧

13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ የሰጠኇቸውን ፡ ሕጌን ፡ ትተዋልና ፣ ቃሌንም ፡ አልሰሙምና ፣

14 ፤ ነገር ፡ ግን ፣ የልባቸውን ፡ ምኞትና ፡ አባቶቻቸው ፡ ያስተማሯቸውን ፡ በዓሊምን ፡ ተከትለዋልና ፣

15 ፤ ስለዚህ ፣ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፣ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ሬትን ፡ አበላዋለኹ ፡
የሐሞትንም ፡ ውሃ ፡ አጠጣዋለኹ ።

16 ፤ እነርሱና ፡ አባቶቻቸውም ፡ ባላወቋቸው ፡ አሕዛብ ፡ መካከል ፡ እበትናቸዋለኹ ፣ እስካጠፋቸውም ፡ ድረስ ፡
በስተኇላቸው ፡ ሰይፍን ፡ እሰድባቸዋለኹ ።

17 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንዲመጡ ፡ አልቃሾች ፡ ሴቶችን ፡ ጥሩ ፤ እንዲመጡም ፡ ወደ ፡ ብልኀተኛዎች ፡
ሴቶች ፡ ላኩ ፤

18 ፤ ዐይኖቻችንም ፡ እንባ ፡ እንዲያፈሱ ፡ የዐይናችንም ፡ ሽፋሽፍቶች ፡ ውሃን ፡ እንዲያፈልቁ ፡ ፈጥነው ፡ ለእኛ ፡
ልቅሶውን ፡ ይያዙ ።

19 ፤ በጽዮን ፦ እንዴት ፡ ተበዘበዝን! ምድርንም ፡ ትተናልና ፣ ቤቶቻችንንም ፡ አፍርሰዋልና ፣ እንዴት ፡ ዐፈርን! የሚል ፡
የልቅሶ ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቷል ።

20 ፤ እናንተ ፡ ሴቶች ፡ ሆይ ፣ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፣ ዦሯችኹም ፡ የአፉን ፡ ቃል ፡ ትቀበል ፣ ለሴቶች ፡
ልጆቻችኹም ፡ ልቅሶውን ፣ እያንዳንዳችኹም ፡ ለባልንጀራዎቻችኹ ፡ ዋይታውን ፡ አስተምሩ ።

21 ፤ ሕፃናቱን ፡ ከመንገድ ፡ ጐልማሳዎቹንም ፡ ከአደባባይ ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ሞት ፡ ወደ ፡ መስኮታችን ፡ ደርሷል ፡ ወደ ፡
አዳራሻችንም ፡ ውስጥ ፡ ገብቷል ።

22 ፤ የሰውም ፡ ሬሳ ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ በዕርሻ ፡ ላይ ፣ ማንምም ፡ እንደማይሰበስበው ፡ ከዐጫጆች ፡ በኇላ ፡ እንደሚቀር ፡
ቃርሚያ ፡ ይወድቃል ።

23 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጠቢብ ፡ በጥበቡ ፡ አይመካ ፣ ኀያልም ፡ በኀይሉ ፡ አይመካ ፣ ባለጠጋም ፡
በብልጥግናው ፡ አይመካ ፤

24 ፤ ነገር ፡ ግን ፣ የሚመካው ። ምሕረትንና ፡ ፍርድን ፡ ጽድቅንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የማደርግ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡



www.ethiopianorthodox.org

መኾኔን ፡ በማወቁና ፡ በማስተዋሉ ፡ በዚህ ፡ ይመካ ፤ ደስ ፡ የሚያሠኙኝ ፡ እነዚህ ፡ ናቸውና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

25-26 ፤ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ያልተገረዙ ፡ ናቸውና ፥ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ልባቸው ፡ ያልተገረዘ ፡
ነውና ፥ የተገረዙትን ፡ ኹሉ ፥ ግብጽንና ፡ ይሁዳን ፡ ኤዶምያስንም ፡ የዐሞንንም ፡ ልጆች ፡ ሞዐብንም ፡ በምድረ ፡ በዳም ፡
የተቀመጡትን ፡ ጠጕራቸውን ፡ በዙሪያ ፡ የተላጩትን ፡ ኹሉ ፥ ባለመገረዛቸው ፡ እነርሱን ፡ የምቀጣበት ፡
ዘመን ፥ እንሆ ፥ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ምዕራፍ ፡ 10 ፤

1 ፤ እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

2 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የአሕዛብን ፡ መንገድ ፡ አትማሩ ፡ ከሰማይ ፡ ምልክትም ፡ አትፍሩ ፤ አሕዛብ ፡
ይፈሩታልና ።

3 ፤ የአሕዛብ ፡ ልማድ ፡ ከንቱ ፡ ነውና ፤ ዛፍ ፡ ከዱር ፡ ይቈረጣል ፥ በሠራተኛም ፡ እጅ ፡ በመጥረቢያ ፡ ይሠራል ።

4 ፤ በብርና ፡ በወርቅ ፡ ያስጌጡታል ፥ እንዳይናወጥም ፡ በችንካርና ፡ በመዶሻ ፡ ይቸነክሩታል ።

5 ፤ እንደ ፡ ተቀረጸ ፡ ዐምድ ፡ ናቸው ፥ እነርሱም ፡ አይናገሩም ፤ መራመድም ፡ አይቻላቸውምና ፥ ይሸከሟቸዋል ። ክፉ ፡
መሥራትም ፡ አይቻላቸውምና ፥ ደግሞም ፡ መልካም ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ አይችሉምና ፡ አትፍሯቸው ።

6 ፤ አቤቱ ፥ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለ ፡ የለም ፤ አንተ ፡ ታላቅ ፡ ነኽ ፥ ስምኽም ፡ በኀይል ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

7 ፤ የአሕዛብ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ በአሕዛብ ፡ ጥበበኛዎች ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ በመንግሥታቸውም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡
ያለ ፡ ስለሌለ ፥ አንተን ፡ መፍራት ፡ ይገባልና ፥ አንተን ፡ የማይፈራ ፡ ማን ፡ ነው ፧

8 ፤ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሰንፈዋል ፥ ደንቍረውማል ፤ ጣዖታት ፡ የሚያስተምሩት ፡ የዕንጨት ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

9 ፤ የሠራተኛና ፡ የአንጥረኛ ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ የኾነ ፡ ከተርሴስ ፡ ጥፍጥፍ ፡ ብር ፡ ከአፌዝም ፡ ወርቅ ፡
ይመጣል ፤ ልብሳቸውም ፡ ሰማያዊና ፡ ቀይ ፡ ግምጃ ፡ ነው ፥ ኹሉም ፡ የብልኀተኛዎች ፡ ሥራ ፡ ናቸው ።

10 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ ሕያው ፡ አምላክና ፡ የዘለዓለም ፡ ንጉሥ ፡
ነው ፤ ከቍጣው ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ትንቀጠቀጣለች ፤ አሕዛብም ፡ መዓቱን ፡ አይችሉም ።

11 ፤ እናንተም ፦ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ያልፈጠሩ ፡ እነዚህ ፡ አማልክት ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ከሰማይም ፡ በታች ፡ ይጠፋሉ ፡
ትሏቸዋላችኹ ።

12 ፤ ምድርን ፡ በኀይሉ ፡ የፈጠረ ፥ ዓለሙን ፡ በጥበቡ ፡ የመሠረተ ፡ ሰማያትንም ፡ በማስተዋሉ ፡ የዘረጋ ፡ ርሱ ፡ ነው ።

13 ፤ ድምፁን ፡ ባሰማ ፡ ጊዜ ፡ ውሃዎች ፡ በሰማይ ፡ ይሰበሰባሉ ፥ ከምድርም ፡ ዳር ፡ ደመናትን ፡ ከፍ ፡
ያደርጋል ፤ ለዝናቡም ፡ መብረቅን ፡ ያደርጋል ፥ ነፋስንም ፡ ከቤተ ፡ መዛግብቱ ፡ ያወጣል ።

14 ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ዕውቀት ፡ ዐጥቶ ፡ ሰንፏል ፥ አንጥረኛም ፡ ኹሉ ፡ ከቀረጸው ፡ ምስል ፡ የተነሣ ፡ አፍሯል ፤ ቀልጦ ፡
የተሠራ ፡ ምስሉ ፡ ውሸት ፡ ነውና ፥ እስትንፋስም ፡ የላቸውምና ።

15 ፤ እነርሱ ፡ ምናምንቴና ፡ የቀልድ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ፤ በተጐበኙ ፡ ጊዜ ፡ ይጠፋሉ ።

16 ፤ የያዕቆብ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ እነዚህ ፡ አይደለም ፤ ርሱ ፡ የኹሉ ፡ ፈጣሪ ፡ ነውና ፤ እስራኤልም ፡ የርስቱ ፡
ነገድ ፡ ነውና ፤ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

17 ፤ በምሽግ ፡ ውስጥ ፡ የተቀመጥሽ ፡ ሆይ ፥ ዕቃሽን ፡ ከመሬት ፡ ሰብስቢ ፤

18 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ በምድሪቱ ፡ የሚኖሩትን ፡ እስኪሰማቸው ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡
እወነጭፋቸዋለኹ ፥ አስጨንቃቸውማለኹ ።

19 ፤ ስለ ፡ ስብራቴ ፡ ወዮልኝ! ቍስሌም ፡ ክፉ ፡ ነው ፥ እኔ ፡ ግን ፦ በእውነት ፡ የመከራ ፡ ቍስሌ ፡ ነው ፥ ርሱንም ፡
መሸከም ፡ ይገባኛል ፡ አልኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

20 ፤ ድንኳኔ ፡ ተበዘበዘ ፡ አውታሬም ፡ ኹሉ ፡ ተቈረጠ ፤ ልጆቼም ፡ ከእኔ ፡ ወጥተው ፡ አይገኙም ፤ ድንኳኔንም ፡
ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሚዘረጋ ፡ መጋረጃዎችንም ፡ የሚያነሣ ፡ የለም ።

21 ፤ እረኛዎች ፡ ሰንፈዋልና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አልጠየቁትምና ፡ አልተከናወነላቸውም ፥ መንጋዎቻቸውም ፡ ኹሉ ፡
ተበትነዋል ።

22 ፤ የወሬን ፡ ድምፅ ፡ ስሙ ፤ እንሆም ፥ የይሁዳን ፡ ከተማዎች ፡ ባድማና ፡ የቀበሮ ፡ ማደሪያ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡
ከሰሜን ፡ ምድር ፡ ጽኑ ፡ ሽብር ፡ መጥቷል ።

23 ፤ አቤቱ ፥ የሰው ፡ መንገድ ፡ ከራሱ ፡ እንዳይደለ ፡ ዐውቃለኹ ፥ አካኼዱንም ፡ ለማቅናት ፡ ከሚራመድ ፡ ሰው ፡
አይደለም ።

24 ፤ አቤቱ ፥ ቅጣኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንዳታዋርደኝ ፡ በመጠን ፡ ይኹን ፡ እንጂ ፡ በቍጣ ፡ አይኹን ።

25 ፤ ያዕቆብን ፡ በልተውታልና ፥ ውጠውትማልና ፥ አጥፍተውትማልና ፥ ማደሪያውንም ፡ አፍርሰዋልና ፥ በማያውቁኽ ፡
አሕዛብ ፡ ስምኽንም ፡ በማይጠሩ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ መዓትኽን ፡ አፍስ ።

___________________ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። _________________

ምዕራፍ ፡ 11 ፤

1 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

2 ፤ የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ ስማ ፥ ለይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ለሚኖሩ ፡ ተናገር ፥

3-4 ፤ እንደዚህም ፡ በላቸው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከግብጽ ፡ አገር ፡ ከብረት ፡
ምድጃ ፡ ባወጣኋቸው ፡ ቀን ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ ያዘዝኹትን ፡ የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ የማይሰማ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡
ይኹን ፤ አልኹም ፦ ቃሌን ፡ ስሙ ፥ ያዘዝኋችኹንም ፡ ኹሉ ፡ አድርጉ ፤ እንዲሁም ፡ እናንተ ፡ ሕዝብ ፡ ትኾኑኛላችኹ ፡
እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናችኋለኹ ።

5 ፤ ይህም ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ የምታፈስውን ፡ ምድር ፡ እሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻችኹ ፡
የማልኹትን ፡ መሐላ ፡ አጸና ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እኔም ፦ አቤቱ ፥ አሜን ፡ ብዬ ፡ መለስኹለት ።

6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ይህችን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡
ተናገር ፥ እንዲህም ፡ በል ፦ የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፡ አድርጉትም ።

7 ፤ አባቶቻችኹን ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ካወጣኹበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፥ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡
እያስጠነቀቅኹ ። ቃሌን ፡ ስሙ ፡ በማለት ፡ አስጠንቅቄያቸው ፡ ነበር ።

8 ፤ እነርሱ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ በክፉ ፡ ልባቸው ፡ እልከኝነት ፡ ኼዱ ፡ እንጂ ፥ አልሰሙም ፥ ዦሯቸውንም ፡
አላዘነበሉም ፤ ስለዚህ ፥ ያዘዝኋቸውን ፡ እነርሱም ፡ ያላደረጉትን ፡ የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡
አመጣኹባቸው ።

9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ በይሁዳ ፡ ሰዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሚኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ዐድማ ፡ ተገኝቷል ።

10 ፤ ቃሌንም ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ወዳሉ ፡ ወዳባቶቻቸው ፡ ኀጢአት ፡ ተመለሱ ፥ ያመልኳቸውም ፡ ዘንድ ፡
እንግዳዎችን ፡ አማልክት ፡ ተከተሉ ፤ የእስራኤል ፡ ቤትና ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ ከአባቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ያደረግኹትን ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ አፈረሱ ።

11 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ሊያመልጡት ፡ የማይችሉትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡
አመጣባቸዋለኹ ፥ ወደ ፡ እኔም ፡ ይጮኻሉ ፤ እኔም ፡ አልሰማቸውም ።

12 ፤ በይሁዳም ፡ ከተማዎችና ፡ በኢየሩሳሌ ፡ የሚኖሩ ፡ ኼደው ፡ ወደሚያጥኑላቸው ፡ አማልክት ፡ ይጮኻሉ ፤ ነገር ፡
ግን ፥ በመከራቸው ፡ ጊዜ ፡ ከቶ ፡ አያድኗቸውም ።

13 ፤ ይሁዳ ፡ ሆይ ፥ አማልክትኽ ፡ እንደ ፡ ከተማዎችኽ ፡ ቍጥር ፡ እንዲሁ ፡ ናቸው ፤ እንደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መንገዶች ፡
ቍጥር ፡ ለነውረኛ ፡ ነገር ፡ መሠዊያ ፥ ርሱም ፡ ለበዓል ፡ ታጥኑበት ፡ ዘንድ ፡ መሠዊያ ፥ አድርጋችኋል ።



www.ethiopianorthodox.org

14 ፤ አንተም ፡ ስለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አትጸልይ ፤ ከመከራቸው ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ በጮኹ ፡ ጊዜ ፡ አልሰማቸውምና ፡ ስለ ፡
እነርሱም ፡ ጩኸትና ፡ ልመና ፡ አታድርግ ።

15 ፤ ወዳጄ ፡ በቤቴ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ አላት ፧ ስእለት ፡ ወይም ፡ የተቀደሰ ፡ ሥጋ ፡ ክፋትሽን ፡ ከአንቺ ፡
ያስወግዳልን ፧ ወይስ ፡ በእነዚህ ፡ ታመልጫለሽን ፧

16 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስምሽን ፦ በመልካም ፡ ፍሬ ፡ የተዋበች ፡ የለመለመች ፡ የወይራ ፡ ዛፍ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ በጽኑ ፡
ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ጩኸት ፡ እሳትን ፡ አነደደባት ፥ ቅርንጫፎቿም ፡ ተሰብረዋል ።

17 ፤ ለበዓልም ፡ በማጠናቸው ፡ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፡ ለራሳቸው ፡ ስለሠሯት ፡ ስለእስራኤልና ፡ ስለይሁዳ ፡ ቤት ፡ ክፋት ፡
የተከለሽ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ተናግሮብሻል ።

18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አስታወቀኝ ፡ እኔም ፡ ዐወቅኹ ፤ ሥራቸውንም ፡ ገለጥኽልኝ ።

19 ፤ እኔም ፡ ለመታረድ ፡ እንደሚነዳ ፡ እንደ ፡ የዋህ ፡ በግ ፡ ጠቦት ፡ ኾንኹ ፤ እነርሱም ፦ ዛፉን ፡ ከፍሬው ፡ ጋራ ፡
እንቍረጥ ፥ ስሙም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዳይታሰብ ፡ ከሕያዋን ፡ ምድር ፡ እናጥፋው ፡ ብለው ፡ ምክርን ፡
እንዳሰቡብኝ ፡ አላወቅኹም ፡ ነበር ።

20 ፤ ኵላሊትንና ፡ ልብን ፡ የምትፈትን ፡ በቅንም ፡ የምትፈርድ ፡ አቤቱ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ክርክሬን ፡
ገልጬልኻለኹና ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ የሚኾን ፡ በቀልኽን ፡ ልይ ።

21 ፤ ስለዚህም ፦ በእጃችን ፡ እንዳትሞት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ትንቢት ፡ አትናገር ፡ ብለው ፡ ነፍስኽን ፡ ስለሚሹ ፡
ስለዐናቶት ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ እቀጣቸዋለኹ ፤

22 ፤ ጕበዛዝታቸው ፡ በሰይፍ ፡ ይሞታሉ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውም ፡ በራብ ፡ ይሞታሉ ፤ በምጐበኛቸውም ፡
ዓመት ፡ በዐናቶት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አመጣባቸዋለኹና ፡ ማንም ፡ ከነርሱ ፡ የሚቀር ፡ የለም ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ምዕራፍ ፡ 12 ፤

1 ፤ አቤቱ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በተሟገትኹ ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ ጻድቅ ፡ ነኽ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡
ልናገር ። የኀጢአተኞች ፡ መንገድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይቃናል ፧ በደልንስ ፡ ለሚያደርጉ ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ደኅንነት ፡
ይኾናል ፧

2 ፤ ተክለኻቸዋል ፤ ሥር ፡ ሰደዋል ፤ አድገዋል ፡ አፍርተውማል ፤ በአፋቸው ፡ አንተ ፡ ቅርብ ፡ ነኽ ፥ ከልባቸው ፡ ግን ፡
ሩቅ ፡ ነኽ ።

3 ፤ አንተ ፡ ግን ፥ አቤቱ ፥ ዐውቀኸኛል ፤ አይተኸኛል ፥ ልቤንም ፡ በፊትኽ ፡ ፈትነኻል ፤ እንደ ፡ በጎች ፡ ለመታረድ ፡
ጕትተኽ ፡ ለያቸው ፥ ለመታረድም ፡ ቀን ፡ አዘጋጃቸው ።

4 ፤ ምድሪቱ ፡ የምታለቅሰው ፥ የአገሩ ፡ ሣርስ ፡ ኹሉ ፡ የሚደርቀው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧ የተቀመጡባት ፡
ሰዎች ፦ ፍጻሜያችንን ፡ አያይም ፡ ብለዋልና ፥ ስለ ፡ ክፋታቸው ፡ እንስሳዎችና ፡ ወፎች ፡ ጠፍተዋል ።

5 ፤ ከእግረኞች ፡ ጋራ ፡ በሮጥኽ ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ቢያደክሙኽ ፥ ከፈረሶች ፡ ጋራ ፡ መታገል ፡ እንዴት ፡
ትችላለኽ ፧ በሰላምም ፡ ምድር ፡ ታምነኽ ፡ ብትቀመጥ ፥ በዮርዳኖስ ፡ ትዕቢት ፡ እንዴት ፡ ታደርጋለኽ ፧

6 ፤ ወንድሞችኽና ፡ የአባትኽ ፡ ቤት ፡ እነርሱ ፡ ጭምር ፡ አታለውኻልና ፥ በኋላኽም ፡ ጮኸዋልና ፤ በመልካምም ፡
ቢናገሩኽም ፡ አትታመናቸው ።

7 ፤ ቤቴን ፡ ትቻለኹ ፡ ርስቴንም ፡ ጥያለኹ ፥ ነፍሴም ፡ የምትወዳትን ፡ በጠላቶቿ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቻለኹ ።

8 ፤ ርስቴ ፡ በዱር ፡ እንዳለ ፡ አንበሳ ፡ ኾናብኛለች ፤ ድምፇን ፡ አንሥታብኛለች ፤ ስለዚህ ፥ ጠልቻታለኹ ።

9 ፤ ርስቴ ፡ እንደ ፡ ዝንጕርጕር ፡ አሞራ ፡ ኾነችብኝን ፧ አሞሮችስ ፡ በዙሪያዋና ፡ በላይዋ ፡ ኾነዋልን ፧ ኺዱ ፥ የምድር ፡
አራዊትን ፡ ኹሉ ፡ ሰብስቡ ፥ ይበሉም ፡ ዘንድ ፡ አምጧቸው ።

10 ፤ ብዙ ፡ እረኞች ፡ የወይኔን ፡ ቦታዬን ፡ አጥፍተዋል ፥ ዕድል ፡ ፈንታዬንም ፡ ረግጠዋል ፤ የአምሮቴን ፡ ዕድል ፡



www.ethiopianorthodox.org

ፈንታ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አድርገውታል ።

11 ፤ ባድማ ፡ አድርገውታል ፥ ፈርሶም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ያለቅሳል ፤ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ባድማ ፡ ኾናለች ፡ በልቡም ፡ የሚያስባት ፡ የለም ።

12 ፤ በወናዎች ፡ ኰረብታዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በዝባዦች ፡ መጥተዋል ፥ የእግዚአብሔር ፡ ሰይፍ ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ ዠምሮ ፡ እስከምድር ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ይበላልና ፤ ለሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ሰላም ፡ የለም ።

13 ፤ ስንዴን ፡ ዘሩ ፡ ሾኽንም ፡ ዐጨዱ ፤ ደከሙ ፥ ምንም ፡ አልረባቸውም ፤ ስለእግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ከፍሬያችኹ ፡ ታፍራላችኹ ።

14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቤ ፡ ለእስራኤል ፡ ያወረስኹትን ፡ ርስት ፡ ለሚነኩት ፡ ክፉዎች ፡ ጎረቤቶች ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ ከምድራቸው ፡ እነቅላቸዋለኹ ፥ የይሁዳንም ፡ ቤት ፡ ከመካከላቸው ፡ እነቅለዋለኹ ።

15 ፤ ከነቀልኋቸውም ፡ በኋላ ፡ መልሼ ፡ እምራቸዋለኹ ፥ እያንዳንዱንም ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡ እያንዳንዱንም ፡ ወደ ፡ ምድሩ ፡ እመልሳለኹ ።

16 ፤ በበዓል ፡ ይምሉ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቤን ፡ እንዳስተማሩ ፡ በስሜ ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ብለው ፡ ይምሉ ፡ ዘንድ ፡ የሕዝቤን ፡ መንገድ ፡ በትጋት ፡ ቢማሩ ፥ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሕዝቤ ፡ መካከል ፡ ይመሠረታሉ ።

17 ፤ ባይሰሙኝ ፡ ግን ፡ ያንን ፡ ሕዝብ ፡ ፈጽሜ ፡ እነቅለዋለኹ ፡ አጠፋውማለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ምዕራፍ ፡ 13 ፤

1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይለኛል ፦ ኺድ ፥ ከተልባ ፡ እግር ፡ የተሠራችን ፡ መታጠቂያ ፡ ለአንተ ፡ ግዛ ፥ ወገብኽንም ፡ ታጠቅባት ፤ በውሃውም ፡ ውስጥ ፡ አትንከራት ።

2 ፤ እንደእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ መታጠቂያን ፡ ገዛኹ ፡ ወገቤንም ፡ ታጠቅኹባት ።

3-4 ፤ ኹለተኛም ፡ ጊዜ ፦ የገዛኻትን ፡ በወገብኽ ፡ ያለችውን ፡ መታጠቂያ ፡ ወስደኽ ፡ ተነሥ ፥ ወደ ፡ ኤፍራጥስም ፡ ኺድ ፥ በዚያም ፡ በተሰነጠቀ ፡ አለት ፡ ውስጥ ፡ ሸሽጋት ፡ የሚል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መጣልኝ ።

5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዳዘዘኝ ፡ ኼድኹ ፡ በኤፍራጥስም ፡ አጠገብ ፡ ሸሸግኋት ።

6 ፤ ከብዙ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፦ ተነሥተኽ ፡ ወደ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ኺድ ፥ በዚያም ፡ ትሸሽጋት ፡ ዘንድ ፡ ያዘዝኹኽን ፡ መታጠቂያ ፡ ከዚያ ፡ ውስጥ ፡ ውሰድ ፡ አለኝ ።

7 ፤ እኔም ፡ ወደ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ኼድኹ ፡ ቈፈርኹም ፥ ከሸሸግኹበትም ፡ ስፍራ ፡ መታጠቂያዪቱን ፡ ወሰድኹ ። እንሆም ፥ መታጠቂያዪቱ ፡ ተበላሽታ ፡ ነበር ፥ ለምንም ፡ አልረባችም ።

8 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፤

9 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንዲሁ ፡ የይሁዳን ፡ ትዕቢት ፡ ታላቁንም ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ትዕቢት ፡ አበላሻለኹ ።

10 ፤ ቃሌን ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ የሚሉ ፥ በልባቸውም ፡ እልከኝነት ፡ የሚኼዱ ፥ ያመልኳቸውና ፡ ይሰግዱላቸው ፡ ዘንድ ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ የሚከተሉ ፡ እነዚህ ፡ ክፉ ፡ ሕዝብ ፡ አንዳች ፡ እንዳማትረባ ፡ እንደዚች ፡ መታጠቂያ ፡ ይኾናሉ ።

11 ፤ መታጠቂያ ፡ በሰው ፡ ወገብ ፡ ላይ ፡ እንደምትጣበቅ ፥ እንዲሁ ፡ ሕዝብና ፡ ስም ፡ ምስጋናና ፡ ክብር ፡ ይኾኑልኝ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ የይሁዳንም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አጣብቄያለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አልሰሙም ።

12 ፤ ስለዚህ ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ማድጋ ፡ ኹሉ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይሞላል ፡ ብለኽ ፡ ትነግራቸዋለኽ ፤ እነርሱም ፦ ማድጋ ፡ ኹሉ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንዲሞላ ፡ በእውኑ ፡ እኛ ፡ አናውቅምን ፧ ይሉኻል ።



www.ethiopianorthodox.org

13 ፤ አንተም ፡ እንዲህ ፡ ትላቸዋለኽ ፡— እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እንሆ ፥ በዚች ፡ ምድር ፡ የሚኖሩትን ፡
ኹሉ ፥ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ የሚቀመጡትን ፡ ነገሥታት ፡ ካህናቱንም ፡ ነቢያቱንም ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የተቀመጡትን ፡ ኹሉ ፡
በስካር ፡ እሞላቸዋለኹ ።

14 ፤ ሰውንም ፡ በሰው ፡ ላይ ፥ አባቶችንና ፡ ልጆችን ፡ ባንድ ፡ ላይ ፥ እቀጠቅጣለኹ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ፤ አጠፋቸዋለኹ ፡ እንጂ ፡ አልራራም ፥ አላዝንም ፥ አልምርም ።

15 ፤ ስሙ ፥ አድምጡ ፤ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ፥ አትታበዩ ።

16 ፤ ሳትጨልም ፡ እግራችኹም ፡ በጨለመችው ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ሳትሰናከል ፥ በተስፋ ፡ የምትጠባበቁትን ፡ ብርሃን ፡
ለሞት ፡ ጥላና ፡ ለድቅድቅ ፡ ጨለማ ፡ ሳይለውጠው ፡ ለአምላካችኹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብርን ፡ ስጡ ።

17 ፤ ይህን ፡ ባትሰሙ ፡ ነፍሴ ፡ ስለ ፡ ትዕቢታችኹ ፡ በስውር ፡ ታለቅሳለች ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንጋ ፡
ተማርኳልና ፥ ዐይኔ ፡ ታነባለች ፥ እንባንም ፡ ታፈሳለች ።

18 ፤ ለንጉሡና ፡ ለንጉሥ ፡ እናት ፡ ለእቴጌዪቱ ፡— የክብራችኹ ፡ አክሊል ፡ ከራሳችኹ ፡ ወርዷልና ፥ ተዋርዳችኹ ፡
ተቀመጡ ፡ በል ።

19 ፤ የደቡብ ፡ ከተማዎች ፡ ተዘግተዋል ፥ የሚከፍታቸውም ፡ የለም ፤ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ ተማርኳል ፥ ፈጽሞ ፡ ተማርኳል ።

20 ፤ ዐይናችኹን ፡ አንሥታችኹ ፡ እነዚህን ፡ ከሰሜን ፡ የሚመጡትን ፡ ተመልከቱ ፤ ለአንቺ ፡ የተሰጠ ፡ መንጋ ፥ የተዋበ ፡
መንጋሽ ፥ ወዴት ፡ አለ ፧

21 ፤ ወዳጆችሽ ፡ እንዲኾኑ ፡ ያስተማርሻቸውን ፡ በራስሽ ፡ ላይ ፡ አለቃዎች ፡ ባደረጋቸው ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ትያለሽ ፧ እንደ ፡
ወላድ ፡ ሴት ፡ ምጥ ፡ አይዝሽምን ፧

22 ፤ በልብሽም ፡— እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ደረሰብኝ ፧ ብትዪ ፥ ከኀጢአትሽ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ የልብስሽ ፡
ዘርፍ ፡ ተገልጧል ፡ ተረከዝሽም ፡ ተገፏል ።

23 ፤ በእውኑ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መልኩን ፡ ወይስ ፡ ነብር ፡ ዝንጕርጕርነትን ፡ ይለውጥ ፡ ዘንድ ፡ ይችላልን ፧ በዚያን ፡ ጊዜ ፡
ክፋትን ፡ የለመዳችኹ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በጎ ፡ ለማድረግ ፡ ትችላላችኹ ።

24 ፤ ስለዚህ ፥ እንደሚያልፍ ፡ እብቅ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ነፋስ ፡ እበትናቸዋለኹ ።

25 ፤ ረስተሽኛልና ፥ በሐሰትም ፡ ታምነሻልና ፥ ዕጣሽ ፡ የለካኹልሽም ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ።

26 ፤ ስለዚህም ፡ የልብስሽን ፡ ዘርፍ ፡ በፊትሽ ፡ እገልጣለኹ ፡ ዕፍረትሽም ፡ ይታያል ።

27 ፤ አስጸያፊ ፡ ሥራሽን ፥ ምንዝርናሽን ፥ ማሽካካትሽን ፥ የግልሙትናሽንም ፡ መዳራት ፡ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡
በሜዳም ፡ አይቻለኹ ። ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ወዮልሽ! ለመንጻት ፡ እንቢ ፡ ብለሻል ፤ ይህስ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧

---ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ። ---

ምዕራፍ ፡ 14 ፤

1 ፤ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ ስለ ፡ ድርቅ ፡ የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፡—

2 ፤ ይሁዳ ፡ አለቀሰች ፥ ደጆቿም ፡ ባዶ ፡ ኾኑ ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ ጨለሙ ፤ የኢየሩሳሌም ፡ ጩኸት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡
ብሏል ።

3 ፤ ታላላቆችም ፡ ብላቴናዎቻቸውን ፡ ወደ ፡ ውሃ ፡ ሰደዱ ፤ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ መጡ ፡ ውሃም ፡ አላገኙም ፥ ዕቃቸውንም ፡
ባዶውን ፡ ይዘው ፡ ተመለሱ ፤ ዐፈሩም ፡ ተዋረዱም ፡ ራሳቸውንም ፡ ተከናነቡ ።

4 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ አልዘነበምና ፡ መሬቱ ፡ ስንጥቅጥቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ዐራሾች ፡ ዐፈሩ ፥ ራሳቸውንም ፡ ተከናነቡ ።

5 ፤ ዋላ ፡ ደግሞ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ወለደች ፥ ሣርም ፡ የለምና ፡ ግልገሏን ፡ ተወች ።

6 ፤ የሜዳ ፡ አህያዎችም ፡ በወና ፡ ኰረብታ ፡ ላይ ፡ ቆመዋል ፥ እንደ ፡ ቀበሮም ፡ ወደ ፡ ነፋስ ፡ አለከለኩ ፤ ልምላሜም ፡



www.ethiopianorthodox.org

የለምና ፡ ዐይኖቻቸው ፡ ጠወለጉ ።

7 ፤ አቤቱ ፥ ኀጢአታችን ፡ ብዙ ፡ ነውና ፥ ባንተም ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርተናልና ፥ ኀጢአታችን ፡
ይመሰክርብናል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ስለ ፡ ስምኽ ፡ ብለኽ ፡ አድርግ ።

8 ፤ አንተ ፡ የእስራኤል ፡ ተስፋ ፡ ሆይ ፡ በመከራም ፡ ጊዜ ፡ የምታድነው ፥ በምድር ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፥ ወደ ፡ ማደሪያ ፡
ዘወር ፡ እንደሚል ፡ መንገደኛ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትኾናለኽ ፧

9 ፤ እንዳንቀላፋ ፡ ሰው ፡ ሰው ፥ ያድንም ፡ ዘንድ ፡ እንደማይችል ፡ ኀያል ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትኾናለኽ ፧ አንተ ፡
ግን ፥ አቤቱ ፥ በመካከላችን ፡ ነኽ ፡ እኛም ፡ በስምኽ ፡ ተጠርተናል ፤ አትተወን ።

10 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ መቅበዝበዝን ፡ ወደዋል ፥ እግራቸውንም ፡
አልከለከሉም ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ በእነርሱ ፡ ደስ ፡ አይለውም ፥ በደላቸውንም ፡ አኹን ፡
ያስባል ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ይቀጣል ።

11 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ መልካም ፡ አትጸልይላቸው ።

12 ፤ በጾሙ ፡ ጊዜ ፡ ጸሎታቸውን ፡ አልሰማም ፤ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ ባቀረቡ ፡ ጊዜ ፡
አልቀበላቸውም ፤ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ አጠፋቸዋለኹ ፡ አለኝ ።

13 ፤ እኔም ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ወዮ! እንሆ ፥ ነቢያት ። በእውነት ፡ ሰላምን ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ እሰጣችኋለኹ ፡
እንጂ ፡ ሰይፍን ፡ አታዩም ፥ ራብም ፡ አያገኛችኹም ፡ ይሏቸዋል ፡ አልኹ ።

14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ነቢያቱ ፡ ውሸት ፡ በስሜ ፡ ትንቢት ፡
ይናገራሉ ፤ አላክኋቸውም ፥ አላዘዝኋቸውም ፥ አልተናገርኋቸውም ፤ የውሸቱን ፡ ራእይ ፡ ሟርትንም ፡ ከንቱንም ፡ ነገር ፡
የልባቸውንም ፡ ሽንገላ ፡ ይሰብኩላችኋል ።

15 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ በስሜ ፡ ትንቢት ፡ ስለሚናገሩ ፡ ነቢያት ፦ በዚች ፡ አገር ፡ ሰይፍና ፡ ራብ ፡ አይኾንም ፡
ስለሚሉ ፡ ስላላክኋቸው ፡ ነቢያት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነዚያ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ ይጠፋሉ ።

16 ፤ ትንቢት ፡ የሚናገሩላቸውም ፡ ሰዎች ፡ ከራብና ፡ ከሰይፍ ፡ የተነሣ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡
ይበተናሉ ፤ ክፋታቸውንም ፡ አፈስባቸዋለኹ ፡ እነርሱንና ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውንም ፡
የሚቀብራቸው ፡ አይገኝም ።

17 ፤ እንደዚህም ፡ ብለኽ ፡ ትነግራቸዋለኽ ፦ የወገኔ ፡ ልጅ ፡ ድንግሊቱ ፡ በታላቅ ፡ ስብራትና ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ በኾነ ፡
ቍስል ፡ ተሰብራለችና ፡ ዐይኖቼ ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ ሳያቋርጡ ፡ እንባ ፡ ያፈሳሉ ።

18 ፤ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ብወጣ ፥ እንሆ ፥ በሰይፍ ፡ የሞቱ ፡ አሉ ፤ ወደ ፡ ከተማም ፡ ብገባ ፥ እንሆ ፥ በራብ ፡ የከሱ ፡
አሉ ፤ ነቢዩና ፡ ካህኑም ፡ ወደማያውቋት ፡ አገር ፡ ኼደዋልና ።

19 ፤ በእውኑ ፡ ይሁዳን ፡ ፈጽመኽ ፡ ጥለኽዋልን ፧ ነፍስኽስ ፡ ጽዮንን ፡ ጠልታታለችን ፧ ስለ ፡ ምን ፡ መታኸን ፧ ፈውስስ ፡
ስለ ፡ ምን ፡ የለንም ፧ ሰላምን ፡ በተስፋ ፡ ተጠባበቅን ፥ መልካምም ፡ አልተገኘም ፤ ፈውስን ፡ በተስፋ ፡
ተጠባበቅን ፥ እንሆም ፥ ድንጋጤ ፡ ኾነ ።

20 ፤ አቤቱ ፥ ባንተ ፡ ላይ ፡ ኀጢአትን ፡ ሠርተናልና ፥ ክፋታችንንና ፡ የአባቶቻችንን ፡ በደል ፡ እናውቃለን ።

21 ፤ ስለ ፡ ስምኽ ፡ ብለኽ ፡ አትናቀን ፥ የክብርኽንም ፡ ዙፋን ፡ አታስነውር ፤ ከእኛ ፡ ጋራም ፡ ያደረግኸውን ፡ ቃል ፡
ኪዳንኽን ፡ ዐስብ ፡ እንጂ ፡ አታፍርስ ።

22 ፤ በእውኑ ፡ በአሕዛብ ፡ ጣዖታት ፡ መካከል ፡ ያዘንብ ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ ይገኛልን ፧ ወይስ ፡ ሰማይ ፡ ዝናብ ፡
ማፍሰስ ፡ ይችላልን ፧ አቤቱ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧ አንተ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡
አድርገኻልና ፥ ስለዚህ ፡ አንተን ፡ በተስፋ ፡ እንጠባበቃለን ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ምዕራፍ ፡ 15 ፤



www.ethiopianorthodox.org

1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደዚህ ፡ አለኝ ፦ ሙሴና ፡ ሳሙኤል ፡ በፊቴ ፡ ቢቆሙም ፥ ልቤ ፡ ወደዚህ ፡ ሕዝብ ፡
አይዘነብልም ፤ ከፊቴ ፡ ጣላቸው ፤ ይውጡ ።

2 ፤ እነርሱም ፦ ወዴት ፡ እንውጣ ፡ ቢሉኽ ፥ አንተ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለሞት ፡ የኾነ ፡ ወደ ፡
ሞት ፥ ለሰይፍም ፡ የኾነ ፡ ወደ ፡ ሰይፍ ፥ ለራብም ፡ የኾነ ፡ ወደ ፡ ራብ ፥ ለምርኮም ፡ የኾነ ፡ ወደ ፡ ምርኮ ፡ ትላቸዋለኽ ።

3 ፤ ሰይፍን ፡ ለመግደል ፡ ውሻዎችንም ፡ ለመጐተት ፡ የሰማያትንም ፡ ወፎች ፡ የምድርንም ፡ አራዊት ፡ ለመብላትና ፡
ለማጥፋት ፥ አራቱን ፡ ዐይነት ፡ ጥፋት ፡ አዝባቸዋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

4 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ የሕዝቅያስ ፡ ልጅ ፡ ምናሴ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ስላደረገው ፡ ኹሉ ፡ በምድር ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡
መካከል ፡ ለመከራ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹ ።

5 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ የሚራራልሽ ፡ ማን ፡ ነው ፧ የሚያዝንልሽስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ወይስ ፡ ስለ ፡ ደኅንነትሽ ፡ ይጠይቅ ፡
ዘንድ ፡ ፈቀቅ ፡ የሚል ፡ ማን ፡ ነው ፧

6 ፤ አንቺ ፡ እኔን ፡ ጥለሻል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ወደ ፡ ኋላሽም ፡ ተመልሰሻል ፤ ስለዚህ ፥ እጄን ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡
ዘርግቼ ፡ አጥፍቼሻለኹ ፤ ከይቅርታ ፡ ደክሜያለኹ ።

7 ፤ በአገርም ፡ ደጆች ፡ ውስጥ ፡ በመንሽ ፡ አበጥሬያቸዋለኹ ፤ የወላድ ፡ መካን ፡ አድርጌያቸዋለኹ ፥ ሕዝቤንም ፡
አጥፍቻለኹ ፤ ከመንገዳቸውም ፡ አልተመለሱም ።

8 ፤ መበለቶቻቸውም ፡ ከባሕር ፡ አሸዋ ፡ ይልቅ ፡ በዝተውብኛል ፤ በብላቴናዎች ፡ እናት ፡ ላይ ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡
አጥፊውን ፡ አምጥቻለኹ ፤ ጣርንና ፡ ድንጋጤን ፡ በድንገት ፡ አምጥቼባታለኹ ።

9 ፤ ሰባት ፡ የወለደች ፡ ደክማለች ፥ ነፍሷንም ፡ አውጥታለች ፤ ቀን ፡ ገና ፡ ሳለ ፡ ፀሐይዋ ፡ ገብታባታለች ፤ ዐፍራለች ፡
ተዋርዳማለች ፤ የተረፉትንም ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ ለሰይፍ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ።

10 ፤ እናቴ ፡ ሆይ ፥ ወዮልኝ! ለምድር ፡ ኹሉ ፡ የክርክርና ፡ የጥል ፡ ሰው ፡ የኾንኹትን ፡ ወለድሽኝ ፡ ለማንም ፡
አላበደርኹም ፥ ማንም ፡ ለእኔ ፡ አላበደረም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ኹሉ ፡ ይረግመኛል ።

11 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ በእውነት ፡ ለደኅንነትኽ ፡ አጸናኻለኹ ፤ በእውነት ፡ በመከራና ፡ በጭንቅ ፡ ጊዜ ፡
ጠላትኽ ፡ እንዲለምንኽ ፡ አደርገዋለኹ ።

12 ፤ በእውኑ ፡ ብረትን ፥ የሰሜንን ፡ ብረት ፥ ናስንም ፡ የሚሰብር ፡ አለን ፧

13 ፤ በዳርቻኽ ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ አለ ፡ ኀጢአትኽ ፡ ኹሉ ፡ ባለጠግነትኽንና ፡ መዝገብኽን ፡ ለመበዝበዝ ፡ በከንቱ ፡
እሰጣለኹ ።

14 ፤ የምታቃጥላችኹ ፡ እሳት ፡ ከቍጣዬ ፡ ትነዳለችና ፡ ከጠላቶችኽ ፡ ጋራ ፡ ወደማታውቀው ፡ ምድር ፡ አሳልፍኻለኹ ።

15 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ታውቃለኽ ፤ ዐስበኝ ፡ ጐብኘኝም ፡ የሚያሳድዱኝንም ፡ ተበቀላቸው ፡ እንጂ ፡ አትታገሣቸው ፤ ስለ ፡
አንተ ፡ ስድብን ፡ እንደ ፡ ታገሥኹ ፡ ዕወቅ ።

16 ፤ ቃልኽ ፡ ተገኝቷል ፡ እኔም ፡ በልቼዋለኹ ፤ አቤቱ ፥ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ በስምኽ ፡ ተጠርቻለኹና ፡ ቃልኽ ፡
ሐሤትና ፡ የልብ ፡ ደስታ ፡ ኾነኝ ።

17 ፤ በዋዘኛዎችና ፡ በደስተኛዎች ፡ ጉባኤ ፡ አልተቀመጥኹም ፤ ቍጣን ፡ ሞልተኽብኛልና ፥ በእጅኽ ፡ ፊት ፡ ለብቻዬ ፡
ተቀመጥኹ ።

18 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ሕመሜ ፡ አዘወተረኝ ፧ ቍስሌስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ የማይፈወስ ፡ ኾነ ፧ ስለ ፡ ምንስ ፦ አልሽርም ፡
አለ ፧ በእውኑ ፡ እንደ ፡ ሐሰተኛ ፡ ምንጭ ፥ እንዳልታመነች ፡ ውሃ ፡ ትኾነኛለኽን ፧

19 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ብትመለስ ፡ እመልስኻለኹ ፡ በፊቴም ፡ ትቆማለኽ ፤ የከበረውንም ፡
ከተዋረደው ፡ ብትለይ ፡ እንደ ፡ አፌ ፡ ትኾናለኽ ፤ እነርሱ ፡ ወዳንተ ፡ ይመለሳሉ ፥ አንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡
አትመለስም ።

20 ፤ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ የተመሸገ ፡ የናስ ፡ ቅጥር ፡ አደርግኻለኹ ፤ ይዋጉኻል ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ለማዳን ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ነኝና ፡ አያሸንፉኽም ።

21 ፤ ከክፉ ፡ ሰዎችም ፡ እጅ ፡ እታደግኻለኹ ፥ ከጨካኞችም ፡ ጡጫ ፡ እቤዥኻለኹ ።

______________________ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ። ______________________

ምዕራፍ ፡ 16 ፤

1 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

2 ፤ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ሚስት ፡ አታግባ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችም ፡ አይኹኑልኽ ።

3 ፤ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ስለተወለዱ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፥ ስለወለዷቸውም ፡ ስለ ፡
እናቶቻቸው ፥ በዚችም ፡ ምድር ፡ ስለወለዷቸው ፡ ስለ ፡ አባቶቻቸው ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦

4 ፤ በክፉ ፡ ሞት ፡ ይሞታሉ ፤ አይለቀስላቸውም ፡ አይቀበሩምም ፥ በመሬትም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡
ይኾናሉ ፤ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ ይጠፋሉ ፥ ሬሳቸውም ፡ ለሰማይ ፡ ወፎችና ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ መብል ፡ ይኾናሉ ።

5 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰላሜን ፥ ቸርነትና ፡ ምሕረትን ፥ ከዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አስወግጃለኹና ፡ ልቅሶ ፡
ወዳለበት ፡ ቤት ፡ አትግባ ፥ ታለቅስም ፥ ታዝንም ፡ ዘንድ ፡ አትኺድ ።

6 ፤ ታላላቆችና ፡ ታናናሾች ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ ይሞታሉ ፤ አይቀበሩም ፥ ሰዎችም ፡ አያለቅሱላቸውም ፥ ስለ ፡ እነርሱም ፡
ገላን ፡ አይነጩላቸውም ፥ ራስንም ፡ አይላጩላቸውም ፤

7 ፤ ሰዎችም ፡ ስለሞቱት ፡ ለማጽናናት ፡ የዕዝን ፡ እንጀራ ፡ አይቈርሱላቸውም ፥ ስለ ፡ አባታቸውና ፡ ስለ ፡ እናታቸውም ፡
የመጽናናት ፡ ጽዋ ፡ አያጠጧቸውም ።

8 ፤ ትበላና ፡ ትጠጣ ፡ ዘንድ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ለመቀመጥ ፡ ወደግብዣ ፡ ቤት ፡ አትግባ ።

9 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ በዐይናችኹ ፡ ፊት ፡
በዘመናችኹም ፡ የእልልታን ፡ ድምፅና ፡ የደስታን ፡ ድምፅ ፡ የወንድ ፡ ሙሽራን ፡ ድምፅና ፡ የሴት ፡ ሙሽራን ፡ ድምፅ ፡
ከዚህ ፡ ስፍራ ፡ አስቀራለኹ ።

10 ፤ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ዅሉ ፡ በተናገርኽ ፡ ጊዜ ፦ ይህን ፡ ዅሉ ፡ ታላቅ ፡ የኾነ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ስለ ፡ ምን ፡
እግዚአብሔር ፡ ተናገረብን ፧ በደላችንስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በአምላካችንስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የሠራነው ፡
ኀጢአታችን ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ቢሉኽ ፥

11 ፤ አንተ ፡ እንዲህ ፡ ትላቸዋለኽ ፦ አባቶቻችኹ ፡ እኔን ፡ ስለ ፡ ተዉ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ሌላዎችንም ፡
አማልክት ፡ ተከተሉ ፡ አመለኳቸውም ፡ ሰገዱላቸውም ፥ እነርሱም ፡ ትተውኛል ፥ ሕጌንም ፡ አልጠበቁም ፤ እናንተም ፡
ከአባቶቻችኹ ፡ ይልቅ ፡ ክፉ ፡ አድርጋችኋል ፤ እንሆም ፥ ዅላችኹ ፡ እንደ ፡ ክፉ ፡ ልባችኹ ፡ እልከኝነት ፡ ኼዳችኋል ፡
እኔንም ፡ አልሰማችኹም ።

13 ፤ ስለዚህ ፥ ከዚች ፡ ምድር ፡ እናንተና ፡ አባቶቻችኹ ፡ ወዳላወቃችኋት ፡ ምድር ፡ እጥላችኋለኹ ፤ ምሕረትንም ፡
አላደርግላችኹምና ፥ በዚያ ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ታመልካላችኹ ።

14 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ዳግመኛ ፡
የማይባልበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤

15 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከሰሜን ፡ ምድር ፡ ካሳደዳቸውም ፡ ምድር ፡ ዅሉ ፡ ያወጣ ፡ ሕያው ፡
እግዚአብሔርን! ይባላል ፤ እኔም ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ወደሰጠኋት ፡ ወደ ፡ ምድራቸው ፡ እመልሳቸዋለኹ ።

16 ፤ እንሆ ፥ ብዙ ፡ ዓሣ ፡ አጥማጆችን ፡ እሰዳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ እነርሱም ፡ ያጠምዷቸዋል ፤ ከዚያም ፡
በኋላ ፡ ብዙ ፡ አዳኞችን ፡ እሰዳለኹ ፥ እነርሱም ፡ ከየተራራውና ፡ ከየኰረብታው ፡ ዅሉ ፡ ከየድንጋዩም ፡ ስንጣቂ ፡ ውስጥ ፡
ያድኗቸዋል ።

17 ፤ ዐይኔ ፡ በመንገዳቸው ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ ከፊቴም ፡ አልተሰወሩም ፥ ኀጢአታቸውም ፡ ከዐይኔ ፡ አልተሸሸገም ።

18 ፤ ምድሬንም ፡ በተጠሉ ፡ በጣዖቶቻቸው ፡ ሬሳዎች ፡ አርክሰዋልና ፥ ርስቴንም ፡ አስጸያፊ ፡ በኾኑ ፡ ነገሮች ፡



www.ethiopianorthodox.org

ሞልተዋልና ፥ አስቀድሜ ፡ የበደላቸውንና ፡ የኀጢአታቸውን ፡ ዕዳ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ እከፍላቸዋለኹ ።

19 ፤ አቤቱ ፥ ኀይሌ ፥ ዐምባዬ ፥ በመከራም ፡ ቀን ፡ መጠጊያዬ ፡ ሆይ ፥ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ አሕዛብ ፡ ወዳንተ ፡
መጥተው ፦ በእውነት ፡ አባቶቻችን ፡ ውሸትንና ፡ ከንቱን ፡ ነገር ፡ የማይረባቸውንም ፡ ወርሰዋል ፡ ይላሉ ።

20 ፤ በእውኑ ፡ ሰው ፡ አማልክት ፡ ያልኾኑትን ፡ ለራሱ ፡ አማልክትን ፡ አድርጎ ፡ ይሠራልን ፧

21 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ አስታውቃቸዋለኹ ፥ በዚች ፡ ጊዜ ፡ እጄንና ፡ ኀይሌን ፡ አስታውቃቸዋለኹ ፤ እነርሱም ፡ ስሜ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያውቃሉ ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ።

ምዕራፍ ፡ 17 ፤

1 ፤ የይሁዳ ፡ ኀጢአት ፡ በብረት ፡ ብርዕና ፡ በተሾለ ፡ እብነ ፡ አልማዝ ፡ ተጽፏል ፤ በልባቸው ፡ጽላትና ፡ በመሠዊያቸው ፡
ቀንዶች ፡ ተቀርጿል ።

2 ፤ ልጆቻቸውም ፡ ከለመለሙ ፡ ዛፎች ፡ በታችና ፡ በረዘሙት ፡ ኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መሠዊያቸውንና ፡
የማምለኪያ ፡ ዐጸዳቸውን ፡ ያስባሉ ።

3 ፤ በሜዳ ፡ ያለው ፡ ተራራዬ ፡ ሆይ ፥ ባለጠግነትኽንና ፡ መዝገብኽን ፡ ኹሉ ፡ የኰረብታውን ፡ መስገጃዎችኽም ፡ ስለ ፡
ኀጢአት ፡ በድንበሮችኽ ፡ ኹሉ ፡ ለመበዝበዝ ፡ እሰጣለኹ ።

4 ፤ አንተም ፡ የሰጠኹኽን ፡ ርስት ፡ ትለቃለኽ ፡ ለዘለዓለምም ፡ በማታውቃትም ፡ ምድር ፡ ለጠላቶቻችኹ ፡ ባሪያ ፡
አደርግኻለኹ ፤ ለዘለዓለም ፡ የሚነደውን ፡ እሳት ፡ በቍጣዬ ፡ አንድዳችኋልና ።

5 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በሰው ፡ የሚታመን ፡ ሥጋ ፡ ለባሹንም ፡ ክንዱ ፡ የሚያደርግ ፡ ልቡም ፡
ከእግዚአብሔር ፡ የሚመለስ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ነው ።

6 ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳለ ፡ ቍጥቋጦ ፡ ይኾናል ፥ መልካምም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አያይም ፤ ሰውም ፡ በሌለበት ፥ ጨው ፡
ባለበት ፡ ምድር ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በደረቅ ፡ ስፍራ ፡ ይቀመጣል ።

7 ፤ በእግዚአብሔር ፡ የታመነ ፡ እምነቱም ፡ እግዚአብሔር ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ቡሩክ ፡ ነው ።

8 ፤ በውሃ ፡ አጠገብ ፡ እንደ ፡ ተተከለ ፥ በወንዝም ፡ዳር ፡ ሥሩን ፡ እንደሚዘረጋ ፡ ሙቀትም ፡ ሲመጣ ፡ እንደማይፈራ ፡
ቅጠሉም ፡ እንደሚለመልም ፥ በድርቅ ፡ ዓመትም ፡ እንደማይሠጋ ፡ ፍሬውንም ፡ እንደማያቋርጥ ፡ ዛፍ ፡ ይኾናል ።

9 ፤ የሰው ፡ ልብ ፡ ከኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ተንኰለኛ ፡ እጅግም ፡ ክፉ ፡ ነው ፤ ማንስ ፡ ያውቀዋል ፧

10 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፥ እንደ ፡ ሥራው ፡ ፍሬ ፡ እሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ልብን ፡
እመረምራለኹ ፡ ኵላሊትንም ፡ እፈትናለኹ ።

11 ፤ ያልወለደችውን ፡ እንደምታቅፍ ፡ ቆቅ ፥ እንዲሁ ፡ በቅን ፡ ሳይኾን ፡ ባለጠግነትን ፡ የሚሰበስብ ፡ ሰው ፡
ነው ፤ በእኩሌታ ፡ ዘመኑ ፡ ይተወዋል ፥ በፍጻሜውም ፡ ሰነፍ ፡ ይኾናል ።

12 ፤ የመቅደሳችን ፡ ስፍራ ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የክብር ፡ ዙፋን ፡ ነው ።

13 ፤ አቤቱ ፥ የእስራኤል ፡ ተስፋ ፡ ሆይ ፥ የሚተዉኽ ፡ ኹሉ ፡ ያፍራሉ ፤ ከአንተም ፡ የሚለዩ ፡ የሕይወትን ፡ ውሃ ፡
ምንጭ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተዋልና ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ ይጻፋሉ ።

14 ፤ አቤቱ ፥ ፈውሰኝ ፡ እኔም ፡ እፈወሳለኹ ፤ አድነኝ ፡ እኔም ፡ እድናለኹ ፤ አንተ ፡ ምስጋናዬ ፡ ነኽና ።

15 ፤ እንሆ ፦ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወዴት ፡ አለች ፧ አኹን ፡ ትምጣ ፡ ይሉኛል ።

16 ፤ እኔም ፡ አንተን ፡ ተከትዬ ፡ እረኛ ፡ ከመኾን ፡ አልቸኰልኹም ፥ የመከራንም ፡ ቀን ፡ አልወደድኹም ፤ አንተ ፡
ታውቃለኽ ፤ ከከንፈሬ ፡ የወጣው ፡ በፊትኽ ፡ ነበረ ።

17 ፤ ለማስፈራራት ፡ አትኹንብኝ ፤ በመከራ ፡ ቀን ፡ አንተ ፡ መጠጊያዬ ፡ ነኽ ።

18 ፤ አሳዳጆቼ ፡ ይፈሩ ፥ እኔ ፡ ግን ፡ አልፈር ፤ እነርሱ ፡ ይደንግጡ ፥ እኔ ፡ ግን ፡ አልደንግጥ ፤ ክፉንም ፡ ቀን ፡



www.ethiopianorthodox.org

አምጣባቸው ፥ በኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ ጥፋት ፡ አጥፋቸው ።

19 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይለኛል ፦ ኺድ ፥ የይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ በሚገቡበትና ፡ በሚወጡበት ፡ በሕዝቡ ፡
ልጆች ፡ በር ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ በሮች ፡ ኹሉ ፡ ቁም ፤

20 ፤ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ በእነዚህ ፡ በሮች ፡ የምትገቡ ፥ እናንተ ፡ የይሁዳ ፡ ነገሥታት ፥ ይሁዳም ፡
ኹሉ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ የምትኖሩ ፡ ኹሉ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

21 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለራሳችኹ ፡ ተጠንቀቁ ፥ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ሸክም ፡
አትሸከሙ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ በሮች ፡ አታግቡ ፥

22 ፤ ከቤቶቻችኹም ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ሸክምን ፡ አታውጡ ፥ ሥራንም ፡ ኹሉ ፡ አትሥሩበት ፤ አባቶቻችኹንም ፡
እንዳዘዝኹ ፡ የሰንበትን ፡ ቀን ፡ ቀድሱ ።

23 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ አልሰሙም ፡ ጆሯቸውን ፡ አላዘነበሉም ፥ እንዳይሰሙና ፡ እንዳይገሠጹም ፡ ዐንገታቸውን ፡ አደነደኑ ።

24 ፤ እኔን ፡ ፈጽሞ ፡ ብትሰሙ ፤ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ በሮች ፡ ሸክም ፡
ባታገቡ ፥ የሰንበትንም ፡ ቀን ፡ ብትቀድሱ ፡ ሥራንም ፡ ኹሉ ፡ ባትሠሩበት ፥

25 ፤ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጡ ፡ ነገሥታትና ፡ መሳፍንት ፡ በሠረገላዎችና ፡ በፈረሶች ፡ ላይ ፡ እየተቀመጡ ፡
በዚች ፡ ከተማ ፡ በሮች ፡ ይገባሉ ፤ እነርሱና ፡ መሳፍንቶቻቸው ፡ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚቀመጡ ፡
ይገባሉ ፥ ይህችም ፡ ከተማ ፡ ለዘለዓለም ፡ የሰው ፡ መኖሪያ ፡ ትኾናለች ።

26 ፤ የሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕትን ፡ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፡ ዕጣኑንም ፡ የምስጋናውንም ፡
መሥዋዕት ፡ ይዘው ፡ ከይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ከኢየሩሳሌምም ፡ ዙሪያ ፡ ከብንያምም ፡ አገር ፡ ከቈላውም ፡ ከደጋውም ፡
ከደቡብም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ይመጣሉ ።

27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሰንበትን ፡ ቀን ፡ እንድትቀድሱ ፥ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ሸክምን ፡ ተሸክማችኹ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሮች ፡
እንዳትገቡ ፡ የነገርኂችኹን ፡ ባትሰሙኝ ፥ በበሮቿ ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ አነዳለኹ ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ አዳራሾች ፡
ትበላለች ፥ አትጠፋም ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ምዕራፍ ፡ 18 ፤

1-2 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፥ እንዲህም ፡ አለው ፦ ተነሥተኽ ፡ ወደሸክላ ፡ ሠሪው ፡
ቤት ፡ ውረድ ፥ በዚያም ፡ ቃሌን ፡ አሰማኻለኹ ።

3 ፤ ወደሸክላ ፡ ሠሪው ፡ ቤትም ፡ ወረድኹ ፥ እንሆም ፥ ሥራውን ፡ በመንኰራኵር ፡ ላይ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ።

4 ፤ ከጭቃም ፡ ይሠራው ፡ የነበረ ፡ ዕቃ ፡ በሸክላ ፡ ሠሪው ፡ እጅ ፡ ተበላሸ ፥ ሸክላ ፡ ሠሪውም ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ መልሶ ፡
ሌላ ፡ ዕቃ ፡ አድርጎ ፡ ሠራው ።

5 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

6 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ ሸክላ ፡ ሠሪ ፡ እንደሚሠራ ፡ በእውኑ ፡ እኔ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ መሥራት ፡
አይቻለኝምን ፨ እንሆ ፥ ጭቃው ፡ በሸክላ ፡ ሠሪ ፡ እጅ ፡ እንዳለ ፥ እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ በእኔ ፡ እጅ ፡ አላችኹ ።

7 ፤ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ መንግሥትም ፡ እነቅል ፡ አፈርስም ፡ አጠፋም ፡ ዘንድ ፡ በተናገርኹ ፡ ጊዜ ፥

8 ፤ ይህ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የተናገርኹበት ፡ ሕዝብ ፡ ከክፋቱ ፡ ቢመለስ ፥ እኔ ፡ አደርግበት ፡ ዘንድ ፡ ካሰብኹት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡
እጸጸታለኹ ።

9 ፤ ስለ ፡ ሕዝቡም ፡ ስለ ፡ መንግሥትም ፡ እሠራውና ፡ እተክለው ፡ ዘንድ ፡ በተናገርኹ ፡ ጊዜ ፥

10 ፤ በፊቴ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ቢያደርግ ፡ ቃሌንም ፡ ባይሰማ ፥ እኔ ፡ አደርግለት ፡ ዘንድ ፡ ስለተናገርኹት ፡ መልካም ፡ ነገር ፡
እጸጸታለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

11 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ለይሁዳ ፡ ሰዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚቀመጡ ። እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ክፉ ፡ ነገር ፡ እፈጥርባችኋለኹ ፥ ዐሳብንም ፡ ዐስብባችኋለኹ ፤ አኹንም ፡ ኹላችኹ ፡ ከክፉ ፡ መንገዳችኹ ፡ ተመለሱ ፥ መንገዳችኹንና ፡ ሥራችኹንም ፡ አቅኑ ፡ ብለኽ ፡ ተናገራቸው ።

12 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፦ እንጨክናለን ፤ ዐሳባችንን ፡ ተከትለን ፡ እንኼዳለን ፡ ኹላችንም ፡ እንደ ፡ ክፉው ፡ ልባችን ፡ እልከኝነት ፡ እናደርጋለን ፡ አሉ ።

13 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በአሕዛብ ፡ መካከል ፦ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ማን ፡ ሰምቷል ፧ ብላችኹ ፡ ጠይቁ ። የእስራኤል ፡ ድንግል ፡ በጣም ፡ የሚያስደነግጠውን ፡ ነገር ፡ አድርጋለች ።

14 ፤ በእውኑ ፡ የሊባኖስ ፡ በረዶ ፡ የምድረ ፡ በዳውን ፡ ድንጋይ ፡ ይተዋልን ፧ ወይስ ፡ ከሩቅ ፡ የምትመጣው ፡ ቀዝቃዛዪቱ ፡ ፈሳሽ ፡ ውሃ ፡ ትደርቃለችን ፧

15 ፤ ሕዝቤ ፡ ግን ፡ ረስተውኛል ፡ ለከንቱ ፡ ነገርም ፡ ዐጥነዋል ፤ ከመንገዱም ፡ ተሰናክለዋል ፡ ከቀድሞውም ፡ ጐዳና ፡ ርቀው ፡ ወዳልተሠራው ፡ ወደ ፡ ጠማማው ፡ መንገድ ፡ ፈቀቅ ፡ ብለዋል ።

16 ፤ ምድራቸውን ፡ ለመደነቂያና ፡ ለዘለዓለም ፡ ማፏጫ ፡ አድርገዋል ፤ የሚያልፍባት ፡ ኹሉ ፡ ይደነቃል ፥ ራሱንም ፡ ያነቃንቃል ።

17 ፤ በጠላት ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ እበትናቸዋለኹ ፥ በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ ዠርባዬን ፡ እንጂ ፡ ፊቴን ፡ አላሳያቸውም ።

18 ፤ እነርሱም ፦ ሕግ ፡ ከካህን ፥ ምክርም ፡ ከጠቢብ ፥ ቃልም ፡ ከነቢይ ፡ አይጠፋምና ፡ ኑ ፥ በኤርምያስ ፡ ላይ ፡ ዐሳብን ፡ እናስብ ። ኑ ፥ በምላስ ፡ እንምታው ፥ ቃሉንም ፡ ኹሉ ፡ አናድምጥ ፡ አሉ ።

19 ፤ አቤቱ ፥ አድምጠኝ ፥ የክርክሬንም ፡ ቃል ፡ ስማ ።

20 ፤ ለነፍሴ ፡ ጕድጓድ ፡ ቈፍረዋልና ፥ በእውኑ ፡ በመልካም ፡ ፋንታ ፡ ክፉ ፡ ይመለሳልን ፧ ስለ ፡ እነርሱ ፡ በመልካም ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ቍጣኽንም ፡ ከነርሱ ፡ እመልስ ፡ ዘንድ ፡ በፊትኽ ፡ እንደ ፡ ቆምኹ ፡ ዐስብ ።

21 ፤ ስለዚህ ፥ ልጆቻቸውን ፡ ለራብ ፡ ስጥ ፥ ለሰይፍም ፡ እጅ ፡ አሳልፈኽ ፡ ስጣቸው ፥ ሚስቶቻቸውም ፡ የወላድ ፡ መካንና ፡ መበለቶች ፡ ይኹኑ ፥ ወንዶቻቸውም ፡ በሞት ፡ ይጥፉ ፥ ጕልማሳዎቻቸውም ፡ በሰልፍ ፡ ጊዜ ፡ በሰይፍ ፡ ይመቱ ።

22 ፤ ሊይዙኝ ፡ ጕድጓድ ፡ ቈፍረዋልና ፥ ለእግሮቼም ፡ ወጥመድ ፡ ሸሽገዋልና ፥ ድንገት ፡ በላያቸው ፡ ጭፍራ ፡ ባመጣኽ ፡ ጊዜ ፡ ከቤታቸው ፡ ጩኸት ፡ ይሰማ ።

23 ፤ አንተ ፡ ግን ፥ አቤቱ ፥ ይገድሉኝ ፡ ዘንድ ፡ በላዬ ፡ የመከሩትን ፡ ምክር ፡ ኹሉ ፡ ታውቃለኽ ፤ በደላቸውን ፡ ይቅር ፡ አትበል ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ከፊትኽ ፡ አትደምስስ ፤ በፊትኽም ፡ ይውደቁ ፥ በቍጣኽ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁ ፡ አድርግባቸው ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ምዕራፍ ፡ 19 ፤

1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ኺድ ፥ ከሸክላ ፡ ሠሪ ፡ ገምቦ ፡ ግዛ ፥ ከሕዝቡም ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ከካህናት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ውሰድ ፤

2 ፤ በካርሲት ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ አጠገብ ፡ ወዳለው ፡ ወደሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ኺድ ፥ በዚያም ፡ የምነግርኽን ፡ ቃል ፡ ተናገር ፥

3 ፤ እንዲህም ፡ በል ፦ የይሁዳ ፡ ነገሥታትና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የሰማውን ፡ ሰው ፡ ዦሮ ፡ ጭው ፡ የሚያደርግ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፥ እንሆ ፥ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ አመጣለኹ ።

4 ፤ ትተውኛልና ፥ ይህንም ፡ ስፍራ ፡ እንግዳ ፡ አድርገውታልና ፥ እነርሱና ፡ አባቶቻቸውም ፡ ለማያውቋቸው ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ ዐጥነዋልና ፥ የይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ ይህን ፡ ስፍራ ፡ በንጹሕ ፡ ደም ፡ ሞልተዋልና ፥



www.ethiopianorthodox.org

5 ፤ እኔም ፡ ያላዘዝኹትን ፡ ያልተናገርኹትንም ፡ ወደ ፡ ልቤም ፡ ያልገባውን ፥ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገው ፡
ለበዓል ፡ ልጆቻቸውን ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉ ፡ ዘንድ ፡ የበዓልን ፡ የኰረብታውን ፡ መስገጃዎች ፡ ሠርተዋልና ፥ ስለዚህ ፥

6 ፤ እንሆ ፥ ይህ ፡ ስፍራ ፡ የዕርድ ፡ ሸለቆ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ቶፌት ፡ ወይም ፡ የሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ዳግመኛ ፡
የማይባልበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

7 ፤ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ምክር ፡ አፈርሳለኹ ፥ በጠላቶቻቸውም ፡ ፊት ፡ በሰይፍና ፡
ነፍሳቸውን ፡ በሚሹት ፡ እጅ ፡ እጥላቸዋለኹ ፥ ሬሳቸውንም ፡ ለሰማይ ፡ ወፎችና ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ መብል ፡ አድርጌ ፡
እሰጣለኹ ።

8 ፤ ይህችንም ፡ ከተማ ፡ ለመደነቂያና ፡ ለማፏጫ ፡ አደርጋታለኹ ፤ የሚያልፍባትም ፡ ኹሉ ፡ ስለተደረገባት ፡
መቅሠፍት ፡ ኹሉ ፡ ይደነቃል ፡ ከንፈሩንም ፡ ይመጥጣል ።

9 ፤ የወንዶችና ፡ የሴቶች ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ሥጋ ፡ አበላቸዋለኹ ፥ ኹሉም ፡ ጠላቶቻቸውንና ፡ ነፍሳቸውን ፡ የሚሹት ፡
በሚያስጨንቋቸው ፡ ጭንቀትና ፡ መከበብ ፡ የባልንጀራዎቻቸውን ፡ ሥጋ ፡ ይበላሉ ።

10 ፤ ገምቦውንም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በሚኼዱ ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ ትሰብራለኽ ፥

11 ፤ እንዲህም ፡ ትላቸዋለኽ ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የሸክላ ፡ ሠሪው ፡ ዕቃ ፡
እንደሚሰባበር ፡ ደግሞም ፡ ይጠገን ፡ ዘንድ ፡ እንደማይቻል ፥ እንዲሁ ፡ ይህን ፡ ሕዝብና ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡
እሰብራለኹ ፤ የሚቀብሩበትም ፡ ስፍራ ፡ ሌላ ፡ የለምና ፡ በቶፌት ፡ ይቀብራሉ ።

12 ፤ እንዲሁ ፡ በዚህ ፡ ስፍራና ፡ በሚኖሩበት ፡ ላይ ፡ አደርጋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ይህችንም ፡ ከተማ ፡ እንደ ፡
ቶፌት ፡ አደርጋለኹ ።

13 ፤ የረከሱትም ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቤቶችና ፡ የይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ቤቶች ፥ እነዚያ ፡ በሰገነታቸው ፡ ላይ ፡ ለሰማይ ፡
ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ያጠኑባቸው ፡ ለሌላዎችም ፡ አማልክት ፡ የመጠጥን ፡ ቍርባን ፡ ያፈሰሱባቸው ፡ ቤቶች ፡ ኹሉ ፥ እንደ ፡
ቶፌት ፡ ስፍራ ፡ ይኾናሉ ።

14 ፤ ኤርምያስም ፡ እግዚአብሔር ፡ ትንቢት ፡ ሊናገር ፡ ወደዚያ ፡ ልኮት ፡ ከነበረው ፡ ስፍራ ፡ ከቶፌት ፡
መጣ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ቆሞ ፡ ለሕዝብ ፡ ኹሉ ፦

15 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ቃሌን ፡ እንዳይሰሙ ፡ ዐንገታቸውን ፡
አደንድነዋልና ፥ እንሆ ፥ በዚች ፡ ከተማና ፡ በመንደሮቿ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የተናገርኹባትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡
አመጣለኹ ።

## ትንቢት ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ምዕራፍ ፡ 20 ፤

1 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የተሾመው ፡ አለቃ ፡ የካህኑ ፡ የኢሜር ፡ ልጅ ፡ ጳስኮር ፡ ኤርምያስ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡
ትንቢት ፡ ሲናገር ፡ ሰማ ።

2 ፤ ጳስኮርም ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ መታው ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ በነበረው ፡ በላይኛው ፡ በብንያም ፡ በር ፡
ባለው ፡ በእግር ፡ ግንድ ፡ ውስጥ ፡ አኖረው ።

3 ፤ በነጋውም ፡ ጳስኮር ፡ ኤርምያስን ፡ ከግንድ ፡ ውስጥ ፡ አወጣው ። ኤርምያስም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ እግዚአብሔር ፡
ስምኽን ፦ ማጎርሚሳቢብ ፡ እንጂ ፡ ጳስኮር ፡ ብሎ ፡ አይጠራኽም ።

4 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ ለራስኽና ፡ ለወዳጆችኽ ፡ ኹሉ ፡ ፍርሀት ፡ አደርግኻለኹ ፤ እነርሱም ፡
በጠላቶቻቸው ፡ ሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ፡ ዐይኖችኽም ፡ ያያሉ ፤ ይሁዳንም ፡ ኹሉ ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡
እሰጣለኹ ፥ ርሱም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ያፈልሳቸዋል ፡ በሰይፍም ፡ ይገድላቸዋል ።

5 ፤ የዚችንም ፡ ከተማ ፡ ባለጠግነት ፡ ኹሉ ፡ ጥሪቷንም ፡ ኹሉ ፡ ክብሯንም ፡ ኹሉ ፡ የይሁዳንም ፡ ነገሥታት ፡ መዝገብ ፡
ኹሉ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፥ እነርሱም ፡ ይበዘብዟቸዋል ፡ ይዘውም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡
ያፈልሷቸዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

6 ፤ አንተም ፥ ጳስኮር ፡ ሆይ ፥ በቤትኽም ፡ የሚኖሩት ፡ ኹሉ ፡ ተማርካችኹ ፡ ትኼዳላችኹ ፤ አንተም ፡ በሐሰትም ፡ ትንቢት ፡ የተናገርኽላቸው ፡ ወዳጆችኽ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ትገባላችኹ ፥ በዚያም ፡ ትሞታላችኹ ፥ በዚያም ፡ ትቀበራላችኹ ።

7 ፤ አቤቱ ፥ አታለልኸኝ ፡ እኔም ፡ ተታለልኹ ፥ ከእኔም ፡ በረታኽ ፡ አሸነፍኽም ፤ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ መሳቂያ ፡ ኾኛለኹ ፥ ኹሉም ፡ ያላግጡብኛል ።

8 ፤ በተናገርኹ ፡ ቍጥር ፡ እጮኻለኹ ፤ ግፍና ፡ ጥፋት ፡ ብዬ ፡ እጮኻለኹ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ ስድብና ፡ ዋዛ ፡ ኾኖብኛልና ።

9 ፤ እኔም ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ አላነሣም ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ በስሙ ፡ አልናገርም ፡ ብል ፥ በዐጥንቶቼ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ እንደሚነድ ፡ እሳት ፡ ያለ ፡ በልቤ ፡ ኾነብኝ ፤ ደከምኹ ፥ መሸከምም ፡ አልቻልኹም ።

10 ፤ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ስድብ ፡ ሰምቻለኹ ፥ ማስፈራራትም ፡ ከቦኛል ። መውደቄን ፡ የሚጠብቁ ፡ የሰላሜ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፦ ምናልባት ፡ ይታለል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እናሸንፈውም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ርሱንም ፡ እንበቀል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ክሰሱት ፡ እኛም ፡ እንከሰዋለን ፡ ይላሉ ።

11 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ኀያልና ፡ እንደ ፡ ጨካኝ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፥ አሳዳጆቼ ፡ ይሰናከላሉ ፥ አያሸንፉም ፤ አይከናወንላቸውምና ፥ በጽኑ ፡ ዕፍረት ፡ ያፍራሉ ፤ ለዘለዓለምም ፡ በማይረሳ ፡ ጕስቍልና ፡ ይጐሰቍላሉ ።

12 ፤ አቤቱ ፥ ጻድቅን ፡ የምትመረምር ፡ ኵላሊትንና ፡ ልብን ፡ የምትመለከት ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ክርክሬን ፡ ገልጨልኻለኹና ፡ በቀልኽን ፡ በላያቸው ፡ ለይ ።

13 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ዘምሩ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመስግኑ ፤ የችግረኛውን ፡ ነፍስ ፡ ከክፉ ፡ አድራጊዎች ፡ እጅ ፡ አድኗልና ።

14 ፤ የተወለድኹባት ፡ ቀን ፡ የተረገመች ፡ ትኹን ፤ እናቴ ፡ እኔን ፡ የወለደችባት ፡ ቀን ፡ የተባረከች ፡ አትኹን ።

15 ፤ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተወልዶልኻል ፡ ብሎ ፡ ለአባቴ ፡ የምሥራች ፡ ነግሮ ፡ ደስ ፡ ያሠኘው ፡ ሰው ፡ የተረገመ ፡ ይኹን ።

16 ፤ ያም ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳይጸጸት ፡ እንደ ፡ ገለበጣቸው ፡ ከተማዎች ፡ ይኹን ፥ በማለዳም ፡ ልቅሶን ፡ በቀትርም ፡ ጩኸትን ፡ ይስማ ፤

17 ፤ እናቴ ፡ መቃብር ፡ ትኾነኝ ፡ ዘንድ ፡ ማሕፀኗም ፡ ዘወትር ፡ ይዞኝ ፡ ያቈይ ፡ ዘንድ ፡ በማሕፀን ፡ ውስጥ ፡ አልገደለኝምና ።

18 ፤ ድካምንና ፡ ጣርን ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ ዘመኔም ፡ በዕፍረት ፡ ታልቅ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ከማሕፀን ፡ ወጣኹ ፧

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ምዕራፍ ፡ 21 ፤

1 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

2 ፤ ይህም ፡ የኾነው ፡ ንጉሡ ፡ ሴዴቅያስ ፦ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ይወጋናልና ፥ ስለ ፡ እኛ ፥ እባክኽ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ጠይቅ ፤ ከእኛም ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ምናልባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተኣምራቱ ፡ ኹሉ ፡ ያደርግ ፡ ይኾናል ፡ ብሎ ፡ የመልክያን ፡ ልጅ ፡ ጳስኮርንና ፡ ካህኑን ፡ የመዕሴያን ፡ ልጅ ፡ ሶፎንያስ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ በላከ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

3 ፤ ኤርምያስም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ሴዴቅያስን ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፦

4 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ በቅጥርም ፡ ውጭ ፡ የከበቧችኹን ፡ ከለዳውያንን ፡ የምትወጉበትን ፡ በእጃችኹ ፡ ያለውን ፡ ዕቃ ፡ ጦራችኹን ፡ እመልሰዋለኹ ፥ እነዚያንም ፡ ወደዚች ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ እሰበስባቸዋለኹ ።

5 ፤ እኔም ፡ በተዘረጋች ፡ እጅና ፡ በብርቱ ፡ ክንድ ፥ በቍጣና ፡ በመዓት ፡ በታላቅም ፡ መቅሠፍት ፡ እወጋችኋለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

6 ፤ በዚችም ፡ ከተማ ፡ የሚኖሩትን ፡ ኹሉ ፡ ሰዎችንና ፡ እንስሳዎችን ፡ እመታለኹ ፥ በጽኑም ፡ ቸነፈር ፡ ይሞታሉ ።

7 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስን ፡ ከቸነፈርና ፡ ከሰይፍ ፡ ከራብም ፡ በዚች ፡
ከተማ ፡ የቀሩትንም ፡ ባሪያዎቹንና ፡ ሕዝቡን ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነጾር ፡ እጅ ፡ በጠላቶቻቸውና ፡ ነፍሳቸውንም ፡
በሚሹት ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹ ፤ ርሱም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡
ይመታቸዋል ፤ አያዝንላቸውም ፥ አይራራላቸውም ፥ አይምራቸውም ።

8 ፤ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ በል ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ፥ በፊታችኹ ፡ የሕይወትን ፡
መንገድና ፡ የሞትን ፡ መንገድ ፡ አድርጌያለኹ ።

9 ፤ በዚች ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ የሚዘገይ ፥ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ ይሞታል ፤ ወጥቶ ፡ ወደከበቧችኹ ፡ ወደ ፡
ከለዳውያን ፡ የሚገባ ፡ ግን ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፥ ነፍሱም ፡ ምርኮ ፡ ትኾንለታለች ።

10 ፤ ለመልካም ፡ ሳይኾን ፡ ለክፉ ፡ ፊቴን ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ አድርጌያለኹና ፤ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡
ትሰጣለች ፥ ርሱም ፡ በእሳት ፡ ያቃጥላታል ።

11 ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

12 ፤ የዳዊት ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለሥራችኹ ፡ ክፋት ፡ ቍጣዬ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡
እንዳይወጣና ፡ ማንም ፡ ሳያጠፋው ፡ እንዳይነድ ፥ በማለዳ ፡ ፍርድን ፡ አድርጉ ፡ የተበዘበዘውንም ፡ ካስጨናቂው ፡ እጅ ፡
አድኑ ።

13 ፤ እነሆ ፥ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ በሜዳ ፡ ላይም ፡ ባለው ፡ ዐምባ ፡ የምትቀመጪ ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡
ነኝ ፤ እናንተም ፦ በእኛ ፡ ላይ ፡ የሚወርድ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ መኖሪያችን ፡ የሚገባ ፡ ማን ፡ ነው ፡፡ የምትሉ ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡
በእናንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፤

14 ፤ እንደ ፡ ሥራችኹም ፡ ፍሬ ፡ እቀጣችኋለኹ ፤ በዱሯም ፡ ውስጥ ፡ እሳትን ፡ አነዳለኹ ፥ በዙሪያዋም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡
ይበላል ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ምዕራፍ ፡ 22 ፤

1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ወደይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ ውረድ ፡ በዚያም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ተናገር ፥

2 ፤ እንዲህም ፡ በል ፦ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ የምትቀመጥ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ አንተና ፡ ባሪያዎችኽ ፡ በእነዚህም ፡
በሮች ፡ የሚገባ ፡ ሕዝብኽ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

3 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ፍርድንና ፡ ጽድቅን ፡ አድርጉ ፡ የተበዘበዘውንም ፡ ካስጨናቂው ፡ እጅ ፡
አድኑ ፤ መጻተኛውንና ፡ ድኻ ፡ አደጉን ፡ መበለቲቱንም ፡ አትበድሉ ፥ አታምፅባቸውም ፥ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ንጹሕ ፡
ደምን ፡ አታፍስሱ ።

4 ፤ ይህንንም ፡ ነገር ፡ ብታደርጉ ፥ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ የሚቀመጡ ፡ ነገሥታት ፥ በሠረገላዎችና ፡ በፈረሶች ፡ ላይ ፡
ተቀምጠው ፥ በዚህ ፡ ቤት ፡ በሮች ፡ ይገባሉ ፤ ርሱም ፡ ባሪያዎቹም ፡ ሕዝቡም ፡ እንዲሁ ፡ ይገባሉ ።

5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህን ፡ ቃል ፡ ባትሰሙ ፥ ይህ ፡ ቤት ፡ ወና ፡ እንዲኾን ፡ በራሴ ፡ ምያለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ አንተ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ገለዓድና ፡ እንደ ፡
ሊባኖስ ፡ ራስ ፡ ነኽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በርግጥ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ማንም ፡ የማይቀመጥባቸውም ፡ ከተማዎች ፡ አደርግኻለኹ ።

7 ፤ መሣሪያም ፡ የሚይዙትን ፡ አጥፊዎች ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ አዘጋጃለኹ ፥ የተመረጡትንም ፡ የዝግባ ፡ ዛፎችኽን ፡
ይቈርጣሉ ፥ በእሳትም ፡ ውስጥ ፡ ይጥሏቸዋል ።

8 ፤ ብዙ ፡ አሕዛብም ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ አጠገብ ፡ ያልፋሉ ፥ ኹሉም ፡ ባልንጀራዎቻቸውን ፦ እግዚአብሔር ፡ በዚች ፡
ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ለምን ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ፡፡ ይላሉ ።

9 ፤ እነርሱም ፦ የአምላካቸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ትተው ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ ስለ ፡ ሰገዱ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ስላመለኳቸውም ፡ ነዋ ፡ ብለው ፡ ይመልሳሉ ።

10 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይመለስምና ፥ የተወለደባትንም ፡ አገር ፡ አያይምና ፡ ለሚወጣ ፡ እጅግ ፡ አልቅሱ ፡ እንጂ ፡ ለሞተ ፡ አታልቅሱ ፡ አትዘኑለትም ።

11 ፤ በአባቱ ፡ በኢዮስያስ ፡ ፋንታ ፡ ስለነገሠው ፡ ከዚህም ፡ ስፍራ ፡ ስለወጣው ፡ ስለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ስለኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ሰሎም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦

12 ፤ እንግዲህም ፡ ወደዚህ ፡ አይመለስም ፥ በተማረከባት ፡ አገር ፡ ይሞታል ፡ እንጂ ፤ ይህችንም ፡ አገር ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አያይም ።

13 ፤ ቤቱን ፡ በግፍ ፡ ሰገነቱንም ፡ በዐመፅ ፡ ለሚሠራ ፥ ባልንጀራውንም ፡ እንዲያው ፡ በከንቱ ፡ ለሚያሠራ ፥ ዋጋውንም ፡ ለማይሰጠው ፤

14 ፤ ለራሴ ፡ ሰፊ ፡ ቤት ፡ ትልቅም ፡ ሰገነት ፡ እሠራለኹ ፡ ለሚል ፥ መስኮትንም ፡ ለሚያወጣ ፥ በዝግባም ፡ ሥራ ፡ ለሚያሳጌጥ ፥ በቀይ ፡ ቀለምም ፡ ለሚቀባው ፡ ወዮለት!

15 ፤ በዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ ስለምትወዳደር ፡ በእውኑ ፡ ትነግሣለኽን ፧ በእውኑ ፡ አባትኽ ፡ አይበላምና ፡ አይጠጣም ፡ ነበርን ፧ ፍርድንና ፡ ጽድቅንስ ፡ አያደርግም ፡ ነበርን ፧ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ መልካም ፡ ኾኖለት ፡ ነበር ።

16 ፤ የድኻውንና ፡ የችግረኛውን ፡ ፍርድ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ፥ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ መልካም ፡ ኾኖ ፡ ነበር ። ይህ ፡ እኔን ፡ ማወቅ ፡ አይደለምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

17 ፤ ዐይንኽና ፡ ልብኽ ፡ ግን ፡ ለሥሥት ፡ ንጹሕ ፡ ደምንም ፡ ለማፍሰስ ፡ ዐመፅንና ፡ ግፍንም ፡ ለመሥራት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

18 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ ስለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ስለኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ኢዮአቄም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወንድሜ ፡ ሆይ ፥ ወዮ! እያሉ ፡ አያለቅሱለትም ፥ ወይም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ወዮ! እያሉ ፡ አያለቅሱለትም ።

19 ፤ አህያም ፡ እንደሚቀበር ፡ ይቀበራል ፥ ከኢየሩሳሌምም ፡ በር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ተጐትቶ ፡ ይጣላል ።

20 ፤ ውሽማዎችሽ ፡ ኹሉ ፡ ጠፍተዋልና ፥ ወደ ፡ ሊባኖስ ፡ ወጥተሽ ፡ ጩኺ ፤ በባሳን ፡ ላይ ፡ ድምፅሽን ፡ አንሺ ፤ በዓባሪምም ፡ ውስጥ ፡ ኾነሽ ፡ ጩኺ ።

21 ፤ በደኅንነትሽ ፡ ጊዜ ፡ ተናገርኹሽ ፤ አንቺም ፦ አልሰማም ፡ አልሽ ። ከሕፃንነትሽ ፡ ዠምሮ ፡ ቃሌን ፡ አለመስማትሽ ፡ መንገድሽ ፡ ነው ።

22 ፤ በግ ፡ ጠባቂዎችሽን ፡ ኹሉ ፡ ነፋስ ፡ ይጠብቃቸዋል ፥ ውሽማዎችሽም ፡ ተማርከው ፡ ይኼዳሉ ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ስለ ፡ ክፋትሽ ፡ ኹሉ ፡ ታፍሪያለሽ ፡ ትጐሳቈዪማለሽ ።

23 ፤ አንቺ ፡ በሊባኖስ ፡ የምትቀመጪ ፥ በዝግባ ፡ ዛፍም ፡ ውስጥ ፡ ጐዦሽን ፡ የምትሠሪ ፡ ሆይ ፥ ምጥ ፡ እንደ ፡ ያዛት ፡ ሴት ፡ ሕማም ፡ በያዘሽ ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ ታጓሪያለሽ!

24 ፤ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአቄም ፡ ልጅ ፡ ኢኮንያን ፡ የቀኝ ፡ እጄ ፡ ማኅተም ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ እንኳ ፥ ከዚያ ፡ እነቅልኽ ፡ ነበር ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤

25 ፤ ነፍስኽንም ፡ ለሚሹት ፡ ለምትፈራቸውም ፡ እጅ ፥ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ ለከለዳውያንም ፡ እጅ ፡ እሰጥኻለኹ ።

26 ፤ አንተንም ፡ የወለደችኽንም ፡ እናትኽን ፡ ወዳልተወለዳችኹባት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ እጥላችኋለኹ ፥ በዚያም ፡ ትሞታላችኹ ።

27 ፤ ይመለሱባትም ፡ ዘንድ ፡ ነፍሳቸው ፡ ወደምትመኘት ፡ ወደዚያች ፡ ምድር ፡ አይመለሱም ።

28 ፤ በእውኑ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ኢኮንያን ፡ የተናቀና ፡ የተሰበረ ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ነውን ፧ ወይስ ፡ ርሱ ፡ ለአንዳች ፡ የማይረባ ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ነውን ፧ ርሱና ፡ ዘሩስ ፡ በማያውቋት ፡ ምድር ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተጥለው ፡ ወደቁ ፧

29 ፤ ምድር ፡ ሆይ ፥ ምድር ፡ ሆይ ፥ ምድር ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሚ ።



www.ethiopianorthodox.org

30 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከዚህ ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ የሚከናወን ፡ በዳዊትም ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጥ ፡ በይሁዳም ፡ የሚነግሥ ፡ እንግዲህ ፡ አይገኝምና ። መካን ፡ በዘመኑም ፡ የማይከናወንለት ፡ ሰው ፡ ብላችኹ ፡ ጻፉ ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ምዕራፍ ፡ 23 ፤

1 ፤ የማሰማሪያዬን ፡ በጎች ፡ ለሚያጠፉና ፡ ለሚበትኑ ፡ እረኞዎች ፡ ወዮላቸው! ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

2 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፥ ሕዝቤን ፡ ስለሚጠብቁ ፡ እረኞዎች ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በጎቼን ፡ በትናችኋል ፥ አባሯችኋቸውማል ፥ አልጐበኛችኋቸውምም ፤ እንሆ ፥ የሥራችኹን ፡ ክፋት ፡ እጐበኝባችኋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

3 ፤ የመንጋዬም ፡ ቅሬታ ፡ ካባረርኋቸው ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ በረታቸው ፡ ሰብስቤ ፡ እመልሳቸዋለኹ ፤ እነርሱም ፡ ያፈራሉ ፥ ይበዙማል ።

4 ፤ የሚጠብቋቸውን ፡ እረኞዎች ፡ አስነሣላቸዋለኹ ፥ ዳግመኛም ፡ አይፈሩምና ፡ አይደነግጡም ፥ ከነሱም ፡ አንድ ፡ አይጐድልም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

5 ፤ እንሆ ፥ ለዳዊት ፡ ጻድቅ ፡ ቊጥቋጥ ፡ የማስነሣበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ርሱም ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ይነግሣል ፥ ይከናወንለታልም ፥ በምድርም ፡ ፍርድንና ፡ ጽድቅን ፡ ያደርጋል ።

6 ፤ በዘመኑም ፡ ይሁዳ ፡ ይድናል ፡ እስራኤልም ፡ ተዘልሎ ፡ ይቀመጣል ፥ የሚጠራበትም ፡ ስም ፦ እግዚአብሔር ፡ ጽድቃችን ፡ ተብሎ ፡ ነው ።

7 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ዳግመኛ ፡ የማይባልበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤

8 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ ዘር ፡ ከሰሜን ፡ አገርና ፡ ካሰደድኋቸውም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ያወጣና ፡ የመራ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ይባላል ፤ በምድራቸውም ፡ ይቀመጣሉ ።

9 ፤ ስለ ፡ ነቢያት ፤ ልቤ ፡ በውስጤ ፡ ተሰብሯል ፡ ዐጥንቶቼም ፡ ኹሉ ፡ ታውከዋል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ የተነሣ ፡ ከቅዱስ ፡ ቃሉም ፡ የተነሣ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንዳሸነፈው ፡ እንደ ፡ ሰካራም ፡ ሰው ፡ ኾኛለኹ ።

10 ፤ ምድር ፡ ከአመንዝራዎች ፡ ተሞልታለችና ፥ ከመርገምም ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ አልቅሳለች ፤ የምድረ ፡ በዳ ፡ ማሰማሪያ ፡ ደርቋል ፤ አካኼዳቸው ፡ ክፉ ፡ ነው ፥ ብርታታቸውም ፡ ቅን ፡ አይደለም ።

11 ፤ ነቢዩና ፡ ካህኑም ፡ ረክሰዋልና ፥ በቤቴም ፡ ውስጥ ፡ ክፋታቸውን ፡ አግኝቻለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

12 ፤ ስለዚህ ፥ መንገዳቸው ፡ በጨለማ ፡ እንዳለች ፡ እንደ ፡ ድጥ ፡ ስፍራ ፡ ትኾንባቸዋለች ፥ እነርሱም ፡ ፍግምግም ፡ ብለው ፡ ይወድቁባታል ፤ እኔም ፡ በምጐበኛቸው ፡ ዓመት ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አመጣባቸዋለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

13 ፤ በሰማርያ ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ ስንፍናን ፡ አይቻለኹ ፤ በበዓል ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፥ ሕዝቤንም ፡ እስራኤል ፡ ያስቱ ፡ ነበር ።

14 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ የሚያስደነግጥን ፡ ነገር ፡ አይቻለኹ ፤ ያመነዝራሉ ፡ በሐሰትም ፡ ይኼዳሉ ፤ ማንም ፡ ከክፋቱ ፡ እንዳይመለስ ፡ የክፉ ፡ አድራጊዎችን ፡ እጅ ፡ ያበረታሉ ፤ ኹሉም ፡ እንደ ፡ ሰዶም ፡ የሚኖሩባትም ፡ እንደ ፡ ገሞራ ፡ ኾኑብኝ ።

15 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ከኢየሩሳሌም ፡ ነቢያት ፡ ዘንድ ፡ ርኵሰት ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ወጥቷልና ፥ ሬትን ፡ አበላቸዋለኹ ፥ የሐሞትንም ፡ ውሃ ፡ አጠጣቸዋለኹ ።

16 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ትንቢት ፡ የሚናገሩላችኹን ፡ የነቢያትን ፡ ቃል ፡ አትስሙ ፤ ከንቱነትን ፡ ያስተምሯችኋል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ሳይኾን ፡ ከገዛ ፡ ልባቸው ፡ የወጣውን ፡ ራእይ ፡ ይናገራሉ ።

17 ፤ ለሚንቁኝ ፡ ኹልጊዜ ፦ እግዚአብሔር ፦ ሰላም ፡ ይኾንላችኋል ፡ ብሏል ፡ ይላሉ ፤ በልቡም ፡ እልከኝነት ፡



www.ethiopianorthodox.org

ለሚኼድ ፡ ኹሉ ፡— ክፉ ፡ ነገር ፡ አያገኛችኹም ፡ ይላሉ ።

18 ፤ ቃሉን ፡ ያይና ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምክር ፡ የቆመ ፡ ማን ፡ ነውና ፧ ቃሉንስ ፡ ያደመጠ ፡ የሰማስ ፡
ማን ፡ ነው ፧

19 ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፥ ርሱም ፡ ቍጣው ፥ የሚያገለባብጥ ፡ ዐውሎ ፡ ነፍስ ፡
ወጥቷል ፤ የዐመፀኛዎችን ፡ ራስ ፡ ይገለባብጣል ።

20 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ የልቡን ፡ ዐሳብ ፡ ሠርቶ ፡ እስኪፈጽም ፡ ድረስ ፡ አይመለስም ፤ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡
ፈጽማችኹ ፡ ታስተውሉታላችኹ ።

21 ፤ እኔ ፡ ሳልካቸው ፡ እነዚህ ፡ ነቢያት ፡ ሮጡ ፤ እኔም ፡ ሳልነግራቸው ፡ ትንቢትን ፡ ተናገሩ ።

22 ፤ በምክሬ ፡ ግን ፡ ቢቆሙ ፡ ኖሮ ፥ ለሕዝቤ ፡ ቃሌን ፡ ባሰሙ ፡ ነበር ፥ ከክፉም ፡ መንገዳቸው ፡ ከሥራቸውም ፡ ክፋት ፡
በመለሷቸው ፡ ነበር ።

23 ፤ እኔ ፡ የቅርብ ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ የሩቅ ፡ አምላክ ፡ አይደለኹም ።

24 ፤ ሰው ፡ በስውር ፡ ቢሸሸግ ፥ እኔ ፡ አላየውምን ፧ ሰማይንና ፡ ምድርንስ ፡ የሞላኹ ፡ እኔ ፡ አይደለኹምን ፧ ይላል ፡
እግዚአብሔር ።

25 ፤ ዐለምኹ ፥ ዐለምኹ ፡ እያሉ ፡ በስሜ ፡ ሐሰትን ፡ የሚናገሩትን ፡ የነቢያትን ፡ ነገር ፡ ሰምቻለኹ ።

26 ፤ ትንቢትን ፡ በሐሰት ፡ በሚናገሩ ፥ የልባቸውንም ፡ ሽንገላ ፡ በሚናገሩ ፡ በነቢያት ፡ ልብ ፡ ይህ ፡ የሚኾነው ፡ እስከ ፡
መቼ ፡ ነው ፧

27 ፤ አባቶቻቸው ፡ ስለ ፡ በዓል ፡ ስሜን ፡ እንደ ፡ ረሱ ፥ እያንዳንዱ ፡ ለባልንጀራው ፡ በሚናገራት ፡ ሕልማቸው ፡ ሕዝቤ ፡
ስሜን ፡ ለማስረሳት ፡ ያስባሉ ።

28 ፤ የሚያልም ፡ ነቢይ ፡ ሕልምን ፡ ይናገር ፤ ቃሌም ፡ ያለበት ፡ ቃሌን ፡ በእውነት ፡ ይናገር ። ገለባ ፡ ከስንዴ ፡ ጋራ ፡
ምን ፡ አለው ፧

29 ፤ በእውኑ ፡ ቃሌ ፡ እንደ ፡ እሳት ፥ ድንጋዩንም ፡ እንደሚያደቅ ፡ መዶሻ ፡ አይደለችምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

30 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ እያንዳንዱ ፡ ከባልንጀራው ፡ ዘንድ ፡ ቃሌን ፡ በሚሰርቁ ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ።

31 ፤ እንሆ ፥ ከምላሳቸው ፡ ትንቢትን ፡ አውጥተው ። ርሱ ፡ ይላል ፡ በሚሉ ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

32 ፤ እንሆ ፥ ሐሰትን ፡ በሚያልሙ ፡ በሚናገሩም ፡ በሐሰታቸውና ፡ በድፍረታቸውም ፡ ሕዝቤን ፡ በሚያስቱ ፡ በነቢያት ፡
ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እኔም ፡ አልላክኋቸውም ፡ አላዘዝኋቸውምም ፡ ለእነዚህም ፡ ሕዝብ ፡ በማናቸውም ፡
አይረቧቸውም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

33 ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ነቢይ ፡ ወይም ፡ ካህን ፡— የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብሎ ፡
ቢጠይቅኽ ፥ አንተ ፡— ሸክሙ ፡ እናንተ ፡ ናችኹ ፥ እጥላችኹማለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ትላቸዋለኽ ።

34 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ የሚለውን ፡ ነቢይንና ፡ ካህንን ፡ ሕዝቡንም ፡ ያን ፡ ሰውና ፡ ቤቱን ፡ እቀጣለኹ ።

35 ፤ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ለባልንጀራው ፥ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ለወንድሙ ፡ እንዲህ ፡ ይበል ፡— እግዚአብሔር ፡ የመለሰው ፡
ምንድር ፡ ነው ፧ እግዚአብሔርስ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ተናገረ ፧

36 ፤ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ ቃል ፡ ሸክም ፡ ይኾንበታልና ፥ የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ ይኾንበታልና ፥ የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡
ብላችኹ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አትጥሩ ፤ የሰራዊትን ፡ ጌታ ፡ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የሕያውን ፡ አምላክ ፡
ቃል ፡ ለውጣችኋልና ።

37 ፤ ለነቢዩ ፡— እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ መለሰልኽ ፧ እግዚአብሔርስ ፡ የተናገረው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ትላለኽ ።

38 ፤ ነገር ፡ ግን ፡— የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ ብትሉ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እኔ ፡— የእግዚአብሔር ፡



www.ethiopianorthodox.org

ሸክም ፡ አትበሉ ፡ ብዬ ፡ ልኬባችኋለኹና ፥ እናንተም ፡ ይህን ፡ ቃል ፦

39 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ ብላችኋልና ፥ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ ፈጽሜ ፡ እረሳችኋለኹ ፥ እናንተንም ፡ ለእናንተና ፡ ለአባቶቻችኹም ፡ የሰጠኋትን ፡ ከተማ ፡ ከፊቴ ፡ እጥላለኹ ።

40 ፤ የዘለዓለምንም ፡ ስድብ ፡ ከቶም ፡ ተረስቶ ፡ የማይጠፋውን ፡ የዘለዓለምን ፡ ዕፍረት ፡ አመጣባችኋለኹ ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።

ምዕራፍ ፡ 24 ፤

1 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአቄምን ፡ ልጅ ፡ ኢኮንያንን ፡ የይሁዳንም ፡ አለቃዎች ፡ ጠራቢዎችንና ፡ ብረት ፡ ሠራተኛዎችን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ማርኮ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ካፈለሳቸው ፡ በኋላ ፥ እግዚአብሔር ፡ አሳየኝ ፥ እንሆም ፥ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ፊት ፡ ኹለት ፡ ቅርጫት ፡ በለስ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

2 ፤ በአንደኛዪቱ ፡ ቅርጫት ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ በለስ ፡ የሚመስል ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ በለስ ፡ ነበረባት ፤ በኹለተኛዪቱ ፡ ቅርጫት ፡ ከክፋቱ ፡ የተነሣ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ የማይቻል ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ በለስ ፡ ነበረባት ።

3 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ኤርምያስ ፡ ሆይ ፥ የምታየው ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ፧ አለኝ ። እኔም ፦ በለስን ፡ አያለኹ ፤ እጅግ ፡ መልካም ፡ የኾነ ፡ መልካም ፡ በለስ ፥ ከክፋቱም ፡ የተነሣ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ የማይቻል ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ የኾነ ፡ ክፉ ፡ በለስ ፡ ነው ፡ አልኹ ።

4 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

5 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንደዚህ ፡ እንደ ፡ መልካሙ ፡ በለስ ፥ እንዲሁ ፡ ከዚህ ፡ ስፍራ ፡ ወደከለዳውያን ፡ ምድር ፡ የሰደድኹትን ፡ የይሁዳን ፡ ምርኮ ፡ ለበጎነት ፡ እመለከተዋለኹ ።

6 ፤ ዐይኔንም ፡ ለበጎነት ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ አደርጋለኹ ፡ ወደዚችም ፡ ምድር ፡ እመልሳቸዋለኹ ፤ እሠራቸዋለኹ ፡ እንጂ ፡ አላፈርሳቸውም ፤ እተክላቸዋለኹ ፡ እንጂ ፡ አልነቅላቸውም ።

7 ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ የሚያውቅ ፡ ልብ ፡ እሰጣቸዋለኹ ፤ በፍጹምም ፡ ልባቸው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመለሳሉና ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑኛል ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ።

8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከክፋቱ ፡ የተነሣ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ እንደማይቻል ፡ እንደ ፡ ክፉው ፡ በለስ ፥ እንዲሁ ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስን ፡ አለቃዎቹንም ፡ በዚችም ፡ አገር ፡ የሚቀሩትን ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቅሬታ ፡ በግብጽም ፡ አገር ፡ የሚቀመጡትን ፡ እጥላቸዋለኹ ።

9 ፤ በማሳድዳቸውም ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ ለስድብና ፡ ለምሳሌ ፡ ለማላገጫና ፡ ለርግማን ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ በምድር ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ለመበተን ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹ ።

10 ፤ ለእነርሱና ፡ ለአባቶቻቸውም ፡ ከሰጠኋቸው ፡ ምድር ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ በመካከላቸው ፡ ሰይፍንና ፡ ራብን ፡ ቸነፈርንም ፡ እሰዳለኹ ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ።

ምዕራፍ ፡ 25 ፤

1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፥ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነጾር ፡ በመዠመሪያው ፡ ዓመት ፥ ስለይሁዳ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

2 ፤ ይህንም ፡ ቃል ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ለይሁዳ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለተቀመጡ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፦

3 ፤ ከይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ከዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮስያስ ፡ ከዐሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ባሉት ፡ በእነዚህ ፡ በኻያ ፡ ሦስቱ ፡ ዓመታት ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣ ፥ እኔም ፡ ማልጄ ፡ ተነሥቼ ፡ ተናገርኋችኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አልሰማችኹም ።

4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ማልዶ ፡ ተነሥቶ ፡ ባሪያዎቹን ፡ ነቢያትን ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ላከ ፤ እናንተም ፡ አላደመጣችኹም ፡



www.ethiopianorthodox.org

ገሯቻችኹንም ፡ አላዘነበላችኹም ።

5 ፤ ርሱም ፦ ኹላችኹ ፡ እናንተ ፡ ከክፉ ፡ መንገዳችኹና ፡ ከሥራችኹ ፡ ክፋት ፡ ተመለሱ ፤ እግዚአብሔርም ፡
ከዘለዓለም ፡ ወደ ፡ ዘለዓለም ፡ ለእናንተና ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ በሰጣችኹ ፡ ምድር ፡ ተቀመጡ ።

6 ፤ ታመልኳቸውም ፡ ትሰግዱላቸውም ፡ ዘንድ ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ አትከተሉ ፥ ክፉም ፡ እንዳላደርግባችኹ ፡
በእጃችኹ ፡ ሥራ ፡ አታስቈጡኝ ፡ አለ ።

7 ፤ ለእናንተ ፡ ጕዳት ፡ እንዲኾን ፡ በእጃችኹ ፡ ሥራ ፡ ታስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፡ አልሰማችኹኝም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

8 ፤ ስለዚህ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ቃሌን ፡ አልሰማችኹምና ፥ እንሆ ፥

9 ፤ ልኬ ፡ የሰሜንን ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ባሪያዬንም ፡ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾርን ፡ እወስዳለኹ ፥ በዚችም ፡
ምድር ፡ በሚቀመጡባትም ፡ ሰዎች ፡ በዙሪያዋም ፡ ባሉ ፡ በእነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አመጣቸዋለኹ ፤ ፈጽሜም ፡
አጠፋቸዋለኹ ፥ ለመደነቂያና ፡ ለማፏጫም ፡ ለዘለዓለምም ፡ ባድማ ፡ አደርጋቸዋለኹ ።

10 ፤ ከነርሱም ፡ የእልልታን ፡ ድምፅና ፡ የደስታን ፡ ድምፅ ፥ የወንድ ፡ሙሽራን ፡ ድምፅና ፡ የሴት ፡ ሙሽራን ፡
ድምፅ ፥ የወፍጮንም ፡ ድምፅ ፡ የመብራትንም ፡ ብርሃን ፡ አስቀራለኹ ።

11 ፤ ይህችም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ባድማና ፡ መደነቂያ ፡ ትኾናለች ፤ እነዚህም ፡ አሕዛብ ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡
ይገዛሉ ።

12 ፤ ሰባው ፡ ዓመትም ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፥ የባቢሎንን ፡ ንጉሥና ፡ ያንን ፡ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ኀጢአታቸው ፡
እቀጣለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የከለዳውያንንም ፡ ምድር ፡ ለዘለዓለም ፡ ባድማ ፡ አደርጋታለኹ ።

13 ፤ በርሷም ፡ ላይ ፡ የተናገርኹትን ፡ ቃሌን ፡ ኹሉ ፥ ማለት ፡ ኤርምያስ ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡
የተናገረውን ፡ በዚች ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ ኹሉ ፥ በዚያች ፡ ምድር ፡ አመጣለኹ ።

14 ፤ ብዙ ፡ አሕዛብና ፡ ታላላቆች ፡ ነገሥታት ፡ እነርሱን ፡ ያስገዟቸዋል ፤ እኔም ፡ እንደ ፡ አደራረጋቸውና ፡ እንደ ፡
እጃቸው ፡ ሥራ ፡ እከፍላቸዋለኹ ።

15 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይለኛል ፦ የዚህን ፡ ቍጣ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጽዋ ፡ ከእጄ ፡ውሰድ ፡
አንተንም ፡ የምሰድባቸውን ፡ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ አጠጣቸው ።

16 ፤ ከምሰድባቸውም ፡ ሰይፍ ፡ የተነሣ ፡ ይጠጣሉ ፡ ይወላገዱማል ፡ ያብዳሉም ።

17 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ ጽዋውን ፡ ወሰድኹ ፥ እግዚአብሔርም ፡ እኔን ፡ የሰደደባቸውን ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡
አጠጣኋቸው ።

18 ፤ ዛሬ ፡ እንደ ኾነው ፡ ኹሉ ፡ ባድማና ፡ መደነቂያ ፡ ማፏጫም ፡ ርግማንም ፡ ኣደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ኢየሩሳሌምንና ፡
የይሁዳን ፡ ከተማዎች ፡ ነገሥታቷንም ፡ አለቃዎቿንም ፡ አጠጣኋቸው ።

19 ፤ የግብጽንም ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖንን ፡ ባሪያዎቹንም ፡ አለቃዎቹንም ፡ ሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፥

20 ፤ የተደባለቀውንም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ የዖፅ ፡ ምድር ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፥ የፍልስጥኤም ፡ ምድር ፡ ነገሥታትንም ፡
ኹሉ ፡ አስቀሎናንም ፡ ጋዛንም ፡ ዐቃሮንንም ፡ የአዞጦንንም ፡ ቅሬታ ፥

21 ፤ ኤዶምያስንም ፥ ሞዐብንም ፥ የዐሞንም ፡ ልጆች ፥

22 ፤ የጢሮስን ፡ ነገሥታትም ፡ ኹሉ ፥ የሲዶናን ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፥ በባሕር ፡ ማዶ ፡ ያለች ፡ የደሴት ፡ ነገሥታትንም ፥

23 ፤ ድዳንንም ፥ ቴማንንም ፥ ቡዝንም ፥ ጠጕራቸውንም ፡ የሚቈርጡትን ፡ ኹሉ ፥

24 ፤ የዐረብ ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሚቀመጡ ፡ የድብልቅ ፡ ሕዝብ ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፥

25 ፤ የዘምሪ ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፥ የዔላም ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፥

26 ፤ የሜዶን ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፥ የቀረቡና ፡ የራቁ ፥ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ የሰሜን ፡ ነገሥታትንም ፡
ኹሉ ፥ በምድር ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታትንም ፡ ኹሉ ፡ አጠጣኋቸው ፤ የሼሻክም ፡ ንጉሥ ፡ ከነርሱ ፡



www.ethiopianorthodox.org

በኋላ ፡ ይጠጣል ።

27 ፤ አንተም ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በመካከላችኹ ፡ ከምሰደው ፡ ሰይፍ ፡ የተነሣ ፡ ጠጡ ፥ ስከሩም ፥ አስታውኩም ፡ ውደቁም ፥ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ አትነሡም ፡ በላቸው ።

28 ፤ ይጠጡም ፡ ዘንድ ፡ ጽዋውን ፡ ከእጅኽ ፡ ለመቀበል ፡ እንቢ ፡ ቢሉ ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ፈጽማችኹ ፡ ትጠጣላችኹ ፡ በላቸው ።

29 ፤ እንሆ ፥ ስሜ ፡ የተጠራባትን ፡ ከተማ ፡ አስጨንቃት ፡ ዘንድ ፡ እዠምራለኹ ፤ በእውኑ ፡ እናንተ ፡ ያልተቀጣችኹ ፡ ትኾናላችኹን ፡ በምድር ፡ በሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሰይፍን ፡ እጠራለኹና ፡ ያለቅጣት ፡ አትቀሩም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

30 ፤ ስለዚህ ፥ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ትንቢት ፡ ትናገርባቸዋለኽ ፥ እንዲህም ፡ ትላቸዋለኽ ፦ እግዚአብሔር ፡ በላይ ፡ ኾኖ ፡ ይጮኻል ፥ በቅዱስ ፡ ማደሪያውም ፡ ኾኖ ፡ ድምፁን ፡ ያሰማል ፤ በበረቱ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ይጮኻል ፥ ወይንም ፡ እንደሚጠምቁ ፡ በምድር ፡ በሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይጮኻል ።

31 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ክርክር ፡ አለውና ፡ ድምፅ ፡ እስከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ይደርሳል ፤ ከሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ይፋረዳል ፥ ኀጢአተኛዎችንም ፡ ለሰይፍ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

32 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከሕዝብ ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፡ ይወጣል ፥ ጽኑም ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ይነሣል ።

33 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ግዳዮች ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ ዠምሮ ፡ እስከምድር ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ይኾናሉ ፤ አይለቀስላቸውም ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ ይኾናሉ ፡ እንጂ ፡ አይከማቹም ፡ አይቀበሩምም ።

34 ፤ ትታረዱና ፡ ትበተኑ ፡ ዘንድ ፡ ቀናችኹ ፡ ደርሷልና ፥ እንደ ፡ ተወደደም ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ትወድቃላችኹና ፡ እናንተ ፡ እረኛዎች ፥ አልቅሱ ፡ ጩኹም ፤ እናንተ ፡ የመንጋ ፡ አውራዎች ፥ በዐመድ ፡ ውስጥ ፡ ተንከባለሉ ።

35 ፤ ሽሽትም ፡ ከእረኛዎች ፡ ማምለጥም ፡ ከመንጋ ፡ አውራዎች ፡ ይጠፋል ።

36 ፤ እግዚአብሔር ፡ ማሰማሪያቸውን ፡ አጥፍቷልና ፥ የእረኛዎች ፡ ጩኸት ፡ ድምፅ ፡ የመንጋ ፡ አውራዎችም ፡ ልቅሶ ፡ ኾኗል ።

37 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ የተነሣ ፡ የሰላም ፡ በረት ፡ ፈርሷል ።

38 ፤ እንደ ፡ አንበሳ ፡ መደቡን ፡ ለቋል ፤ ካስጨናቂውም ፡ ሰይፍና ፡ ከጽኑ ፡ ቍጣው ፡ የተነሣ ፡ ምድራቸው ፡ ባድማ ፡ ኾናለችና ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ።

ምዕራፍ ፡ 26 ፤

1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ መንግሥት ፡ መዠመሪያ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ መጣ ።

2 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ቁም ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይሰግዱ ፡ ዘንድ ፡ ለሚመጡት ፡ ለይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ትነግራቸው ፡ ዘንድ ፡ ያዘዝኹኽን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ተናገራቸው ፤ አንዲትም ፡ ቃል ፡ አታጕድል ።

3 ፤ ምናልባት ፡ ይሰሙ ፥ ከክፉ ፡ መንገዳቸውም ፡ ይመለሱ ፡ ይኾናል ፤ እኔም ፡ ስለሥራቸው ፡ ክፋት ፡ ያሰብኹባቸውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እተዋለኹ ።

4 ፤ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በፊታችኹ ፡ በሰጠኹት ፡ ሕጌ ፡ ትኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ባትሰሙኝ ፥

5 ፤ ያልሰማችኹትን ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ የላክኋቸውን ፡ የባሪያዎቼን ፡ የነቢያትን ፡ ቃል ፡ ባትሰሙ ፥

6 ፤ ይህን ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ሴሎ ፡ አደርገዋለኹ ፥ ይህችንም ፡ ከተማ ፡ ለምድር ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ርግማን ፡



www.ethiopianorthodox.org

አደርጋታለኹ ።

7 ፤ ካህናቱም ፡ ነቢያቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ኤርምያስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሲናገር ፡ ሰሙ ።

8 ፤ ኤርምያስም ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ካህናትና ፡
ነቢያት ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡— ሞትን ፡ ትሞታለኽ ።

9 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡— ይህ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ሴሎ ፡ ይኾናል ፥ ይህችም ፡ ከተማ ፡ ባድማና ፡ ወና ፡ ትኾናለች ፡
ብለኽ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትንቢት ፡ ተናገርኽ ፡ ብለው ፡ ያዙት ። ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡
በኤርምያስ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ ነበር ።

10 ፤ የይሁዳም ፡ አለቃዎች ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከንጉሥ ፡ ቤት ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወጡ ፥ በዐዲሱም ፡
በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ መግቢያ ፡ ተቀመጡ ።

11 ፤ ካህናቱና ፡ ነቢያቱም ፡ ለአለቃዎቹና ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡— በጆሯችኹ ፡ እንደ ፡ ሰማችኹ ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡
ትንቢት ፡ ተናግሯልና ፥ ይህ ፡ ሰው ፡ ሞት ፡ የሚገባው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ።

12 ፤ ኤርምያስም ፡ ለአለቃዎችና ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡— በሰማችኹት ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በዚች ፡
ቤትና ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልኮኛል ።

13 ፤ አኹንም ፡ መንገዳችኹንና ፡ ሥራችኹን ፡ አሳምሩ ፥ የአምላካችኹንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ስሙ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የተናገረባችኹን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ይተዋል ።

14 ፤ እኔ ፡ ግን ፥ እንሆ ፥ በእጃችኹ ፡ ነኝ ፤ በዐይናችኹ ፡ መልካምና ፡ ቅን ፡ የመሰለውን ፡ አድርጉብኝ ።

15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በጆሯችኹ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡
ልኮኛልና ፥ ብትገድሉኝ ፡ ንጹሕ ፡ ደምን ፡ በራሳችኹና ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ በሚኖሩባትም ፡ ላይ ፡ እንድታመጡ ፡ በርግጥ ፡
ዕወቁ ።

16 ፤ አለቃዎቹና ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ለካህናትና ፡ ለነቢያት ፡— ይህ ፡ ሰው ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡
ተናግሮናልና ፥ ሞት ፡ አይገባውም ፡ አሉ ።

17 ፤ ከአገሩ ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተው ፡ ለሕዝቡ ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ።

18 ፤ ሞሬታዊው ፡ ሚክያስ ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሕዝቅያስ ፡ ዘመን ፡ ነቢይ ፡ ነበረ ፤ ለይሁዳም ፡ ሕዝብ ፡
ኹሉ ፡— የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ጽዮን ፡ እንደ ፡ ዕርሻ ፡ ትታረሳለች ፥ ኢየሩሳሌም ፡
የፍርስራሽ ፡ ክምር ፡ ትኾናለች ፥ የቤቱም ፡ ተራራ ፡ እንደ ፡ዱር ፡ ከፍታ ፡ ይኾናል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

19 ፤ በእውኑ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስና ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ገደሉትን ፡ በእውኑ ፡ እግዚአብሔርን ፡
አልፈሩምን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ አልተማለሉምን ፡ እግዚአብሔርስ ፡ የተናገረባቸውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡
አይተውምን ፡ እኛም ፡ በነፍሳችን ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ክፋት ፡ እናደርጋለን ።

20 ፤ ደግሞም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ትንቢት ፡ የተናገረ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፡ የቂርያትይዓሪም ፡
ሰው ፥ የሸማያ ፡ ልጅ ፥ኦርዮ ፡ ይባል ፡ ነበር ፤ በዚችም ፡ ከተማ ፡ በዚችም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ኤርምያስ ፡ ቃል ፡
ኹሉ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ።

21 ፤ ንጉሡም ፡ ኢዮአቄም ፡ ኀያላኑም ፡ ኹሉ ፡ አለቃዎቹም ፡ ኹሉ ፡ ቃሉን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ሊገድለው ፡
ፈለገ ፤ ኦርዮም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፈርቶ ፡ ሸሸ ፡ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ገባ ።

22 ፤ ንጉሡም ፡ ኢዮአቄም ፡ የዓክቦርን ፡ ልጅ ፡ ኤልናታንን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሌላዎችን ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡
ላካቸው ፤

23 ፤ ከግብጽም ፡ ኦርዮን ፡ አውጥተው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ኢዮአቄም ፡ ይዘውት ፡ መጡ ፤ ርሱም ፡ በሰይፍ ፡
ገደለው ፡ ሬሳውንም ፡ ክቡራን ፡ ባልኾኑ ፡ ሰዎች ፡ መቃብር ፡ ጣለው ።

24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሕዝቡ ፡ እጅ ፡ እንዳይሰጥና ፡ እንዳይገድሉት ፡ የሳፋን ፡ ልጅ ፡ የአኪቃም ፡ እጅ ፡ ከኤርምያስ ፡ ጋራ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ነበረች ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ።

ምዕራፍ ፡ 27 ፤

1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ መንግሥት ፡ መዠመሪያ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጣ ።

2 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይለኛል ፦ እስራትና ፡ ቀንበር ፡ ሥራ ፡ በዐንገትኽም ፡ ላይ ፡ አድርግ ፤

3 ፤ ወደይሁዳ ፡ ንጉሥም ፡ ወደ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በመጡት ፡ መልእክተኛዎች ፡ እጅ ፡ ወደኤዶምያስ ፡ ንጉሥ ፡ ወደሞዐብም ፡ ንጉሥ ፡ ወደዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ ወደጢሮስም ፡ ንጉሥ ፡ ወደሲዶናም ፡ ንጉሥ ፡ ላካቸው ።

4 ፤ ለጌታዎቻቸውም ፡ እንዲነግሩ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ እዘዛቸው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለጌታዎቻችኹ ፡ እንዲህ ፡ በሉ ።

5 ፤ ምድሪቱን ፡ በምድርም ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎችንና ፡ እንስሳዎችን ፡ በታላቅ ፡ ኀይሌና ፡ በተዘረጋችው ፡ ክንዴ ፡ ፈጥሬያለኹ ፤ ለዐይኔም ፡ መልካም ፡ ለኾነው ፡ እሰጣታለኹ ።

6 ፤ አኹንም ፡ እነዚህን ፡ ምድሮች ፡ ኹሉ ፡ ለባሪያዬ ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነጾር ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቻለኹ ፤ ይገዙለትም ፡ ዘንድ ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊትን ፡ ደግሞ ፡ ሰጥቼዋለኹ ።

7 ፤ የገዛ ፡ ራሱም ፡ ምድር ፡ ጊዜ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ለርሱና ፡ ለልጁ ፡ ለልጅ ፡ ልጁም ፡ ይገዛሉ ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብዙ ፡ አሕዛብና ፡ ታላላቆች ፡ ነገሥታት ፡ ርሱን ፡ ያስገዙታል ።

8 ፤ ለባቢሎን ፡ ንጉሥም ፡ ለናቡከደነጾር ፡ የማይገዛውን ፥ ከባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ቀንበር ፡ በታች ፡ ዐንገቱን ፡ ዝቅ ፡ የማያደርገውን ፡ ሕዝብና ፡ መንግሥት ፥ ያን ፡ ሕዝብ ፡ በእጁ ፡ እስካጠፋው ፡ ድረስ ፥ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ እቀጣለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

9 ፤ እናንተ ፡ ግን ፦ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አትገዙም ፡ የሚሏችኹን ፡ ነቢያታችኹንና ፡ ሟርተኛዎቻችኹን ፥ ሕልም ፡ ዐላሚዎቻችኹንና ፡ ቃላተኛዎቻችኹን ፡ መተተኛዎቻችኹንም ፡ አትስሙ ፤

10 ፤ ከምድራችኹ ፡ እንዲያርቋችኹ ፥ እኔም ፡ እንዳሳድዳችኹ ፡ እናንተም ፡ እንድትጠፉ ፡ ሐሰተኛ ፡ ትንቢትን ፡ ይናገሩላችኋልና ።

11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ቀንበር ፡ በታች ፡ ዐንገቱን ፡ ዝቅ ፡ የሚያደርገውንና ፡ የሚገዛለትን ፡ ሕዝብ ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ እተወዋለኹ ፤ እነርሱም ፡ ያርሷታል ፡ ይቀመጡባትማል ።

12 ፤ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ለሴዴቅያስም ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ተናገርኹ ፦ ከባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ቀንበር ፡ በታች ፡ ዐንገታችኹን ፡ ዝቅ ፡ አድርጉ ፥ ለርሱና ፡ ለሕዝቡም ፡ ተገዙላቸው ፥ በሕይወትም ፡ ኑሩ ።

13 ፤ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ስለ ፡ አለ ፡ ሕዝብ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፥ አንተና ፡ ሕዝብኽ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ ለምን ፡ ትሞታላችኹ ፧

14 ፤ ሐሰተኛን ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩላችኋልና ። ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አትገዙም ፡ የሚሏችኹን ፡ የነቢያትን ፡ ቃል ፡ አትስሙ ።

15 ፤ እኔ ፡ አልላክኋቸውምና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እኔ ፡ እንዳሳድዳችኹ ፥ እናንተና ፡ ትንቢት ፡ የሚናገሩላችኹ ፡ ነቢያትም ፡ እንድትጠፉ ፡ በስሜ ፡ ሐሰተኛ ፡ ትንቢትን ፡ ይናገራሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

16 ፤ ለካህናትም ፡ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ተናገርኹ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሐሰተኛውን ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩላችኋልና ፦ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ከባቢሎን ፡ ይመለሳል ፡ የሚሏችኹን ፡ የነቢያታችኹን ፡ ቃል ፡ አትስሙ ።

17 ፤ እነርሱም ፡ አትስሙ ፤ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ተገዙ ፡ በሕይወትም ፡ ኑሩ ። ይህችስ ፡ ከተማ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ባድማ ፡ ትኾናለች ፧



www.ethiopianorthodox.org

18 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ነቢያት ፡ ቢኾኑ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ቢገኝ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የቀረችው ፡ ዕቃ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ እንዳትኼድ ፡ ወደሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይማለሉ ፡፡

19-20 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአቄምን ፡ ልጅ ፡ ኢኮንያንንና ፡ የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ከበርቴዎች ፡ ኹሉ ፡ ማርኮ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ባፈለሳቸው ፡ ጊዜ ፡ ስላልወሰዳቸው ፡ ዐምዶች ፡ ስለ ፡ ኵሬውም ፡ ስለ ፡ መቀመጫዎቹም ፡ በዚችም ፡ ከተማ ፡ ስለቀረች ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፤

21 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ስለቀረችው ፡ ዕቃ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

22 ፤ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ትወሰዳለች ፡ እስከምጐበኛትም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ትኖራለች ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ አወጣታለኹ ፡ ወደዚህም ፡ ስፍራ ፡ እመልሳታለኹ ፡፡

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ፡፡

ምዕራፍ ፡ 28 ፤

1 ፤ በዚያም ፡ ዓመት ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሴዴቅያስ ፡ መንግሥት ፡ መጀመሪያ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ በዐምስተኛው ፡ ወር ፡ ነቢዩ ፡ የገባዖን ፡ ሰው ፡ የዓዙር ፡ ልጅ ፡ ሐናንያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በካህናትና ፡ በሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረኝ ፡፡

2 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ይናገራል ፡፡ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ ቀንበር ፡ ሰብሬያለኹ ፡፡

3 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ከዚች ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ የወሰዳትን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ በኹለት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ወደዚች ፡ ስፍራ ፡ እመልሳታለኹ ፤

4 ፤ ወደ ፡ ባቢሎንም ፡ የኼዱትን ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአቄምን ፡ ልጅ ፡ ኢኮንያንንና ፡ የይሁዳን ፡ ምርኮ ፡ ኹሉ ፡ ወደዚች ፡ ስፍራ ፡ እመልሳቸዋለኹ ፤ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ ቀንበር ፡ እሰብራለኹና ፡፡

5 ፤ ነቢዩ ፡ ኤርምያስም ፡ በካህናቱና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በቆሙት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ለነቢዩ ፡ ለሐናንያ ፡ ተናገረ ፡፡

6 ፤ ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ አሜን ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ያድርግ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ምርኮውንም ፡ ኹሉ ፡ ከባቢሎን ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ በመመለስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተናገርኸውን ፡ ትንቢት ፡ ይፈጽም ፡፡

7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጆሮኽና ፡ በሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ጆሮ ፡ የምናገረውን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ስማ ፤

8 ፤ ከጥንት ፡ ከእኔና ፡ ከአንተ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ነቢያት ፡ በብዙ ፡ አገርና ፡ በታላላቅ ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሰልፍና ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ቸነፈርም ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ፡፡

9 ፤ ስለ ፡ ሰላም ፡ የተናገረ ፡ ነቢይ ፥ የነቢዩ ፡ ቃል ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ እግዚአብሔር ፡ በእውነት ፡ የሰደደው ፡ ነቢይ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይታወቃል ፡፡

10 ፤ ነቢዩም ፡ ሐናንያ ፡ ቀንበሩን ፡ ከነቢዩ ፡ ከኤርምያስ ፡ ዐንገት ፡ ወስዶ ፡ ሰበረው ፡፡

11 ፤ ሐናንያም ፡ በሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንዲሁ ፡ በኹለት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ የናቡከደነጾርን ፡ ቀንበር ፡ ከአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ዐንገት ፡ እሰብራለኹ ፡ አለ ፡፡ ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፡ መንገዱን ፡ ኼደ ፡፡

12 ፤ ነቢዩም ፡ ሐናንያ ፡ ቀንበሩን ፡ ከነቢዩ ፡ ከኤርምያስ ፡ ዐንገት ፡ ከሰበረ ፡ በኋላ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

13 ፤ ኺድ ፥ ለሐናንያ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገረው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አንተ ፡ የዕንጨትን ፡ ቀንበር ፡



www.ethiopianorthodox.org

ሰብረኻል ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ የብረትን ፡ ቀንበር ፡ እሠራለኹ ።

14 ፤ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነጾር ፡
ይገዙለት ፡ ዘንድ ፡ የብረትን ፡ ቀንበር ፡ በእነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ዐንገት ፡ ላይ ፡ አድርጌያለኹ ፤ እነርሱም ፡
ይገዙለታል ፥ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፡ ደግሞ ፡ ሰጥቼዋለኹ ።

15 ፤ ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢዩን ፡ ሐናንያን ፦ ሐናንያ ፡ ሆይ ፥ ስማ ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በሐሰት ፡ እንዲታመን ፡
አድርገኻል ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላከኽም ።

16 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ከምድር ፡ ላይ ፡ እሰድኻለኹ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡
ዐመፅን ፡ ተናግረኻልና ፥ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ትሞታለኽ ፡ አለው ።

17 ፤ ነቢዩም ፡ ሐናንያ ፡ በዚያው ፡ ዓመት ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ሞተ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ።

ምዕራፍ ፡ 29 ፤

1 ፤ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ወደተረፉት ፡ የምርኮ ፡ ሽማግሌዎች ፥ ወደ ፡ ካህናቱም ፥ ወደ ፡ ነቢያቱም ፥ ናቡከደነጾር ፡
ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ማርኮ ፡ ወዳፈለሰውም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የላከው ፡ የደብዳቤው ፡ ቃል ፡
ይህ ፡ ነው ።

2 ፤ ይህም ፡ የኾነው ፡ ንጉሡ ፡ ኢኮንያን ፣ እናቱም ፡ እቴጌዪቱ ፣ ጃን ፡ ደረባዎቹም ፣ የይሁዳና ፡ የኢየሩሳሌምም ፡
አለቃዎች ፣ ጠራቢዎችና ፡ ብረት ፡ ሠራተኛዎችም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

3 ፤ ኤርምያስ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ በላካቸው ፡
በሳፋን ፡ ልጅ ፡ በኤልዓሣና ፡ በኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡ በገማርያ ፡ እጅ ፡ ደብዳቤውን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ላከው ።

4 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ላስማረክኋቸው ፡
ምርኮኛዎች ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

5 ፤ ቤት ፡ ሥርታችኹ ፡ ተቀመጡ ፥ አታክልትም ፡ ተክላችኹ ፡ ፍሬዋን ፡ ብሉ ፤

6 ፤ ተጋቡ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችንም ፡ ውለዱ ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹንም ፡ አጋቡ ፥ እነርሱም ፡
ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ልጆች ፡ ይውለዱ ፤ ከዚያም ፡ ተባዙ ፡ ጥቂቶችም ፡ አትኹኑ ።

7 ፤ በርሷ ፡ ሰላም ፡ ሰላም ፡ ይኾንላችኋልና ፥ ወደ ፡ ርሷ ፡ ላስማርክኋችኹ ፡ ከተማ ፡ ሰላምን ፡ ፈልጉ ፥ ስለ ፡ ርሷም ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልዩ ።

8 ፤ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ በመካከላችኹ ፡ ያሉት ፡
ነቢያታችኹና ፡ ሟርተኛዎቻችኹ ፡ አያታሏችኹ ፥ እናንተም ፡ የምታልሙትን ፡ ሕልም ፡ አትስሙ ።

9 ፤ በስሜ ፡ ሐሰተኛ ፡ ትንቢትን ፡ ይናገሩላችኋልና ፤ እኔም ፡ አላክኋቸውም ።

10 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ሰባው ፡ ዓመት ፡ በባቢሎን ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ እጐበኛችኋለኹ ፥ ወደዚህም ፡
ስፍራ ፡ እመልሳችኹ ፡ ዘንድ ፡ መልካሚቱን ፡ ቃሌን ፡ እፈጽምላችኋለኹ ።

11 ፤ ለእናንተ ፡ የማስባትን ፡ ዐሳብ ፡ እኔ ፡ ዐውቃለኹ ፤ ፍጻሜና ፡ ተስፋ ፡ እሰጣችኹ ፡ ዘንድ ፡ የሰላም ፡ ዐሳብ ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ የክፉ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

12 ፤ እናንተም ፡ ትጠሩኛላችኹ ፥ ኼዳችኹም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ትጸልያላችኹ ፥ እኔም ፡ እሰማችኋለኹ ።

13 ፤ እናንተ ፡ ትሹኛላችኹ ፥ በፍጹም ፡ ልባችኹም ፡ ከሻችኹኝ ፡ ታገኙኛላችኹ ።

14 ፤ ከእናንተም ፡ ዘንድ ፡ እገኛለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ምርኳችኹንም ፡ እመልሳለኹ ፥ ከአሕዛብም ፡ ኹሉ ፡
ዘንድ ፡ እናንተንም ፡ ካሳደድኹበት ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ እሰበስባችኋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እናንተንም ፡ ለምርኮ ፡
ወዳፈለስኹበት ፡ ስፍራ ፡ እመልሳችኋለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

15 ፤ እናንተም ፦ እግዚአብሔር ፡ በባቢሎን ፡ ነቢያትን ፡ አስነሥቶልናል ፡ ብላችኋልና ፤

16 ፤ እግዚአብሔር ፡ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ስለተቀመጠ ፡ ንጉሥ ፡ ከእናንተም ፡ ጋራ ፡ ስላልተማረኩት ፡
ወንድሞቻችኹ ፥ በዚች ፡ ከተማ ፡ ስለሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ዅሉ ፥ እንዲህ ፡ ይላልና ፦

17 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ፥ ሰይፍንና ፡ ራብን ፡ ቸነፈርንም ፡
እሰድባቸዋለኹ ፥ ከክፋቱም ፡ የተነሣ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ እንደማይቻል ፡ እንደ ፡ ክፉ ፡ በለስ ፡ አደርጋቸዋለኹ ።

18 ፤ በሰይፍም ፡ በራብም ፡ በቸነፈርም ፡ አሳዳድዳቸዋለኹ ፥ ባሳደድኹባቸውም ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ዘንድ ፡ ለጥላቻና ፡
ለመደነቂያ ፡ ለማፏጨም ፡ ለመሰደቢያም ፡ እንዲኾኑ ፡ በምድር ፡ መንግሥታት ፡ ዅሉ ፡ ዘንድ ፡ ለመበተን ፡ አሳልፌ ፡
እሰጣቸዋለኹ ።

19 ፤ ይህም ፡ የኾነው ፡ ቃሌን ፡ ስላልሰሙ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ ባሪያዎቼን ፡ ነቢያትን ፡
ወደ ፡ እነርሱ ፡ ሰድጃለኹና ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ አልሰማችኹም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

20 ፤ ስለዚህ ፥ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ የሰደድኋችኹ ፡ ምርኮኞዎች ፡ ዅሉ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ስሙ ።

21 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በስሜ ፡ ሐሰተኛ ፡ ትንቢትን ፡ ስለሚናገሩላችኹ ፡ ስለቆላያ ፡
ልጅ ፡ ስለ ፡ አክአብና ፡ ስለመዕሴያ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ሴዴቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ፥ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡
በናቡከደነጾር ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹ ፥ በዐይኖቻችኹም ፡ ፊት ፡ ይገድላቸዋል ።

22 ፤ ከነርሱም ፡ የተነሣ ፡ በባቢሎን ፡ ያሉ ፡ የይሁዳ ፡ ምርኮኞዎች ፡ ዅሉ ፦ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በእሳት ፡ እንደ ፡
ጠበሳቸው ፡ እንደ ፡ ሴዴቅያስና ፡ እንደ ፡ አክአብ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያድርግኽ ፡ የምትባል ፡ ርግማንን ፡ ያነሣሉ ፤ እኔም ፡
ዐውቃለኹ ፡ ምስክርም ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

23 ፤ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ስንፍና ፡ አድርገዋልና ፥ ከባልንጀራዎቻቸውም ፡ ሚስቶች ፡ ጋራ ፡
አመንዝረዋልና ፥ ያላዘዝኋቸውንም ፡ ቃል ፡ በስሜ ፡ በሐሰት ፡ ተናግረዋልና ።

24 ፤ ለኔሔላማዊው ፡ ለሸማያ ፡ እንዲህ ፡ በል ፦

25 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በኢየሩሳሌም ፡ ወዳለው ፡ ሕዝብ ፡
ዅሉ ፥ ወደ ፡ ካህኑም ፡ ወደመዕሴያ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሶፎንያስ ፥ ወደ ፡ ካህናቱም ፡ ዅሉ ፡ ደብዳቤዎችን ፡ በስምኽ ፡
እንዲህ ፡ ስትል ፡ ልከኻል ።

26 ፤ እያበደ ፡ ትንቢት ፡ የሚናገርን ፡ ሰው ፡ ዅሉ ፡ በእግር ፡ ግንድና ፡ በዛንጅር ፡ ታኖረው ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ቤት ፡ አለቃ ፡ እንድትኾን ፡ እግዚአብሔር ፡ በካህኑ ፡ በዮዳዔ ፡ ፋንታ ፡ ካህን ፡ አድርጎኻል ።

27 ፤ አኹንስ ፡ ትንቢት ፡ ተናጋሪውን ፡ የዓናቶቱን ፡ ሰው ፡ ኤርምያስን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አትዘልፈውም ፧

28 ፤ ርሱ ፦ ምርኮው ፡ የረዘመው ፡ ነውና ፥ ቤት ፡ ሠርታችኹ ፡ ተቀመጡ ፥ አታክልትንም ፡ ተክላችኹ ፡ ፍሬዋን ፡
ብሉ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ልኳልና ።

29 ፤ ካህኑም ፡ ሶፎንያስ ፡ ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ ዦሮ ፡ አነበበው ።

30 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

31 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኔሔላማዊው ፡ ስለ ፡ ሸማያ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ ብለኽ ፡ ወደ ፡ ምርኮኞዎች ፡ ዅሉ ፡ ላክ ። እኔ ፡
ሳልከው ፡ ሸማያ ፡ ትንቢት ፡ ተናግሮላችኋልና ፥ በሐሰትም ፡ እንድትታመኑ ፡ አድርጓችኋልና ፤

32 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ፥ ኔሔላማዊውን ፡ ሸማያንና ፡ ዘሩን ፡ እቀጣለኹ ፤ እኔም ፡
የማደርግላችኹን ፡ መልካሙን ፡ ነገር ፡ የሚያይ ፡ ሰው ፡ በመካከላችኹ ፡ አይኖርላችኹም ፡

_____ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ። _____

ምዕራፍ ፡ 30 ፤

1 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦



www.ethiopianorthodox.org

2 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የነገርኹኽን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በመጽሐፍ ፡ ጻፍ ።

3 ፤ እንሆ ፥ የሕዝቤን ፡ የእስራኤልንና ፡ የይሁዳን ፡ ምርኮ ፡ የምመልስባት ፡ ዘመን ፡ ይመጣልና ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ፤ ለአባቶቻቸውም ፡ ወደሰጠኹት ፡ ምድር ፡ እመልሳቸዋለኹ ፥ እነርሱም ፡ ይገዟታል ።

4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እስራኤልና ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

5 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ የሚያስፈራ ፡ ድምፅ ፡ ሰምተናል ፤ የፍርሀት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሰላም ፡ አይደለም ።

6 ፤ ጠይቁ ፥ ወንድ ፡ ይወልድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተመልከቱ ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ወላድ ፡ እጁን ፡ በወገቡ ፡
ላይ ፡ አድርጎ ፡ ፊቱም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ጥቍረት ፡ ተለውጦ ፡ አየኹ ፧

7 ፤ ወዮ! ያ ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፥ ርሱንም ፡ የሚመስል ፡ የለምና ፤ ያ ፡ የያዕቆብ ፡ መከራ ፡ ዘመን ፡ ነው ፥ ነገር ፡
ግን ፥ ከርሱ ፡ ይድናል ።

8 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ቀንበርን ፡ ከዐንገትኽ ፡
እሰብራለኹ ፥ እስራትኽንም ፡ እበጥሳለኹ ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ለሌላ ፡ አትገዛም ፤

9 ፤ ለአምላካቸው ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ለማስነሣላቸው ፡ ለንጉሣቸው ፡ ለዳዊትም ፡ ይገዛሉ ፡ እንጂ ፡ ሌላዎች ፡ አሕዛብ ፡
እንደ ፡ ገና ፡ አይገዟቸውም ።

10 ፤ እንሆ ፥ አንተን ፡ ከሩቅ ፡ ዘርኽንም ፡ ከምርኮ ፡ አገር ፡ አድናለኹና ፡ ባሪያዬ ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ አትፍራ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ፥ አንተም ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ አትደንግጥ ፤ ያዕቆብም ፡ ይመለሳል ፡ ያርፍማል ፡ ተዘልሎም ፡
ይቀመጣል ፤ ማንም ፡ አያስፈራውም ።

11 ፤ አድንኽ ፡ ዘንድ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ አንተንም ፡ የበተንኹባቸውን ፡ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡
ፈጽሜ ፡ አጠፋለኹ ፥ አንተን ፡ ግን ፡ ፈጽሜ ፡ አላጠፋኽም ፤ በመጠን ፡ እቀጣኻለኹ ፥ ያለቅጣትም ፡ ከቶ ፡
አልተውኽም ።

12 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስብራትኽ ፡ የማይፈወስ ፡ ቍስልኽም ፡ ክፉ ፡ ነው ።

13 ፤ ትጠገን ፡ ዘንድ ፡ ክርክርኽን ፡ የሚፈርድልኽ ፡ የለም ፥ ቍስልኽንም ፡ የሚፈውስ ፡ መድኀኒት ፡ የለኽም ።

14 ፤ ውሽማዎችኽ ፡ ኹሉ ፡ረስተውኻል ፡ አይፈልጉኽምም ፤ በደልኽ ፡ ታላቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ኀጢአትኽም ፡ ስለ ፡
በዛ ፥ በጠላት ፡ ማቍሰልና ፡ በጨካኝ ፡ ቅጣት ፡ አቍስዬኻለኹና ።

15 ፤ ሕመምኽ ፡ የማይፈወስ ፡ ኾኗልና ፥ ስለ ፡ ስብራትኽ ፡ ለምን ፡ ትጮኻለኽ ፧ በደልኽ ፡ ታላቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡
ኀጢአትኽም ፡ ስለ ፡ በዛ ፥ ይህን ፡ አድርጌብኻለኹ ።

16 ፤ ስለዚህ ፥ የሚውጡኽ ፡ ኹሉ ፡ ይዋጣሉ ፥ ጠላቶችኽም ፡ ኹላቸው ፡ ይማረካሉ ፤ የዘረፉኽም ፡
ይዘረፋሉ ፥ የበዘበዙኽንም ፡ ኹሉ ፡ ለመበዝበዝ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ።

17 ፤ እኔ ፡ ጤናኽን ፡ እመልስልኻለኹ ፡ ቍስልኽንም ፡ እፈውሳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ማንም ፡
የማይሻት ፥ የተጣለች ፡ ጽዮን ፡ ብለው ፡ ጠርተውሻልና ።

18 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የያዕቆብን ፡ ድንኳን ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፥ ለማደሪያውም ፡
እራራለኹ ፤ ከተማዪቱም ፡ በጕብታዋ ፡ ላይ ፡ ትሠራለች ፥ አዳራሹም ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ የሰው ፡ መኖሪያ ፡ ይኾናል ።

19 ፤ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ የምስጋናና ፡ የዘፋኞች ፡ ድምፅ ፡ ይወጣል ፤ እኔም ፡ አበዛቸዋለኹ ፡ አያንሱምም ፥ እኔም ፡
አከብራቸዋለኹ ፡ ታናሽም ፡ አይኾኑም ።

20 ፤ ልጆቻቸውም ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ይኾናሉ ፥ ማኅበራቸውም ፡ በፊቴ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፤ የሚያስጨንቋቸውንም ፡
ኹሉ ፡ እቀጣለኹ ።

21 ፤ አለቃቸው ፡ ከነርሱ ፡ ውስጥ ፡ ይኾናል ፥ ገዣቸውም ፡ ከመካከላቸው ፡ ይወጣል ፤ እኔ ፡ አቀርበዋለኹ ፡ ርሱም ፡
ይቀርባል ፤ ይህስ ፡ ባይኾን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ለመቅረብ ፡ የሚደፍር ፡ ማን ፡ ነው ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

22 ፤ እናንተም ፡ ሕዝብ ፡ ትኾኑኛላችኹ ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናችኋለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

23 ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፥ ርሱም ፡ ቍጣው ፥ የሚያገለባብጥ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡
ወጥቷል ፤ የዐመፀኛዎችንም ፡ ራስ ፡ ይገለባብጣል ።

24 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ የልቡን ፡ ዐሳብ ፡ ሠርቶ ፡ እስኪፈጽም ፡ ድረስ ፡ አይመለስም ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡
ታስተውሉታላችኹ ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 31 ።

ምዕራፍ ፡ 31 ፤

1 ፤ በዚያን ፡ ዘመን ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ለእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ ዅሉ ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ፡ እነርሱም ፡
ሕዝብ ፡ ይኾኑኛል ።

2 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እስራኤል ፡ ማረፊያ ፡ ሊሻ ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡ ከሰይፍ ፡ የተረፈው ፡ ሕዝብ ፡
በምድረ ፡ በዳ ፡ ሞገስ ፡ አገኘ ።

3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከሩቅ ፡ ተገለጠልኝ ፡ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ በዘለዓለም ፡ ፍቅር ፡
ወድጄሻለኹ ፤ ስለዚህ ፥ በቸርነት ፡ ሳብኹሽ ።

4 ፤ የእስራኤል ፡ ድንግል ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡ ገና ፡ እሠራሻለኹ ፡ አንቺም ፡ ትሠሪያለሽ ፤ እንደ ፡ ገናም ፡ ከበሮሽን ፡
አንሥተሽ ፡ ከዘፋኞች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ዘፈን ፡ ትወጫለሽ ።

5 ፤ እንደ ፡ ገናም ፡ በሰማርያ ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ የወይን ፡ ቦታዎችን ፡ ትተክሊያለሽ ፤ አትክልተኛዎች ፡ ይተክላሉ ፡
በፍሬውም ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

6 ፤ በኤፍሬምም ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ጠባቂዎች ፦ ተነሡ ፥ ወደ ፡ ጽዮን ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንውጣ ፡ ብለው ፡ የሚጮኹበት ፡ ቀን ፡ ይመጣልና ።

7 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ስለ ፡ ያዕቆብ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፡ ስለ ፡ አሕዛብም ፡ አለቃዎች ፡ እልል ፡
በሉ ፤ አውሩ ፥ አመስግኑ ። እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ የእስራኤልን ፡ ቅሬታ ፡ አድኗል ፡ በሉ ።

8 ፤ እንሆ ፥ ከሰሜን ፡ አገር ፡ አመጣቸዋለኹ ፥ ከምድርም ፡ ዳርቻ ፡ እሰበስባቸዋለኹ ፥ በመካከላቸውም ፡ ዕውሩና ፡
ዐንካሳው ፡ ያረገዘችና ፡ የወለደችም ፡ በአንድነት ፤ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ኾነው ፡ ወደዚህ ፡ ይመለሳሉ ።

9 ፤ በልቅሶ ፡ ወጡ ፡ እኔም ፡ በማጽናናት ፡ አመጣቸዋለኹ ፤ በወንዝ ፡ ዳር ፡ በቀን ፡ መንገድ ፡
አስኬዳቸዋለኹ ፥ በርሱም ፡ አይሰናከሉም ፤ እኔ ፡ ለእስራኤል ፡ አባት ፡ ነኝና ፥ ኤፍሬምም ፡ በኵሬ ፡ ነውና ።

10 ፤ አሕዛብ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፥ በሩቅም ፡ ላሉ ፡ ደሴቶች ፡ አውሩና ፦ እስራኤልን ፡ የበተነ ፡ ርሱ ፡
ይሰበስበዋል ፥ እረኛም ፡ መንጋውን ፡ እንደሚጠብቅ ፡ ይጠብቀዋል ፡ በሉ ።

11 ፤ እግዚአብሔር ፡ ያዕቆብን ፡ ተቤዥቶታል ፥ ከበረቱበትም ፡ እጅ ፡ አድኖታል ።

12 ፤ ይመጣሉ ፡ በጽዮንም ፡ ተራራ ፡ እልል ፡ ይላሉ ፤ ወደእግዚአብሔርም ፡ በጎነት ፥ ወደ ፡ እኽልና ፡ ወደ ፡ ወይን ፡
ጠጅ ፡ ወደ ፡ ዘይትም ፥ ወደ ፡ በጎችና ፡ ወደ ፡ ላሞች ፡ ይሰበሰባሉ ፤ ነፍሳቸውም ፡ እንደ ፡ ረካች ፡ ገነት ፡
ትኾናለች ፥ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ አያዝኑም ።

13 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ድንግሊቱ ፡ በዘፈን ፡ ደስ ፡ ይላታል ፥ ጕበዛዝቱና ፡ ሽማግሌዎቹም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ደስ ፡
ይላቸዋል ፤ ልቅሷቸውንም ፡ ወደ ፡ ደስታ ፡ እመልሳለኹ ፥ አጽናናቸውማለኹ ፥ ከሐዘናቸውም ፡ ደስ ፡ አሠኛቸዋለኹ ።

14 ፤ የካህናቱንም ፡ ነፍስ ፡ በብዛት ፡ አረካታለኹ ፡ ሕዝቤም ፡ በጎነቴን ፡ ይጠግባል ።

15 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የዋይታና ፡ የመራራ ፡ ልቅሶ ፡ ድምፅ ፡ በራማ ፡ ተሰማ ፤ ራሔል ፡ ስለ ፡ ልጆቿ ፡
አለቀሰች ፤ የሉምና ፡ ስለ ፡ ልጆቿ ፡ መጽናናትን ፡ እንቢ ፡ አለች ።

16 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ድምፅሽን ፡ ከልቅሶ ፡ ዐይንሽንም ፡ ከእንባ ፡ ከልክዪ ፤ ለሥራሽ ፡ ዋጋ ፡
ይኾናልና ፥ ከጠላትም ፡ ምድር ፡ ይመለሳሉ ።

17 ፤ ለፍጻሜሽም ፡ ተስፋ ፡ አለ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ልጆችሽም ፡ ወደ ፡ ዳርቻቸው ፡ ይመለሳሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

18 ፤ ኤፍሬም ፦ ቀጣኸኝ ፡ እኔም ፡ እንዳልተገራ ፡ ወይፈን ፡ ተቀጣኹ ፤ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኬ ፡
ነኽና ፥ መልሰኝ ፡ እኔም ፡ እመለሳለኹ ።

19 ፤ ከተመለስኹ ፡ በኋላ ፡ ተጸጸትኹ ፥ ከተገሠጽኹም ፡ በኋላ ፡ ጭኔን ፡ ጸፋኹ ፤ የብላቴንነቴንም ፡ ስድብ ፡
ተሸክሜያለኹና ፡ ዐፈርኹ ፥ ተዋረድኹም ፡ ብሎ ፡ ሲያለቅስ ፡ ሰማኹ ።

20 ፤ በእውነት ፡ ኤፍሬም ፡ ለእኔ ፡ የከበረ ፡ ልጅ ፡ ነውን ፧ ወይስ ፡ የተወደደ ፡ ሕፃን ፡ ነውን ፧ በርሱ ፡ ላይ ፡ በተናገርኹ ፡
ቍጥር ፡ ዐስበዋለኹ ፤ ስለዚህ ፥ አንዠቴ ፡ ታወከችለት ፥ ርኅራኄም ፡ እራራለታለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

21 ፤ ለራስሽ ፡ የመንገድ ፡ ምልክት ፡ አድርጊ ፥ መንገድንም ፡ የሚመሩ ፡ ዐምዶችን ፡ ትከዪ ፥ ልብሽንም ፡
ወደኼድሽበት ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ጥርጊያው ፡ አቅኚ ፤ አንቺ ፡ የእስራኤል ፡ ድንግል ፡ ሆይ ፥ ተመለሺ ፥ ወደ ፡ እነዚህም ፡
ወደ ፡ ከተማዎችሽ ፡ ተመለሺ ።

22 ፤ አንቺ ፡ ከዳተኛ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ትቅበዘበዢለሽ ፧ እግዚአብሔር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ዐዲስ ፡ ነገርን ፡
ፈጥሯልና ፥ ሴት ፡ ወንድን ፡ ትከባለች ።

23 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፣ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ምርኳቸውን ፡ በመለስኹ ፡ ጊዜ ፡
በይሁዳ ፡ አገር ፡ በከተማዎቿ ። የጽድቅ ፡ ማደሪያ ፡ ሆይ ፥ የቅድስና ፡ ተራራ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ይባርክኽ ፡ የሚልን ፡
ነገር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይናገራሉ ።

24 ፤ በይሁዳ ፡ ከተማዎችና ፡ በአገሩ ፡ ኹሉ ፡ ከገበሬዎችና ፡ መንጋን ፡ ይዘው ፡ ከሚዞሩ ፡ ጋራ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡
ይገኛሉ ።

25 ፤ የደከመችውን ፡ ነፍስ ፡ አርክቻለኹና ፥ ያዘነችውንም ፡ ነፍስ ፡ ኹሉ ፡ አጥግቤያለኹና ።

26 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ነቃኹ ፡ ተመለከትኹም ፥ እንቅልፌም ፡ ጣፋጭ ፡ ኾነልኝ ።

27 ፤ የእስራኤልን ፡ ቤትና ፡ የይሁዳን ፡ ቤት ፡ በሰው ፡ ዘርና ፡ በእንስሳ ፡ ዘር ፡ የምዘራበት ፡
ዘመን ፥ እንሆ ፥ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

28 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ አፈርሳቸውና ፡ ክፉ ፡ አድርግባቸው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተጋኹባቸው ፥ እንዲሁ ፡ እሠራቸውና ፡
እተክላቸው ፡ ዘንድ ፡ እተጋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

29 ፤ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ ዳግመኛ ፡ እንዲህ ፡ አይልም ፦ አባቶች ፡ ጨርቋ ፡ የወይን ፡ ፍሬ ፡ በሉ ፥ የልጆችም ፡
ጥርሶች ፡ ጠረሱ ፤

30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በገዛ ፡ በደሉ ፡ ይሞታል ፤ መራራውን ፡ የወይን ፡ ፍሬ ፡ የሚበላ ፡ ኹሉ ፡ ጥርሶቹ ፡
ይጠርሳሉ ።

31 ፤ እንሆ ፥ ከእስራኤል ፡ ቤትና ፡ ከይሁዳ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ ዐዲስ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የምገባበት ፡ ወራት ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ፤

32 ፤ ከግብጽ ፡ አገር ፡ አወጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እጃቸውን ፡ በያዝኹበት ፡ ቀን ፡ ከአባቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ገባኹት ፡
ያለ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አይደለም ፤ እነርሱ ፡ በኪዳኔ ፡ አልጸኑምና ፥ እኔም ፡ ቸል ፡ አልኋቸው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

33 ፤ ከነዚያ ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ ከእስራኤል ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ የምገባው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይህ ፡ ነውና ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ፤ ሕጌን ፡ በልቡናቸው ፡ አኖራለኹ ፥ በልባቸውም ፡ እጽፈዋለኹ ፤ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ፡
እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑኛል ።

34 ፤ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ባልንጀራውን ፥ እያንዳንዱም ፡ ወንድሙን ፦ እግዚአብሔርን ፡ ዕወቅ ፡ ብሎ ፡
አያስተምርም ፤ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ኹሉ ፡ ያውቁኛልና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። በደላቸውን ፡
እምራቸዋለኹና ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አላስብምና ።

35 ፤ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የሚባል ፥ ፀሓይን ፡ በቀን ፡ የጨረቃንና ፡ የከዋክብትን ፡ ሥርዐት ፡ በሌሊት ፡ ብርሃን ፡
አድርጎ ፡ የሚሰጥ ፥ እንዲተሙም ፡ የባሕርን ፡ ሞገዶች ፡ የሚያናውጥ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦



www.ethiopianorthodox.org

36 ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከፊቴ ፡ ቢወገድ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ የእስራኤል ፡ ዘር ፡ በፊቴ ፡ ሕዝብ ፡
እንዳይኾን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይቀራል ።

37 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰማይ ፡ በላይ ፡ ቢከነዳ ፥ የምድርም ፡ መሠረት ፡ በታች ፡ ቢመረመር ፥ በዚያን ፡
ጊዜ ፡ ስላደረጉት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የእስራኤልን ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ እጥላለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

38 ፤ ከሐናንኤል ፡ ግንብ ፡ ዠምሮ ፡ እስከማእዘኑ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ከተማ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚሠራበት ፡
ዘመን ፥ እንሆ ፥ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

39 ፤ የተለካበትም ፡ ገመድ ፡ ወደጋሬብ ፡ ኰረብታ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይኼዳል ፥ ወደ ፡ ጎዓም ፡ ይዞራል ።

40 ፤ የሬሳም ፡ ሸለቆ ፡ ኹሉ ፡ የዐመድም ፡ ዕርሻ ፡ ኹሉ ፡ እስከቄድሮን ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ እስካለው ፡
እስከፈረስ ፡ በር ፡ ማእዘን ፡ ድረስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ይኾናል ፤ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ለዘለዓለም ፡
አይነቀልም ፡ አይፈርስምም ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 32 ።

ምዕራፍ ፡ 32 ፤

1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሴዴቅያስ ፡ በዐሥረኛው ፡ ዓመት ፥ በናቡከደነጾር ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡
ዓመት ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

2 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሰራዊት ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከቦ ፡ ነበር ፤ ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡
ቤት ፡ በነበረው ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ታስሮ ፡ ነበር ።

3 ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አስጠብቆት ፡ ነበርና ፦ ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ትንቢት ፡
ትናገራለኽ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ይህችን ፡ ከተማ ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡
እሰጣለኹ ፡ ርሱም ፡ ይይዛታል ፤

4 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በእውነት ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ዐልፎ ፡ ይሰጣል ፥ አፍ ፡ ለአፍም ፡
ይናገረዋል ፥ ዐይኑም ፡ ዐይኑን ፡ ያያል ፡ እንጂ ፡ ከከለዳውያን ፡ እጅ ፡ አያመልጥም ፤

5 ፤ ርሱም ፡ ሴዴቅያስን ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ያፈልሰዋል ፥ እኔም ፡ እስክጐበኘው ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ይኖራል ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ፤ ከከለዳውያን ፡ ጋራ ፡ ብትዋጉ ፡ ምንም ፡ አትረቡም ።

6 ፤ ኤርምያስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

7 ፤ እንሆ ፥ የአጎትኽ ፡ የሰሎም ፡ ልጅ ፡ ዐናምኤል ፡ ወዳንተ ፡ መጥቶ ፦ ትገዛው ፡ ዘንድ ፡ መቤዠቱ ፡ የአንተ ፡
ነውና ፥ በዐናቶት ፡ ያለውን ፡ ዕርሻዬን ፡ ግዛ ፡ ይልኻል ።

8 ፤ እንደእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ የአጎቴ ፡ ልጅ ፡ ዐናምኤል ፡ እኔ ፡ ወዳለኹበት ፡ ወደግዞቱ ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡
መጥቶ ፦ በብንያም ፡ አገር ፡ በዐናቶት ፡ ያለውን ፡ ዕርሻዬን ፥ እባክኽ ፥ ግዛ ፤ ርስቱ ፡ የአንተ ፡ ነውና ፥ መቤዠቱም ፡
የአንተ ፡ ነውና ፤ ለአንተ ፡ ግዛው ፡ አለኝ ። ይህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐወቅኹ ።

9 ፤ በዐናቶትም ፡ ያለውን ፡ ዕርሻ ፡ ከአጎቴ ፡ ልጅ ፡ ከዐናምኤል ፡ ገዛኹ ፥ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ሰቅል ፡ ብርም ፡ መዘንኹለት ።

10 ፤ በውሉም ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ፈረምኹ ፡ ዐተምኹትም ፥ ምስክሮችንም ፡ ጠርቼ ፡ ብሩን ፡ በሚዛን ፡ መዘንኹለት ።

11 ፤ የታተመውንና ፡ የተከፈተውን ፡ የውል ፡ ወረቀት ፡ ወሰድኹ ፤

12 ፤ የአጎቴም ፡ ልጅ ፡ ዐናምኤል ፥ የውሉንም ፡ ወረቀት ፡ የፈረሙ ፡ ምስክሮች ፥ በግዞትም ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡
የተቀመጡ ፡ አይሁድ ፡ ኹሉ ፡ እያዩ ፡ የውሉን ፡ ወረቀት ፡ ለመሕሴያ ፡ ልጅ ፡ ለኔርያ ፡ ልጅ ፡ ለባሮክ ፡ ሰጠኹት ።

13 ፤ በፊታቸውም ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ባሮክን ፡ አዘዝኹት ፦

14 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ብዙ ፡ ቀን ፡ ይጠበቁ ፡ ዘንድ ፡
የታተመውንና ፡ የተከፈተውን ፡ ይህን ፡ የውል ፡ ወረቀት ፡ ወስደኽ ፡ በሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ውስጥ ፡ አኑራቸው ።


www.ethiopianorthodox.org

15 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ሰዎች ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ ቤትንና ፡
ዕርሻን ፡ የወይን ፡ ቦታንም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይገዛሉ ።

16 ፤ ለኔርያ ፡ ልጅ ፡ ለባሮክም ፡ የውሉን ፡ ወረቀት ፡ ከሰጠኹት ፡ በኋላ ፥ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ጸለይኹ ።

17 ፤ አቤቱ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ አንተ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በታላቅ ፡ ኀይልኽና ፡ በተዘረጋች ፡
ክንድኽ ፡ ፈጥረኻል ፥ ከአንተም ፡ የሚያቅት ፡ ነገር ፡ የለም ።

18 ፤ ለብዙ ፡ ሺሕ ፡ ምሕረት ፡ ታደርጋለኽ ፥ የአባቶችንም ፡ በደል ፡ ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ በልጆቻቸው ፡ ብብት ፡
ትመልሳለኽ ፤ ስምኽ ፡ ታላቅና ፡ ኀያል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

19 ፤ በምክር ፡ ታላቅ ፡ በሥራም ፡ ብርቱ ፡ ነኽ ፤ ለኹሉም ፡ እንደ ፡ መንገዱና ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ፍሬ ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡
ዐይኖችኽ ፡ በአዳም ፡ ልጆች ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ተገልጠዋል ።

20 ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ምልክትንና ፡ ድንቅን ፡ ነገር ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ደግሞም ፡ በእስራኤልና ፡ በሌላዎች ፡
ሰዎች ፡ መካከል ፡ አድርገኻል ፥ እንደ ፡ ዛሬም ፡ ለአንተ ፡ ስም ፡ አድርገኻል ።

21 ፤ በምልክትና ፡ በድንቅ ፡ ነገር ፥ በብርቱ ፡ እጅና ፡ በተዘረጋች ፡ ክንድ ፡ በታላቅም ፡ ግርማ ፡ ሕዝብኽን ፡ እስራኤልን ፡
ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አወጣኽ ።

22 ፤ ትሰጣቸውም ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ የማልኽላቸውን ፡ ምድር ፥ ወተትና ፡ ማርንም ፡ የምታፈሰውን ፡
ምድር ፥ ሰጠኻቸው ፤

23 ፤ እነርሱም ፡ ገብተው ፡ ወረሷት ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ቃልኽን ፡ አልሰሙም ፥ በሕግኽም ፡ አልኼዱም ፤ ያደርጉም ፡ ዘንድ ፡
ካዘዝኻቸው ፡ ኹሉ ፡ ምንም ፡ አላደረጉም ፤ ስለዚህ ፥ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አመጣኽባቸው ።

24 ፤ እንሆ ፥ የዐፈር ፡ ድልድል ፥ ሊይዟትም ፡ እስከ ፡ ከተማዪቱ ፡ ድረስ ፡ ቀርበዋል ፤ ከሰይፍና ፡ ከራብ ፡ ከቸነፈርም ፡
የተነሣ ፡ ከተማዪቱ ፡ ለሚዋጉት ፡ ለከለዳውያን ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ፥ የተናገርኸውም ፡ ኾኗል ፤ እንሆም ፥ አንተ ፡
ታየዋለኽ ።

25 ፤ አንተም ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፦ ዕርሻውን ፡ በብር ፡ ግዛ ፡ ምስክሮችንም ፡ ጥራ ፡ አልኸኝ ፤ ከተማዪቱ ፡
ግን ፡ ለከለዳውያን ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ።

26 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

27 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ የሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤

28 ፤ በእውኑ ፡ እኔን ፡ የሚያቅተኝ ፡ ነገር ፡ አለን ፥ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ይህችን ፡
ከተማ ፡ ለከለዳውያን ፡ እጅና ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነጾር ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፥ ርሱም ፡ ይይዛታል ።

29 ፤ ይህችን ፡ ከተማ ፡ የሚወጉ ፡ ከለዳውያን ፡ መጥተው ፡ በእሳት ፡ ያነዷታል ፥ ያስቈጡኝም ፡ ዘንድ ፡ በሰገነታቸው ፡
ላይ ፡ ለበዓል ፡ ካጠኑባቸው ፥ ለሌላዎችም ፡ አማልክት ፡ የመጠጥን ፡ ቍርባን ፡ ካፈሰሱባቸው ፡ ቤቶች ፡ ጋራ ፡
ያቃጥሏታል ።

30 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ከታናሽነታቸው ፡ ዠምሮ ፡ በፊቴ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ብቻ ፡
አድርገዋልና ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እኔን ፡ በእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ከማስቈጣት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ አላደረጉምና ።

31 ፤ ከፊቴ ፡ አስወግዳት ፡ ዘንድ ፡ ይህች ፡ ከተማ ፡ ከሠሯት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ቍጣዬንና ፡ መዓቴን ፡
ለማነሣሣት ፡ ኾናለችና ፤

32 ፤ ይህም ፡ እኔን ፡ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፥ እነርሱና ፡ ነገሥታታቸው ፡ አለቃዎቻቸውም ፡ ካህናታቸውም ፡ ነቢያታቸውም ፡
የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚኖሩ ፥ ስላደረጉት ፡ ስለእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ ስለይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ክፋት ፡ ኹሉ ፡
ነው ።

33 ፤ ፊታቸውንም ፡ ሳይኾን ፡ ዠርባቸውን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መለሱ ፤ እኔም ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ ሳስተምራቸው ፡ ተግሣጽን ፡



www.ethiopianorthodox.org

ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ አልሰሙም ።

34 ፤ ያረክሱትም ፡ ዘንድ ፡ ስሜ ፡ በተጠራበት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ርኵሰታቸውን ፡ አኖሩ ።

35 ፤ ይሁዳን ፡ ወደ ፡ ኀጢአት ፡ እንዲያገቡት ፥ ይህንን ፡ ርኵሰት ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፥ እኔ ፡ ያላዘዝኹትንና ፡ በልቤ ፡
ያላሰብኹትን ፡ ነገር ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለሞሎክ ፡ በእሳት ፡ ያሳልፉ ፡ ዘንድ ፡ በሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡
ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የበዓልን ፡ የኰረብታውን ፡ መስገጃዎች ፡ ሠሩ ።

36 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተ ፡ ስለ ፡ ርሷ ፦ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡
ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ፡ ስለምትላት ፡ ከተማ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

37 ፤ እንሆ ፥ በቍጣዬና ፡ በመዓቴ ፡ በታላቅም ፡ መቅሠፍቴ ፡ እነርሱን ፡ ካሳደድኹባት ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡
እሰበስባቸዋለኹ ፥ ወደዚህም ፡ ስፍራ ፡ እመልሳቸዋለኹ ፥ ተዘልለውም ፡ እንዲኖሩ ፡ አደርጋለኹ ፤

38 ፤ እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑኛል ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ።

39 ፤ ለእነርሱም ፡ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ ለልጆቻቸው ፡ መልካም ፡ ይኾንላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዲፈሩኝ ፡ አንድ ፡
ልብና ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ እሰጣቸዋለኹ ።

40 ፤ ለእነርሱም ፡ ከማደርገው ፡ በጎነት ፡ አልመለስም ፡ ስል ፥ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ የዘለዓለምን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
እገባለኹ ፤ ከእኔም ፡ ዘንድ ፡ ፈቀቅ ፡ እንዳይሉ ፡ መፈራቴን ፡ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ አኖራለኹ ።

41 ፤ ለእነርሱም ፡ መልካምን ፡ በማድረግ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ በእውነትም ፡ በፍጹም ፡ ልቤና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሴ ፡ በዚች ፡
ምድር ፡ እተክላቸዋለኹ ።

42 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ይህን ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡
እንዳመጣኹ ፥ እንዲሁ ፡ የተናገርኹላቸውን ፡ በጎነት ፡ ኹሉ ፡ አመጣላቸዋለኹ ።

43 ፤ እናንተም ፦ ያለሰውና ፡ ያለእንስሳ ፡ ያለች ፡ ባድማ ፡ ናት ፥ ለከለዳውያንም ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ፡ በምትሏት ፡
ምድር ፡ ዕርሻን ፡ ይገዛሉ ።

44 ፤ ምርኮኛዎቻቸውንም ፡ እመልሳለኹና ፡ በብንያም ፡ አገር ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ዙሪያ ፡ ባሉ ፡ ስፍራዎች ፥ በይሁዳም ፡
ከተማዎች ፡ በደጋውም ፡ ባሉ ፡ ከተማዎች ፡ በቈላውም ፡ ባሉ ፡ ከተማዎች ፡ በደቡብም ፡ ባሉ ፡ ከተማዎች ፥ ሰዎች ፡
ዕርሻውን ፡ በብር ፡ ይገዛሉ ፡ በውሉም ፡ ወረቀት ፡ ፈርመው ፡ ያትማሉ ፡ ምስክሮችንም ፡ ይጠራሉ ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 33 ።

ምዕራፍ ፡ 33 ፤

1 ፤ ኤርምያስ ፡ ገና ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ታስሮ ፡ ሳለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኹለተኛ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
መጣለት ፦

2 ፤ ስሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ የኾነ ፥ ያደረገው ፡ እግዚአብሔር ፥ ያጸናውም ፡ ዘንድ ፡ የሠራው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፦

3 ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ ጩኽ ፥ እኔም ፡ እመልስልኻለኹ ፤ አንተም ፡ የማታውቀውን ፡ ታላቅና ፡ ኀይለኛ ፡ ነገርን ፡ አሳይኻለኹ ።

4 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዐፈር ፡ ድልድልና ፡ ለምሽግ ፡ ስለ ፡ ፈረሱ ፡ ስለዚች ፡ ከተማ ፡
ቤቶች ፥ ስለይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ ቤቶች ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦

5 ፤ ከለዳውያን ፡ ለመዋጋት ፡ መጥተዋል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በቍጣዬና ፡ በመዓቴ ፡ በገደልኋቸው ፡ ሰዎች ፡ ሬሳዎች ፡
ሊሞሏቸው ፡ ነው ፥ ስለ ፡ ክፋታቸው ፡ ኹሉ ፡ ፊቴን ፡ ከዚች ፡ ከተማ ፡ ሰውሬያለኹና ።

6 ፤ እንሆ ፥ ፈውስንና ፡ መድኀኒትን ፡ አመጣላታለኹ ፥ እፈውሳቸውማለኹ ፤ የሰላምንና ፡ የእውነትን ፡ ብዛት ፡
እገልጥላቸዋለኹ ።

7 ፤ የይሁዳን ፡ ምርኮና ፡ የእስራኤልንም ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፥ ቀድሞም ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ አድርጌ ፡ እሠራቸዋለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

8 ፤ እኔንም ፡ ከበደሉበት ፡ ኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ አነጻቸዋለኹ ፡ እኔንም ፡ የበደሉኝን ፡ ያመፁብኝንም ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ኹሉ ፡ ይቅር ፡ እላለኹ ።

9 ፤ ይህችም ፡ ከተማ ፡ እኔ ፡ የምሠራላቸውን ፡ በጎነት ፡ ኹሉ ፡ በሚሰሙ ፡ እኔም ፡ ስላመጣኹላቸው ፡ በጎነትና ፡ ሰላም ፡ ኹሉ ፡ በሚፈሩና ፡ በሚደነግጡ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ለደስታ ፡ ስም ፡ ለምስጋናም ፡ ለክብርም ፡ ትኾናለች ።

10 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እናንተ ፦ ያለሰውና ፡ ያለእንስሳ ፡ ያለች ፡ ባድማ ፡ ናት ፡ በምትሏት ፡ በዚች ፡ ስፍራ ፥ የሚቀመጥባቸው ፡ በሌላ ፥ ያለሰውና ፡ ያለእንስሳ ፡ ባድማ ፡ በኾኑ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፥

11 ፤ የሐሤት ፡ ድምፅና ፡ የደስታ ፡ ድምፅ ፥ የወንድ ፡ሙሽራ ፡ ድምፅና ፡ የሴት ፡ ሙሽራ ፡ ድምፅ ፦ እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነውና ፥ ምሕረቱም ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ የሰራዊትን ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ የሚሉ ፡ ድምፅ ፥ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የምስጋናን ፡ መሥዋዕት ፡ የሚያመጡት ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይሰማል ። የምድርን ፡ ምርኮ ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አድርጌ ፡ እመልሳለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

12 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ባድማ ፡ ኾኖ ፥ ያለሰውና ፡ ያለእንስሳ ፡ ባለው ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ በከተማዎችም ፡ ኹሉ ፡ መንጋዎቻቸውን ፡ የሚያሳርፉት ፡ የእረኛዎች ፡ መኖሪያ ፡ ይኾናል ።

13 ፤ በደጋው ፡ ላይ ፡ ባሉ ፡ ከተማዎች ፡ በቈላውም ፡ ባሉ ፡ ከተማዎች ፡ በደቡብም ፡ ባሉ ፡ ከተማዎች ፥ በብንያምም ፡ አገር ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ዙሪያ ፡ ባሉ ፡ ስፍራዎች ፥ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ መንጋዎቹ ፡ በተቈጣጣሪው ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ያልፋሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

14 ፤ እነሆ ፥ ስለእስራኤል ፡ ቤትና ፡ ስለይሁዳ ፡ ቤት ፡ የተናገርኹትን ፡ መልካም ፡ ቃል ፡ የምፈጽምበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

15 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ለዳዊት ፡ የጽድቅን ፡ ቍጥቋጥ ፡ አበቅልለታለኹ ፤ ርሱም ፡ ፍርድንና ፡ ጽድቅን ፡ በምድር ፡ ያደርጋል ።

16 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ይሁዳ ፡ ይድናል ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ተዘልላ ፡ ትቀመጣለች ፤ የምትጠራበትም ፡ ስም ፦ እግዚአብሔር ፡ ጽድቃችን ፡ ተብሎ ፡ ነው ።

17 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ በእስራኤል ፡ ቤት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጥ ፡ ሰው ፡ ከዳዊት ፡ ዘንድ ፡ አይታጣም ፤

18 ፤ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ የሚያቀርብ ፡ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፡ የሚያቃጥል ፡ ኹልጊዜም ፡ የሚሠዋ ፡ ሰው ፡ ከሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ ዘንድ ፡ በእኔ ፡ ፊት ፡ አይታጣም ።

19 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

20 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ በወራቱ ፡ እንዳይኾን ፡ የቀን ፡ ቃል ፡ ኪዳኔንና ፡ የሌሊት ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ ማፍረስ ፡ ብትችሉ ፥

21 ፤ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ የሚነግሥ ፡ ልጅ ፡ እንዳይኾንለት ፡ ከባሪያዬ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፥ ከአገልጋዮቼም ፡ ከሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ኪዳኔ ፡ ደግሞ ፡ ይፈርሳል ።

22 ፤ የሰማይን ፡ ሰራዊት ፡ መቍጠር ፡ የባሕርንም ፡ አሸዋ ፡ መስፈር ፡ እንደማይቻል ፥ እንዲሁ ፡ የባሪያዬን ፡ የዳዊትን ፡ ዘርና ፡ የሚያገለግሉኝን ፡ ሌዋውያንን ፡ አበዛለኹ ።

23 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

24 ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፦ እግዚአብሔር ፡ የመረጣቸውን ፡ ኹለቱን ፡ ወገን ፡ ጥሏቸዋል ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ አትመለከትምን ፧ እንዲሁ ፡ በፊታቸው ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሕዝብ ፡ እንዳይኾን ፡ ሕዝቤን ፡ አቃለዋል ።

25 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የቀንና ፡ የሌሊት ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ የሰማይንና ፡ የምድርንም ፡ ሥርዐት ፡ ያላጸናኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥



www.ethiopianorthodox.org

26 ፤ እኔም ፡ ደግሞ ፡ በአብርሃምና ፡ በይሥሐቅ ፡ በያዕቆብም ፡ ዘር ፡ ላይ ፡ ገዢዎች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ከዘሩ ፡
እንዳልወስድ ፥ የያዕቆብንና ፡ የባሪያዬን ፡ የዳዊትን ፡ ዘር ፡ እጥላለኹ ፤ ምርኳቸውን ፡
እመልሳለኹና ፥ እምራቸውማለኹና ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 34 ።

ምዕራፍ ፡ 34 ፤

1 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾርና ፡ ሰራዊቱ ፡ ኹሉ ፡ ከእጁም ፡ ግዛት ፡ በታች ፡ ያሉ ፡ የምድር ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡
አሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ኢየሩሳሌምንና ፡ ከተማዎቿን ፡ ኹሉ ፡ ይወጉ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

2 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ኺድ ፡ ለይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ለሴዴቅያስ ፡ ተናገር ፡
እንዲህም ፡ በለው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ይህችን ፡ ከተማ ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡
እሰጣለኹ ፥ በእሳትም ፡ ያቃጥላታል ፤

3 ፤ አንተም ፡ በርግጥ ፡ ትያዛለኽ ፡ በእጅም ፡ አልፈኽ ፡ ትሰጣለኽ ፡ እንጂ ፡ ከእጁ ፡ አታመልጥም ፤ ዐይንኽም ፡
የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ ዐይን ፡ ታያለች ፥ ርሱም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አፍ ፡ ለአፍ ፡ ይናገራል ፥ ወደ ፡ ባቢሎንም ፡ ትገባለኽ ።

4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስማ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ አንተ ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፦ በሰይፍ ፡ አትሞትም ፥ በሰላም ፡ ትሞታለኽ ፡ እንጂ ፤

5 ፤ ከአንተ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ እንደ ፡ ዱሮ ፡ ነገሥታት ፡ እንደ ፡ አባቶችኽ ፡ መቃጠል ፥ እንዲሁ ፡
ያቃጥሉኻልና ፦ ወየው! ጌታ ፡ ሆይ ፡ እያሉ ፡ ያለቅሱልኻል ፤ እኔ ፡ ቃልን ፡ ተናግሬያለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

6-7 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ሰራዊት ፡ ኢየሩሳሌምንና ፡ የቀሩትን ፡ የይሁዳን ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፥ ከተመሸጉት ፡
ከይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ የተረፉትን ፡ ለኪሶንና ፡ ዓዜቃን ፡ በወጋ ፡ ጊዜ ፥ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ለይሁዳ ፡
ንጉሥ ፡ ለሴዴቅያስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ነገረው ።

8-9 ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ዕብራዊ ፡ የኾነውን ፡ ወንድ ፡ ባሪያውንና ፡ ዕብራዊት ፡ የኾነች ፡ ሴት ፡ ባሪያውን ፡ ሐራነት ፡
እንዲያወጣ ፥ አይሁዳዊ ፡ ወንድሙንም ፡ ማንም ፡ እንዳይገዛ ፥ ስለ ፡ ሐራነታቸው ፡ ዐዋጅ ፡ እንዲነገር ፡ ንጉሡ ፡
ሴዴቅያስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

10 ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ወንድ ፡ ባሪያውንና ፡ ሴት ፡ ባሪያውን ፡ ሐራነት ፡ እንዲያወጣ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ማንም ፡
እንዳይገዛቸው ፡ ወደቃል ፡ ኪዳኑ ፡ የገቡ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉና ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ሰሙ ፥ ሐራነትም ፡ አወጧቸው ።

11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ተመልሰው ፡ ሐራነት ፡ ያወጧቸውን ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ባሪያዎቻቸውን ፡
አስመለሱ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ባሪያዎችም ፡ አድርገው ፡ ገዟቸው ።

12 ፤ ስለዚህ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

13 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አባቶቻችኹን ፡ ከባርነት ፡ ቤት ፡ ከግብጽ ፡ አገር ፡
ባወጣኋቸው ፡ ቀን ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረግኹ ።

14 ፤ ሰባት ፡ ዓመት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፥ የተሸጠላችኹን ፡ ስድስትም ፡ ዓመት ፡ የተገዛላችኹን ፡ ዕብራዊ ፡
ወንድማችኹን ፡ እያንዳንዳችኹ ፡ ሐራነት ፡ ታወጡታላችኹ ፥ እያንዳንዱም ፡ ያወጣዋል ፤ አባቶቻችኹ ፡ ግን ፡
አልሰሙኝም ፡ ጆሯቸውንም ፡ አላዘነበሉም ።

15 ፤ እናንተም ፡ ዛሬ ፡ ተመልሳችኹ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ባልንጀራውን ፡ ሐራነት ፡ ለማውጣት ፡ ዐዋጅ ፡ በመንገር ፡ ለዐይኔ ፡
ደስ ፡ የሚያሠኘን ፡ ነገር ፡ አድርጋችኹ ፡ ነበር ፥ በስሜም ፡ በሚጠራበት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በፊቴ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
አድርጋችኹ ፡ ነበር ።

16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ተመልሳችኹ ፡ ስሜን ፡ አስነቀፋችኹ ፥ እያንዳንዳችኹም ፡ በፈቃዳቸው ፡ እንዲኼዱ ፡ ሐራነት ፡
ያወጣችኋቸውን ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ባሪያዎቻችኹን ፡ አስመለሳችኹ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ባሪያዎችም ፡ እንዲኾኑላችኹ ፡


www.ethiopianorthodox.org

ገዛቸኋቸው ።

17 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ለወንድሙና ፡ ለባልንጀራው ፡ የሐራነት ፡ ዐዋጅ ፡ ለመንገር ፡ እኔን ፡ አልሰማችኹም ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ ለሰይፍና ፡ ለቸነፈር ፡ ለራብም ፡ የሐራነት ፡ ዐዋጅ ፡ እናገርባችኋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ በምድርም ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ እንድትበተኑ ፡ አደርጋችኋለኹ ።

18 ፤ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ የተላለፉትን ፡ ሰዎች ፥ እንቦሳውንም ፡ ቈርጠው ፡ በቍራጮ ፡ መካከል ፡ ባለፉ ፡ ጊዜ ፡ በፊቴ ፡ ያደረጉትን ፡ የቃል ፡ ኪዳንን ፡ ቃል ፡ ያልፈጸሙትን ፥

19 ፤ የይሁዳን ፡ አለቃዎችና ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ አለቃዎች ፡ ጃን ፡ ደረባዎችን ፡ ካህናትንም ፡ በእንቦሳም ፡ ቍራጭ ፡ መካከል ፡ ያለፉትን ፡ የአገሩን ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥

20 ፤ ለጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ነፍሳቸውንም ፡ ለሚሿት ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፤ ሬሳቸውም ፡ ለሰማይ ፡ ወፎችና ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ መብል ፡ ይኾናል ።

21 ፤ የይሁዳንም ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስንና ፡ አለቃዎቹን ፡ ለጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ነፍሳቸውንም ፡ ለሚሿት ፡ እጅ ፡ ከእናንተም ፡ ለተመለሱት ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሰራዊት ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ።

22 ፤ እንሆ ፥ አዛለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ወደዚችም ፡ ከተማ ፡ እመልሳቸዋለኹ ፤ ርሷንም ፡ ይወጋሉ ፡ ይይዟትማል ፡ በእሳትም ፡ ያቃጥሏታል ፤ የይሁዳንም ፡ ከተማዎች ፡ ሰው ፡ የሌለበት ፡ ባድማ ፡ አደርጋቸዋለኹ ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 35 ።

ምዕራፍ ፡ 35 ፤

1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ ዘመን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

2 ፤ ወደሬካባውያን ፡ ቤት ፡ ኼደኽ ፡ ተናገራቸው ፥ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ከጓዳዎቹ ፡ ወደ ፡ አንዲቱ ፡ አግባቸው ፡ የወይን ፡ ጠጅም ፡ አጠጣቸው ።

3 ፤ የከባስንን ፡ ልጅ ፡ የኤርምያስን ፡ ልጅ ፡ ያእዛንያን ፡ ወንድሞቹንም ፡ ልጆቹንም ፡ ኹሉ ፡ የሬካባውያንን ፡ ወገን ፡ ኹሉ ፡ ወሰድኋቸው ፤

4 ፤ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ በበረኛው ፡ በሰሎም ፡ ልጅ ፡ በመዕሴያ ፡ ጓዳ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ በአለቃዎች ፡ ጓዳ ፡ አጠገብ ፡ ወዳለው ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ወደጌዴልያ ፡ ልጅ ፡ ወደሐናን ፡ ልጆች ፡ ጓዳ ፡ አገባኋቸው ።

5 ፤ በሬካባውያንም ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የሞላባቸውን ፡ ማድጋዎችንና ፡ ጽዋዎችን ፡ አኑሬ ፦ የወይኑን ፡ ጠጅ ፡ ጠጡ ፡ አልኋቸው ።

6 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፦ የወይኑን ፡ ጠጅ ፡ አንጠጣም ፥ አባታችን ፡ የሬካብ ፡ ልጅ ፡ ኢዮናዳብ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዞናልና ። እናንተና ፡ ልጆቻችኹ ፡ ለዘለዓለም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አትጠጡ ።

7 ፤ በምትኖሩባት ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ እንድትኖሩ ፥ በዕድሜያችኹ ፡ ሙሉ ፡ በድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ፡ እንጂ ፡ ቤትን ፡ አትሥሩ ፥ ዘርንም ፡ አትዝሩ ፥ ወይንም ፡ አትትከሉ ፥ አንዳችም ፡ አይኹንላችኹ ።

8 ፤ እኛም ፡ የአባታችንን ፡ የሬካብ ፡ ልጅ ፡ የኢዮናዳብን ፡ ቃል ፡ ባዘዘን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ታዝዘናል ፤ እኛም ፡ ሚስቶቻችንም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችንም ፡ ዕድሜያችንን ፡ ሙሉ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አልጠጣንም ፤

9 ፤ የምንቀመጥበትንም ፡ ቤት ፡ አልሠራንም ፤ የወይን ፡ ቦታና ፡ ዕርሻ ፡ ዘርም ፡ የለንም ፤

10 ፤ በድንኳንም ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠናል ፥ ታዝዘናል ፥ አባታችንም ፡ ኢዮናዳብ ፡ ያዘዘንን ፡ ኹሉ ፡ አድርገናል ።

11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ወደዚች ፡ ምድር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፦ ኑ ፡ ከከለዳውያን ፡ ሰራዊትና ፡ ከሶርያ ፡ ሰራዊት ፡ ፊት ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንኺድ ፡ አልን ፤ እንዲሁም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጥን ።

12 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦



www.ethiopianorthodox.org

13 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ኺድና ፡ ለይሁዳ ፡ ሰዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚቀመጡ ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ ቃሌን ፡ ትሰሙ ፡ ዘንድ ፡ ተግሣጽን ፡ አትቀበሉምን ፦ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

14 ፤ የሬካብ ፡ ልጅ ፡ ኢዮናዳብ ፡ ልጆቹ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንዳይጠጡ ፡ ያዘዛቸው ፡ ቃል ፡ ተፈጸመ ፤ ለአባታቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ታዘዋልና ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አይጠጡም ፤ እኔም ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ ተናግሬያችኋለኹ ፤ ተናገርኹ ፥ ኾኖም ፡ አልሰማችኹኝም ።

15 ፤ ደግሞም ፦ እያንዳንዳችኹ ፡ ከክፉ ፡ መንገዳችኹ ፡ ተመለሱ ፥ ሥራችኹንም ፡ አሳምሩ ፥ ታመልኳቸውም ፡ ዘንድ ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ አትከተሉ ፥ ለእናንተና ፡ ለአባቶቻችኹም ፡ በሰጠኹት ፡ ምድር ፡ ትቀመጣላችኹ ፡ እያልኹ ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ ባሪያዎቼን ፡ ነቢያትን ፡ ኹሉ ፡ ልኬባችኹ ፡ ነበር ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ዦሯችኹን ፡ አላዘነበላችኹም ፡ እኔንም ፡ አልሰማችኹኝም ።

16 ፤ የሬካብ ፡ ልጅ ፡ የኢዮናዳብ ፡ ልጆች ፡ አባታቸው ፡ ያዘዛቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጽመዋልና ፥ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ አልሰማኝምና ፤

17 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፣ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በተናገርኋቸው ፡ ጊዜ ፡ አልሰሙምና ፥ በጠራኋቸውም ፡ ጊዜ ፡ አልመለሱልኝምና ፡ የተናገርኹባቸውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ በሚቀመጡ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አመጣባቸዋለኹ ።

18 ፤ ኤርምያስም ፡ ሬካባውያንን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለአባታችኹ ፡ ለኢዮናዳብ ፡ ትእዛዝ ፡ ታዝዛችኋልና ፥ ትእዛዙንም ፡ ኹሉ ፡ ጠብቃችኋልና ፥ ያዘዛችኹንም ፡ ፈጽማችኋልና ፤

19 ፤ ስለዚህ ፥ በፊቴ ፡ የሚቆም ፡ ሰው ፡ ከሬካብ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮናዳብ ፡ ወገን ፡ ለዘለዓለም ፡ አይታጣም ።

________________ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 36 ። ________________

ምዕራፍ ፡ 36 ፤

1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጣ ፦

2 ፤ አንድ ፡ የመጽሐፍ ፡ ክርታስ ፡ ውሰድ ፥ ለአንተም ፡ ከተናገርኹበት ፡ ቀን ፡ ከኢዮስያስ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በእስራኤልና ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ በአሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የተናገርኹኽን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ጻፍበት ።

3 ፤ ምናልባት ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፦ እኔ ፡ አደርግባቸዋለኹ ፡ ያልኹትንና ፡ ያሰብኹትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ይሰሙ ፡ ይኾናል ፥ ከክፉ ፡ መንገዳቸው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ እኔም ፡ በደላቸውንና ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ እል ፡ ዘንድ ።

4 ፤ ኤርምያስም ፡ የኔርያን ፡ ልጅ ፡ ባሮክን ፡ ጠራ ፥ ባሮክም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለርሱ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ከኤርምያስ ፡ አፍ ፡ በመጽሐፉ ፡ ክርታስ ፡ ጻፈ ።

5 ፤ ኤርምያስም ፡ ባሮክን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አዘዘው ፦ እኔ ፡ ተግዤያለኹ ፤ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እገባ ፡ ዘንድ ፡ አልችልም ።

6 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ኺድ ፥ ከአፌም ፡ የጻፍኸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በጾም ፡ ቀን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በሕዝቡ ፡ ዦሮ ፡ በክርታሱ ፡ አንብብ ፤ ደግሞም ፡ ከከተማዎቻቸው ፡ በሚወጡ ፡ በይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ዦሮ ፡ አንብበው ።

7 ፤ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ የተናገረው ፡ ቍጣውና ፡ መዓቱ ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፥ ምናልባት ፡ ጸሎታቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ትወድቅ ፡ ይኾናል ፥ ኹሉም ፡ ከክፉ ፡ መንገዱ ፡ ይመለስ ፡ ይኾናል ።

8 ፤ የኔርያም ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ያዘዘውን ፡ ኹሉ ፡ አደረገ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በመጽሐፉ ፡ አነበበ ።

9 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ በዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡ በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የተቀመጡ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ከይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የመጡ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡



www.ethiopianorthodox.org

በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመጾም ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ።

10 ፤ ባሮክም ፡ የኤርምያስን ፡ ቃል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በላይኛው ፡ አደባባይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በዐዲሱ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ ባለው ፡ በጸሓፊው ፡ በሳፋን ፡ ልጅ ፡ በገማርያ ፡ ጓዳ ፡ በሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ጆሮ ፡ በመጽሐፉ ፡ አነበበ ።

11 ፤ የሳፋንም ፡ ልጅ ፡ የገማርያ ፡ ልጅ ፡ ሚክያስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ከመጽሐፉ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥

12 ፤ ወደንጉሡ ፡ ቤት ፡ ወደጸሓፊው ፡ ጓዳ ፡ ወረደ ፤ እንሆም ፥ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፥ ጸሓፊው ፡ ኤሊሳማ ፥ የሸማያ ፡ ልጅ ፡ ድላያ ፥ የዓክቦር ፡ ልጅ ፡ ኤልናታን ፥ የሳፋን ፡ ልጅ ፡ ገማርያ ፥ የሐናንያ ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅያስ ፡ አለቃዎቹም ፡ ኹሉ ፡ በዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

13 ፤ ሚክያስም ፡ ባሮክ ፡ በሕዝቡ ፡ ጆሮ ፡ በመጽሐፉ ፡ ባነበበ ፡ ጊዜ ፡ የሰማውን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ነገራቸው ።

14 ፤ አለቃዎቹም ፡ ኹሉ ፦ በሕዝቡ ፡ ጆሮ ፡ ያነበብኸውን ፡ ክርታስ ፡ በእጅኽ ፡ ይዘኽ ፡ ና ፡ የሚል ፡ መልእክት ፡ በኵሲ ፡ ልጅ ፡ በሰሌምያ ፡ ልጅ ፡ በናታንያ ፡ ልጅ ፡ በይሁዲ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ባሮክ ፡ ላኩ ። የኔርያም ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ ክርታሱን ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ መጣ ።

15 ፤ እነርሱም ፦ እስኪ ፡ ተቀመጥ ፥ በጆሯችንም ፡ አንብብ ፡ አሉት ። ባሮክም ፡ በጆሯቸው ፡ አነበበው ።

16 ፤ ቃሉንም ፡ ኹሉ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ፈርተው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተመካከሩ ፥ ባሮክንም ፦ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በርግጥ ፡ ለንጉሡ ፡ እንናገራለን ፡ አሉት ።

17 ፤ ባሮክንም ፦ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ከአፉ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ጻፍኸው ፡ ንገረን ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ።

18 ፤ ባሮክም ፦ ይህን ፡ ቃል ፡ ከአፉ ፡ ይነግረኝ ፡ ነበር ፥ እኔም ፡ በመጽሐፉ ፡ ላይ ፡ በቀለም ፡ እጽፍ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ።

19 ፤ አለቃዎቹም ፡ ባሮክን ፦ አንተና ፡ ኤርምያስ ፡ ኺዱ ፥ ተሸሸጉ ፥ ወዴትም ፡ እንደ ፡ ኾናችኹ ፡ ማንም ፡ አይወቅ ፡ አሉት ።

20 ፤ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ ገቡ ፥ ክርታሱንም ፡ በጸሓፊው ፡ በኤሊሳማ ፡ ጓዳ ፡ አኑረውት ፡ ነበር ፤ ቃሉንም ፡ ኹሉ ፡ በንጉሡ ፡ ጆሮ ፡ ተናገሩ ።

21 ፤ ንጉሡም ፡ ክርታሱን ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ይሁዲን ፡ ላከ ፥ ርሱም ፡ ከጸሓፊው ፡ ከኤሊሳማ ፡ ጓዳ ፡ ወሰደው ፤ ይሁዲም ፡ በንጉሡና ፡ በንጉሡ ፡ አጠገብ ፡ በቆሙት ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ጆሮ ፡ አነበበው ።

22 ፤ ንጉሡም ፡ በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ በክረምት ፡ ቤት ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፥ በፊቱም ፡ በምድጃ ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ ይነድ ፡ ነበር ።

23 ፤ ይሁዲም ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ አራት ፡ ዐምድ ፡ ያኽል ፡ ባነበበ ፡ ቍጥር ፥ ንጉሡ ፡ በካራ ፡ ቀደደው ፤ ክርታሱም ፡ በምድጃ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ እሳት ፡ ፈጽሞ ፡ እስኪቃጠል ፡ ድረስ ፡ በምድጃ ፡ ውስጥ ፡ ወዳለው ፡ እሳት ፡ ጣለው ።

24 ፤ ንጉሡም ፡ ይህንም ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ የሰሙ ፡ ባሪያዎቹ ፡ ኹሉ ፡ አልፈሩም ፡ ልብሳቸውንም ፡ አልቀደዱም ።

25 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኤልናታንና ፡ ድላያ ፡ ገማርያም ፡ ክርታሱን ፡ እንዳያቃጥል ፡ ንጉሡን ፡ ለመኑት ፥ ርሱ ፡ ግን ፡ አልሰማቸውም ።

26 ፤ ንጉሡም ፡ ጸሓፊውን ፡ ባሮክንና ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ ይይዙ ፡ ዘንድ ፡ የንጉሡን ፡ ልጅ ፡ ይረሕምኤልንና ፡ የዓዝርኤልን ፡ ልጅ ፡ ሰራያን ፡ የዓብድኤልንም ፡ ልጅ ፡ ሰሌምያን ፡ አዘዘ ፥ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ሰወራቸው ።

27 ፤ ንጉሡም ፡ ክርታሱንና ፡ ባሮክ ፡ ከኤርምያስ ፡ አፍ ፡ የጻፈውን ፡ ቃል ፡ ካቃጠለ ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

28 ፤ ዳግመኛም ፡ ሌላ ፡ ክርታስ ፡ ውሰድ ፥ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄም ፡ ባቃጠለው ፡ ክርታስ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ የቀድሞውን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ጻፍበት ።

29 ፤ የይሁዳንም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄምን ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አንተ ፦ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በርግጥ ፡ ይመጣል ፡ ይህችንም ፡ አገር ፡ ያፈርሳታል ፡ ከሰውና ፡ ከእንስሳም ፡ ባዶ ፡ ያደርጋታል ፡ ብለኽ ፡ ለምን ፡



www.ethiopianorthodox.org

ጻፍኽበት ፨ ብለኽ ፡ ይህን ፡ ክርታስ ፡ አቃጥለኻል ።

30 ፤ ስለዚህም ፡ ስለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ኢዮአቄም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡
ተቀማጭ ፡ አይኖርለትም ፤ ሬሳውም ፡ በቀን ፡ ለትኵሳት ፡ በሌሊትም ፡ ለውርጭ ፡ ይጣላል ።

31 ፤ ስለ ፡ ኀጢአታቸውም ፡ ርሱንና ፡ ዘሩን ፡ ባሪያዎቹንም ፡ እቀጣለኹ ፤ እነርሱም ፡ አልሰሙምና ፡ የተናገርኹባቸውን ፡
ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በእነርሱ ፡ ላይና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሚቀመጡ ፡ በይሁዳም ፡ሰዎች ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ።

ኤርምያስም ፡ ሌላ ፡ ክርታስ ፡ ወሰደ ፡ ለኔርያም ፡ ልጅ ፡ ለጸሓፊው ፡ ለባሮክ ፡ ሰጠው ፤ ርሱም ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡
ኢዮአቄም ፡ በእሳት ፡ ያቃጠለውን ፡ የመጽሐፉን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ከኤርምያስ ፡ አፍ ፡ ጻፈበት ፤ ደግሞም ፡ እንደ ፡
ቀድሞው ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ብዙ ፡ ቃል ፡ ተጨመረበት ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፤ ምዕራፍ ፡ 37 ።

ምዕራፍ ፡ 37 ፤

1 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ በይሁዳ ፡ ያነገሠው ፡ የኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በኢዮአቄም ፡ ልጅ ፡
በኢኮንያን ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

2 ፤ ርሱም ፡ ኾነ ፡ ባሪያዎቹ ፡ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ እጅ ፡ የተናገረውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
አልሰሙም ።

3 ፤ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፦ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ጸልይ ፡ ብሎ ፡ የሰሌምያን ፡ ልጅ ፡
ዮካልንና ፡ ካህኑን ፡ የመዕሴያን ፡ ልጅ ፡ ሶፎንያስን ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ ላከ ።

4 ፤ ርሱንም ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ገና ፡ አላገቡትም ፡ ነበርና ፤ ኤርምያስ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ይወጣና ፡ ይገባ ፡ ነበር ።

5 ፤ የፈርዖንም ፡ ሰራዊት ፡ ከግብጽ ፡ ወጣ ፤ ኢየሩሳሌምንም ፡ ከበዋት ፡ የነበሩ ፡ ከለዳውያን ፡ ይህን ፡ ወሬ ፡ በሰሙ ፡
ጊዜ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ።

6 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

7 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከእኔ ፡ ትጠይቁ ፡ ዘንድ ፡ የላካችኹን ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡
እንዲህ ፡ በሉት ፦ እንሆ ፤ ሊረዳችኹ ፡ የወጣው ፡ የፈርዖን ፡ ሰራዊት ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይመለሳል ።

8 ፤ ከለዳውያንም ፡ ተመልሰው ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡ ይዋጋታል ፡ ይይዟትማል ፡ በእሳትም ፡ ያቃጥሏታል ።

9 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አይኼዱምና ፦ ከለዳውያን ፡ በርግጥ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ይኼዳሉ ፡ ብላችኹ ፡
ራሳችኹን ፡ አታታልሉ ።

10 ፤ እናንተም ፡ የሚዋጉትን ፡ የከለዳውያንን ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ብትመቱት ፡ ኖሮ ፤ ከነርሱም ፡ የተወጉት ፡ ብቻ ፡ ቢቀሩ ፡
ኖሮ ፤ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ በድንኳኑ ፡ ተነሥቶ ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡ በእሳት ፡ ባቃጠሏት ፡ ነበር ።

11 ፤ የከለዳውያንም ፡ ሰራዊት ፡ ከፈርዖን ፡ ሰራዊት ፡ ፊት ፡ የተነሣ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፤

12 ፤ ኤርምያስ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ የርስቱን ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ከዚያ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ወደብንያም ፡ አገር ፡ ሊኼድ ፡
ከኢየሩሳሌም ፡ ወጣ ።

13 ፤ በብንያምም ፡ በር ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ የሐናንያ ፡ ልጅ ፡ የሰሌምያ ፡ ልጅ ፡ የሪያ ፡ የተባለ ፡ የዘበኛዎች ፡ አለቃ ፡ በዚያ ፡
ነበረ ፤ ርሱም ፦ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ መኰብለልኽ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ ያዘው ።

14 ፤ ኤርምያስም ፦ ሐሰት ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ መኰብለሌ ፡ አይደለም ፡ አለ ፤ ርሱ ፡ ግን ፡
አልሰማውም ፤ የሪያም ፡ ኤርምያስን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አለቃዎች ፡ አመጣው ።

15 ፤ አለቃዎችም ፡ ተቈጥተው ፡ ኤርምያስን ፡ መቱት ፤ የጸሓፊውንም ፡ የዮናታንን ፡ ቤት ፡ የግዞት ፡ ቤት ፡ አድርገውት ፡
ነበርና ፤ በዚያ ፡ አኖሩት ።

16 ፤ ኤርምያስም ፡ ወደጕድጓድ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ጓዳዎቹ ፡ ገባ ፤ ኤርምያስም ፡ በዚያ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፤



www.ethiopianorthodox.org

17 ፤ ንጉሡ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ልኮ ፡ አስመጣው ፥ ንጉሡም ፡ በቤቱ ። በእውኑ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የኾነ ፡ ቃል ፡
አለን ፡ ብሎ ፡ በቈይታ ፡ ጠየቀው ። ኤርምያስም ፦ አዎን ፡ አለ ። ደግሞም ፦ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አልፈኽ ፡
ትሰጣለኽ ፡ አለ ።

18 ፤ ኤርምያስም ፡ ደግሞ ፡ ንጉሡን ፡ ሴዴቅያስን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ በግዞት ፡ ቤት ፡ የጣላችኹኝ ፡ አንተን ፡ ወይስ ፡
ባሪያዎችኽን ፡ ወይስ ፡ ሕዝብኽን ፡ ምን ፡ በድያችኹ ፡ ነው ፧

19 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በእናንተና ፡ በዚች ፡ አገር ፡ አይመጣባችኹም ፡ ብለው ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩላችኹ ፡ የነበሩ ፡
ነቢያታችኹ ፡ ወዴት ፡ አሉ ፧

20 ፤ ንጉሡ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እንድትሰማኝ ፡ አኹን ፡ እለምንኻለኹ ፤ እባክኽ ፥ ልመናዬ ፡ ወዳንተ ፡ ይድረስ ፤ በዚያ ፡
እንዳልሞት ፡ ወደጸሓፊው ፡ ወደዮናታን ፡ ቤት ፡ አትመልሰኝ ።

21 ፤ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፡ አዘዘ ፥ ኤርምያስንም ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ አኖሩት ፥ እንጀራም ፡ ኹሉ ፡ ከከተማ ፡
እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ እንጀራ ፡ ከጋጋሪዎች ፡ መንገድ ፡ ይሰጡት ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡
ኤርምያስ ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 38 ።

ምዕራፍ ፡ 38 ፤

1 ፤ ኤርምያስም ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ የማታን ፡ ልጅ ፡ ስፋጥያስ ፥ የጳስኮርም ፡ ልጅ ፡
ጎዶልያስ ፥ የሰሌምያም ፡ ልጅ ፡ ዮካል ፥ የመልክያም ፡ ልጅ ፡ ጳስኮር ፡ ሰሙ ።

2 ፤ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሏልና ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዚች ፡ ከተማ ፡ የሚቀመጥ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡
በቸነፈርም ፡ ይሞታል ፤ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ ግን ፡ የሚወጣ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፥ ነፍሱም ፡ እንደ ፡ ምርኮ ፡
ትኾንለታለች ፥ በሕይወትም ፡ ይኖራል ።

3 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ይህች ፡ ከተማ ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሰራዊት ፡ እጅ ፡ በርግጥ ፡
ትሰጣለች ፥ ርሱም ፡ ይይዛታል ።

4 ፤ አለቃዎቹም ፡ ንጉሡን ፦ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ቃል ፡ ሲነግራቸው ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ የቀሩትን ፡ የሰልፈኛዎቹን ፡
እጅ ፡ የሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ ያደክማልና ፥ ይህ ፡ ሰው ፡ እንዲገደል ፡ እንለምንኻለን ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ክፉትን ፡ እንጂ ፡
ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ሰላምን ፡ አይመኝለትምና ፡ አሉት ።

5 ፤ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፦ ንጉሡ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልምና ፥ እንሆ ፥ በእጃችኹ ፡ ነው ፡
አለ ።

6 ፤ ኤርምያስንም ፡ ወሰዱት ፡ በግዞት ፡ ቤቱም ፡ አደባባይ ፡ ወደነበረው ፡ ወደንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ወደመልክያ ፡ጕድጓድ ፡
ውስጥ ፡ ጣሉት ፤ ኤርምያስንም ፡ በገመድ ፡ አወረዱት ። በጕድጓድም ፡ ውስጥ ፡ ጭቃ ፡ እንጂ ፡ ውሃ ፡
አልነበረበትም ፤ ኤርምያስም ፡ ወደ ፡ ጭቃው ፡ ውስጥ ፡ ገባ ።

7 ፤ በንጉሡም ፡ ቤት ፡ የነበረው ፡ ጃን ፡ ደረባ ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ አቢሜሌክ ፡ ኤርምያስን ፡ በጕድጓዱ ፡ ውስጥ ፡
እንዳኖሩት ፡ሰማ ። ንጉሡም ፡ በብንያም ፡ በር ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።

8 ፤ አቢሜሌክም ፡ ከንጉሡ ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡ ንጉሡን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦

9 ፤ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ በጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ በመጣላቸው ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
በማድረጋቸው ፡ ኹሉ ፡ ክፉ ፡ አድርገዋል ፤ በከተማዪቱም ፡ ውስጥ ፡ እንጀራ ፡ ስለሌለ ፡ በዚያ ፡ በራብ ፡ ይሞታል ።

10 ፤ ንጉሡም ፡ ኢትዮጵያዊውን ፡ አቢሜሌክም ፦ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ሠላሳ ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ ውሰድ ፥ ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፡
ሳይሞት ፡ ከጕድጓድ ፡ አውጣው ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ።

11 ፤ አቢሜሌክም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሰዎችን ፡ ይዞ ፡ ኼደ ፥ ከቤተ ፡ መዛግብቱም ፡ በታች ፡ ወደነበረው ፡ ወደንጉሥ ፡ ቤት ፡
ገባ ፥ ከዚያም ፡ አሮጌ ፡ ጨርቅና ፡ ዕላቂ ፡ ልብስ ፡ወሰደ ፥ ወደ ፡ ኤርምያስም ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ በገመድ ፡
አወረደው ።



www.ethiopianorthodox.org

12 ፤ ኢትዮጵያዊውም ፡ አቢሜሌክ ፡ ኤርምያስን ፦ ይህን ፡ አሮጌ ፡ ጨርቅና ፡ ዕላቂውን ፡ ልብስ ፡ በብብትኽ ፡ ከገመዱ ፡ በታች ፡ አድርግ ፡ አለው ፤ ኤርምያስም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

13 ፤ ኤርምያስንም ፡ በገመዱ ፡ ጐተቱት ፡ ከጕድጓድም ፡ አወጡት ፥ ኤርምያስም ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ተቀመጠ ።

14 ፤ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ልኮ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወደነበረው ፡ ወደ ፡ ሦስተኛው ፡ መግቢያ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ አስመጣው ፤ ንጉሡም ፡ ኤርምያስን ፦ አንዲት ፡ ነገር ፡ እጠይቅኻለኹ ፤ ምንም ፡ አትሸሽገኝ ፡ አለው ።

15 ፤ ኤርምያስም ፡ ሴዴቅያስን ፦ ብነግርኽ ፡ በእውኑ ፡ አትገድለኝምን ፧ ብመክርኽም ፡ አትሰማኝም ፡ አለው ።

16 ፤ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፦ ይህችን ፡ ነፍስ ፡ የፈጠረልን ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! አልገድልኽም ፥ ነፍስኽንም ፡ ለሚሹ ፡ ለእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ አልሰጥኽም ፡ ብሎ ፡ በቈይታ ፡ ለኤርምያስ ፡ ማለ ።

17 ፤ ኤርምያስም ፡ ሴዴቅያስን ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቃዎች ፡ ብትወጣ ፥ ነፍስኽ ፡ በሕይወት ፡ ትኖራለች ፡ ይህችም ፡ ከተማ ፡ በእሳት ፡ አትቃጠልም ፤ አንተም ፡ ቤትኽም ፡ በሕይወት ፡ ትኖራላችኹ ።

18 ፤ ወደባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቃዎች ፡ ባትወጣ ፡ ግን ፥ ይህች ፡ ከተማ ፡ በከለዳውያን ፡ እጅ ፡ ትሰጣለች ፥ በእሳትም ፡ ያቃጥሏታል ፡ አንተም ፡ ከእጃቸው ፡ አታመልጥም ፡ አለው ።

19 ፤ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኤርምያስን ፦ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ በኰበለሉት ፡ በአይሁድ ፡ እጅ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡኛል ፡ እነርሱም ፡ ያፌዙብኛል ፡ ብዬ ፡ እፈራለኹ ፡ አለው ።

20 ፤ ኤርምያስም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ አሳልፈው ፡ አይሰጡኽም ። እኔ ፡ የምነግርኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እባክኽ ፥ ስማ ፤ ይቀናኻል ፥ ነፍስኽም ፡ በሕይወት ፡ ትኖራለች ።

21 ፤ ትወጣ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ብትል ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ያሳየኝ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

22 ፤ እንሆ ፥ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ የቀሩትን ፡ ሴቶች ፡ ኹሉ ፡ ወደባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቃዎች ፡ ያወጣሉ ፤ እነዚያም ፡ ሴቶች ፦ ባለሟሎችኽ ፡ አታለሉኻል ፡ አሸንፈውኽማል ፤ እግሮችኽ ፡ ግን ፡ አኹን ፡ በጭቃ ፡ ውስጥ ፡ ከገቡ ፡ እነርሱ ፡ ከአንተ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰዋል ፡ ይላሉ ።

23 ፤ ሚስቶችኽንና ፡ ልጆችኽንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ ያወጣሉ ፤ አንተም ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ትያዛለኽ ፡ እንጂ ፡ ከእጃቸው ፡ አታመልጥም ፤ ይህችም ፡ ከተማ ፡ በእሳት ፡ ትቃጠላለች ።

24 ፤ ሴዴቅያስም ፡ ኤርምያስን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ይህን ፡ ቃል ፡ ማንም ፡ አይወቅ ፥ አንተም ፡ አትሞትም ።

25 ፤ አለቃዎቹ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተነጋገርኹ ፡ ቢሰሙ ፥ ወዳንተም ፡ መጥተው ፦ ለንጉሡ ፡ ያልኸውን ፡ ንገረን ፡ አትሸሽገንም ፥ እኛም ፡ አንገድልኽም ፤ ደግሞ ፡ ንጉሡ ፡ ያለኽን ፡ ንገረን ፡ ቢሉኽ ፥ አንተ ፦

26 ፤ በዚያ ፡ እሞት ፡ ዘንድ ፡ ወደዮናታን ፡ ቤት ፡ አትመልሰኝ ፡ ብዬ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ለመንኹ ፡ በላቸው ።

27 ፤ አለቃዎቹም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጥተው ፡ ጠየቁ ፥ ንጉሡም ፡ እንዳዘዘው ፡ እንደዚህ ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ነገራቸው ። ነገሩም ፡ አልተሰማምና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ መነጋገርን ፡ ተው ።

28 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ እስከተያዘችበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ተቀመጠ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 39 ።

ምዕራፍ ፡ 39 ፤

1 ፤ ኢየሩሳሌምም ፡ በተያዘች ፡ ጊዜ ፥ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሴዴቅያስ ፡ በዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ በዐሥረኛው ፡ ወር ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾርና ፡ ሰራዊቱ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጥተው ፡ ከበቧት ፤

2 ፤ በሴዴቅያስም ፡ በዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ በአራተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዘጠነኛው ፡ ቀን ፡ ከተማዪቱ ፡ ተሰበረች ።



www.ethiopianorthodox.org

3 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፥ ኤርጌል ፡ ሳራስር ፥ ሳምጋርናቦ ፥ ሠርሰኪም ፥ ራፌስ ፥ ኤርጌል ፡ ሳራስር ፥ ራብማግ ፥ ከቀሩት ፡ ከባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ገብተው ፡ በመካከለኛው ፡ በር ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ።

4 ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ሰልፈኛዎቹም ፡ ኹሉ ፡ ባይዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ኰበለሉ ፥ በሌሊትም ፡ በንጉሡ ፡ አትክልት ፡ መንገድ ፡ በኹለቱ ፡ ቅጥር ፡ መካከል ፡ ከነበረው ፡ ደጅ ፡ ከከተማዪቱ ፡ ወጡ ፤ በዐረባም ፡ መንገድ ፡ ወጡ ።

5 ፤ የከለዳውያንም ፡ ሰራዊት ፡ ተከታተላቸው ፥ ሴዴቅያስንም ፡ በኢያሪኮ ፡ ሜዳ ፡ አገኙት ፤ ይዘውም ፡ በሐማት ፡ ምድር ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ሪብላ ፡ ወደባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ናቡከደነጾር ፡ አመጡት ፡ ርሱም ፡ ፍርድን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተናገረ ።

6 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ የሴዴቅያስን ፡ ልጆች ፡ በዐይኑ ፡ ፊት ፡ በሪብላ ፡ ገደላቸው ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ የይሁዳን ፡ ከበርቴዎች ፡ ኹሉ ፡ ገደለ ።

7 ፤ የሴዴቅያስንም ፡ ዐይን ፡ አወጣ ፥ ወደ ፡ ባቢሎንም ፡ ይወስደው ፡ ዘንድ ፡ በሰንሰለት ፡ አሰረው ።

8 ፤ ከለዳውያንም ፡ የንጉሡንና ፡ የሕዝቡን ፡ ቤቶች ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉ ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቅጥር ፡ አፈረሱ ።

9 ፤ የዘበኛዎቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ በከተማዪቱ ፡ የቀሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ርሱም ፡ የኰበለሉትን ፡ ሰዎች ፡ የቀረውንም ፡ የሕዝቡን ፡ ቅሬታ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ማረካቸው ።

10 ፤ አንዳች ፡ ከሌላቸው ፡ ከሕዝቡ ፡ ድኻዎች ፡ ግን ፡ የዘበኛዎቹ ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ በይሁዳ ፡ አገር ፡ ተዋቸው ፥ የወይኑን ፡ ቦታና ፡ ዕርሻውን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሰጣቸው ።

11–12 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ስለ ፡ ኤርምያስ ፦ ውሰደውና ፡ በመልካም ፡ ተመልከተው ፥ የሚሻውንም ፡ ነገር ፡ አድርግለት ፡ እንጂ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ አታድርግበት ፡ ብሎ ፡ የዘበኛዎቹን ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳንን ፡ አዘዘ ።

13 ፤ የዘበኛዎቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ላከ ፥ ናቡሽዝባንም ፡ ራፋስቂስም ፡ ኤርጌል ፡ ሳራስርም ፡ ራብማግም ፡ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ላኩ ፤

14 ፤ ኤርምያስንም ፡ ከግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ አወጡት ፥ ወደ ፡ ቤቱም ፡ ይወስደው ፡ ዘንድ ፡ ለሳፋን ፡ ልጅ ፡ ለአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ለጎዶልያስ ፡ ሰጡት ፤ እንዲህም ፡ በሕዝብ ፡ መካከል ፡ ተቀመጠ ።

15 ፤ በግዞትም ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ታስሮ ፡ ሳለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጣ ፦

16 ፤ ኺድ ፡ ለኢትዮጵያዊውም ፡ ለአቢሜሌክ[261] ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ለበጎነት ፡ ሳይኾን ፡ ለክፋት ፡ ቃሌን ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በፊትኽ ፡ ይፈጸማል ።

17 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ አድንኻለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ በምትፈራቸው ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ አልሰጥኽም ።

18 ፤ ፈጽሜ ፡ አድንኻለኹ ፡ ነፍስኽም ፡ እንደ ፡ ምርኮ ፡ ትኾንልኻለች ፡ እንጂ ፡ በሰይፍ ፡ አትወድቅም ፥ በእኔ ፡ ታምነኻልና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 40 ።

ምዕራፍ ፡ 40 ፤

1 ፤ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ በተማረኩት ፡ በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ ምርኮኛዎች ፡ መካከል ፡ የዘበኛዎቹ ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ በሰንሰለት ፡ አስሮ ፡ በወሰደው ፡ ጊዜ ፡ ከራማ ፡ ከለቀቀው ፡ በኋላ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

2 ፤ የዘበኛዎቹም ፡ አለቃ ፡ ኤርምያስን ፡ ወሰደው ፡ እንዲህም ፡ አለው ፦ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተናገረ ፤

3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አመጣው ፡ እንደ ፡ ተናገረውም ፡ አደረገ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡

261 ዕብ. ፥ ዐበድመለክ ፡ (የንጉሥ ፡ አገልጋይ) ።



www.ethiopianorthodox.org

ሠርታችኋልና ፤ ቃሉንም ፡ አልሰማችኹምና ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ኾነባችኹ ።

4 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ በእጅኽ ፡ ካለችው ፡ ሰንሰለት ፡ ዛሬ ፡ ፈታኹኽ ። ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ መምጣት ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ ቢታይኽ ፥ ና ፥ እኔም ፡ በመልካም ፡ አይኻለኹ ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ መምጣት ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ ባይታይኽ ፡ ግን ፥ ተቀመጥ ፤ እንሆ ፥ አገሪቱ ፡ ዅሉ ፡ በፊትኽ ፡ ናት ፤ ትኼድ ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ ወደሚታይኽ ፡ ደስ ፡ ወደሚያሠኝኽም ፡ ስፍራ ፡ ኺድ ።

5 ፤ ርሱም ፡ ገና ፡ ሳይመለስ ። የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ላይ ፡ ወደሾመው ፡ ወደሳፋን ፡ ልጅ ፡ ወደአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ ተመለስ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ተቀመጥ ፤ ወይም ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፡ ደስ ፡ ወደሚያሠኝኽ ፡ ስፍራ ፡ ኺድ ፡ አለው ። የዘበኛዎቹም ፡ አለቃ ፡ ሥንቅና ፡ ስጦታ ፡ ሰጥቶ ፡ አሰናበተው ።

6 ፤ ኤርምያስም ፡ የአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ኼደ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ በቀሩት ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ተቀመጠ ።

7 ፤ በየሜዳውም ፡ የነበሩት ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎችና ፡ ሰዎቻቸው ፡ ዅሉ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የአኪቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሾመ ፥ ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ልጆችንም ፥ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ያልተማረኩትን ፡ የምድርን ፡ ድኻዎች ፥ እንዳስጠበቀ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፥

8 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናንና ፡ ዮናታን ፥ የተንሑሜትም ፡ ልጅ ፡ ሰራያ ፥ የነጦፋዊውም ፡ የዮፌ ፡ ልጆች ፡ የማዕካታዊውም ፡ ልጅ ፡ ያእዛንያ ፡ ከሰዎቻቸው ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ መጡ ።

9 ፤ የሳፋንም ፡ ልጅ ፡ የአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስ ፡ ለእነርሱና ፡ ለሰዎቻቸው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ማለ ። ለከለዳውያን ፡ ትገዙ ፡ ዘንድ ፡ አትፍሩ ፤ በምድር ፡ ተቀመጡ ፡ ለባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ተገዙ ፥ መልካምም ፡ ይኾንላችኋል ።

10 ፤ እኔም ፥ እንሆ ፥ ወደ ፡ እኛ ፡ በሚመጡት ፡ ከለዳውያን ፡ ፊት ፡ እቆም ፡ ዘንድ ፡ በምጽጳ ፡ እኖራለኹ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ወይንንና ፡ የበጋ ፡ ፍሬ ፡ ዘይትንም ፡ አከማቹ ፥ በየዕቃችኹም ፡ ውስጥ ፡ ክተቱ ፥ በያዛችኋቸውም ፡ ከተማዎቻችኹ ፡ ተቀመጡ ።

11 ፤ በሞዐብም ፡ በዐሞንም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ በኤዶምያስም ፡ በምድርም ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ አይሁድ ፡ ዅሉ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የይሁዳን ፡ ቅሬታ ፡ እንዳስቀረ ፥ የሳፋንንም ፡ ልጅ ፡ የአኪቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ በላያቸው ፡ እንደ ፡ ሾመው ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥

12 ፤ አይሁድ ፡ ዅሉ ፡ ከተሰደዱበት ፡ ስፍራ ፡ ዅሉ ፡ ተመለሱ ፥ ወደይሁዳም ፡ አገር ፡ ጎዶልያስ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ መጡ ፥ ወይንና ፡ የበጋንም ፡ ፍሬ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ አከማቹ ።

13 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ በየሜዳውም ፡ የነበሩ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎች ፡ ዅሉ ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ መጥተው ፡—

14 ፤ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ በዓሊስ ፡ ይገድልኽ ፡ ዘንድ ፡ የናታንያን ፡ ልጅ ፡ እስማኤልን ፡ እንደ ፡ ሰደደ ፡ ታውቃለኽን ፦ አሉት ። የአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስ ፡ ግን ፡ አላመናቸውም ።

15 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡— እባክኽ ፥ ልኺድ ፤ ማንም ፡ ሳያውቅ ፡ የናታንያን ፡ ልጅ ፡ እስማኤልን ፡ ልግደለው ፤ ወዳንተ ፡ የተሰበሰቡ ፡ አይሁድ ፡ ዅሉ ፡ እንዲበተኑ ፡ የይሁዳም ፡ ቅሬታ ፡ እንዲጠፋ ፡ ነፍስኽን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይገድላል ፦ ብሎ ፡ በምጽጳ ፡ በቈይታ ፡ ለጎዶልያስ ፡ ተናገረ ።

16 ፤ የአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስ ፡ ግን ፡ የቃሬያን ፡ ልጅ ፡ ዮሐናንን ፡— በእስማኤል ፡ ላይ ፡ ሐሰት ፡ ተናግረኻልና ፥ ይህን ፡ ነገር ፡ አታድርግ ፡ አለው ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 41 ።

ምዕራፍ ፡ 41 ፤

1 ፤ በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ ከመንግሥት ፡ ወገንና ፡ ከንጉሡ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ አለቃዎች ፡ አንዱ ፡ የኤሊሳማ ፡ ልጅ ፡ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ከዐሥር ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ወደአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ መጣ ፤ በዚያም ፡ በምጽጳ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ እንጀራ ፡ በሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

2 ፤ የናታንያም ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ዐሥሩ ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተው ፡ የሳፋንን ፡ ልጅ ፡ የአኪቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ በሰይፍ ፡ መቱ ፥ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ የሾመውን ፡ ገደሉ ።

3 ፤ እስማኤልም ፡ ከጎዶልያስ ፡ ጋራ ፡ በምጽጳ ፡ የነበሩትን ፡ አይሁድ ፡ ኹሉ ፥ በዚያም ፡ የተገኙትን ፡ የከለዳውያንን ፡ ሰልፈኛዎች ፡ ኹሉ ፡ ገደላቸው ።

4 ፤ ጎዶልያስን ፡ ከገደለ ፡ በኋላ ፡ ማንም ፡ ሳያውቅ ፡ በኹለተኛው ፡ ቀን ፥

5 ፤ ጢማቸውን ፡ ላጭተው ፡ ልብሳቸውንም ፡ ቀደው ፡ ገላቸውንም ፡ ነጭተው ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ የእኽል ፡ ቍርባንና ፡ ዕጣን ፡ በእጃቸው ፡ እየያዙ ፥ ሰማንያ ፡ ሰዎች ፡ ከሴኬምና ፡ ከሴሎ ፡ ከሰማርያም ፡ መጡ ።

6 ፤ የናታንያም ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ከምጽጳ ፡ ወጥቶ ፡ እያለቀሰ ፡ ሊገናኛቸው ፡ ኼደ ፤ በተገናኛቸውም ፡ ጊዜ ፦ ወደአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ ኑ ፡ አላቸው ።

7 ፤ ወደከተማም ፡ መካከል ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ገደሏቸው ፥ በጕድጓድም ፡ መካከል ፡ ጣሏቸው ።

8 ፤ በመካከላቸውም ፡ እስማኤልን ፦ በሜዳ ፡ የተሸሸገ ፡ ስንዴና ፡ ገብስ ፡ ዘይትና ፡ ማርም ፡ አለንና ፡ አትግደለን ፡ የሚሉት ፡ ዐሥር ፡ ሰዎች ፡ ተገኙ ። ርሱም ፡ ተዋቸው ፥ ከወንድሞቻቸውም ፡ ጋራ ፡ አልገደላቸውም ።

9 ፤ እስማኤልም ፡ ከጎዶልያስ ፡ ጋራ ፡ የገደላቸውን ፡ የሰዎች ፡ ሬሳ ፡ ኹሉ ፡ የጣለበት ፡ ጕድጓድ ፡ ንጉሡ ፡ አሣ ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ ባኦስን ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡ የሠራው ፡ ጕድጓድ ፡ ነበረ ፤ የናታንያም ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ የገደላቸውን ፡ ሞላበት ።

10 ፤ እስማኤልም ፡ በምጽጳ ፡ የነበረውን ፡ የሕዝቡን ፡ ቅሬታ ፡ ኹሉ ፥ የንጉሡን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ የዘበኛዎቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ለአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ለጎዶልያስ ፡ የሰጠውን ፡ በምጽጳ ፡ የቀሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ማረካቸው ፤ የናታንያም ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ማርኮ ፡ ወደዐሞን ፡ ልጆች ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ ተነሣ ።

11 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ያደረገውን ፡ ክፋት ፡ ኹሉ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥

12 ፤ ሰዎቹን ፡ ኹሉ ፡ ይዘው ፡ ከናታንያ ፡ ልጅ ፡ ከእስማኤል ፡ ጋራ ፡ ሊዋጉ ፡ ኼዱ ፥ በገባዖንም ፡ ባለው ፡ በታላቁ ፡ ውሃ ፡ አጠገብ ፡ አገኙት ።

13 ፤ ከእስማኤልም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ የቃሬያን ፡ ልጅ ፡ ዮሐናንን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎችን ፡ ኹሉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

14 ፤ እስማኤልም ፡ ከምጽጳ ፡ የማረካቸው ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ ተመለሱ ፥ ወደቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዮሐናን ፡ ኼዱ ።

15 ፤ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ግን ፡ ከስምንት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ከዮሐናን ፡ አመለጠ ፡ ወደዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ኼደ ።

16 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ የአኪቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ በምጽጳ ፡ ከገደለው ፡ በኋላ ፡ ከናታንያ ፡ ልጅ ፡ ከእስማኤል ፡ ያስመለሷቸውን ፡ የሕዝቡን ፡ ቅሬታ ፡ ኹሉ ፥ ከገባዖን ፡ ያስመለሷቸውን ፡ ሰልፈኛዎች ፥ ሴቶችንም ፥ ልጆችንም ፥ ጃን ፡ ደረባዎችንም ፥ ወሰዱ ፤

17 ፤ ተነሥተውም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ በጌሮት ፡ ከመዓም ፡ ተቀመጡ ፤

18 ፤ እስማኤል ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ የሾመውን ፡ የአኪቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ ስለ ፡ ገደለው ፡ ከለዳውያንን ፡ ፈርተዋልና ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 42 ።

ምዕራፍ ፡ 42 ፤

1 ፤ የጭፍራ ፡ አለቃዎችም ፡ ኹሉ ፡ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ የሆሻያም ፡ ልጅ ፡ ያእዛንያ ፡ ሕዝብም ፡ ኹሉ ፡ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ቀረቡ ፥



www.ethiopianorthodox.org

2-3 ፤ ነቢዩንም ፡ ኤርምያስን ፦ ዐይኖችኽ ፡ እንዳዩን ፡ ከብዙ ፡ ጥቂት ፡ ቀርተናልና ፥ ልመናችን ፥ እባክኽ ፥ በፊትኽ ፡ ትድረስ ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ የምንኼድበትን ፡ መንገድና ፡ የምናደርገውን ፡ ነገር ፡ ያሳየን ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኛ ፥ ስለዚህ ፡ ቅሬታ ፡ ኹሉ ፥ ወደ ፡ አምላክኽ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልይ ፡ አሉት ።

4 ፤ ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፦ ሰምቻችኋለኹ ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ ቃላችኹ ፡ ወደ ፡ አምላካችኹ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጸልያለኹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሚመልስላችኹን ፡ ኹሉ ፡ እነግራችኋለኹ ፥ ከእናንተም ፡ ምንም ፡ አልሸሽግም ፡ አላቸው ።

5 ፤ ኤርምያስንም ፦ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባንተ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ የላከውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ባናደርግ ፥ እግዚአብሔር ፡ በመካከላችን ፡ እውነተኛና ፡ ታማኝ ፡ ምስክር ፡ ይኹን ።

6 ፤ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በመስማታችን ፡ መልካም ፡ እንዲኾንልን ፥ መልካም ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ ቢኾን ፥ አንተን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ የምንልክኽ ፡ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እንሰማለን ፡ አሉት ።

7 ፤ ከዐሥር ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጣ ።

8 ፤ የቃሬያንም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናንን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፡ ጠራ ፥ እንዲህም ፡ አላቸው ፦

9 ፤ ጸሎታችኹን ፡ በፊቱ ፡ አቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ የላካችኹኝ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

10 ፤ ስላደረግኹባችኹ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ተጸጽቻለኹና ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ ብትቀመጡ ፡ እሠራችኋለኹ ፡ እንጂ ፡ አላፈርሳችኹም ፥ እተክላችኋለኹ ፡ እንጂ ፡ አልነቅላችኹም ።

11 ፤ ከምትፈሩት ፡ ከባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አትፍሩ ፤ አድናችኹ ፡ ዘንድ ፡ ከእጁም ፡ አስጥላችኹ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ አትፍሩ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

12 ፤ ርሱ ፡ እንዲምራችኹ ፡ ወደ ፡ አገራችኹም ፡ እንዲመልሳችኹ ፡ እኔ ፡ እምራችኋለኹ ።

13 ፤ እናንተ ፡ ግን ፦ በዚች ፡ ምድር ፡ አንቀመጥም ፡ ብትሉ ፡ የአምላካችኹንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ባትሰሙ ፥

14 ፤ እናንተም ፦ አይደለም ፤ ሰልፍ ፡ ወደማናይባት ፡ የመለከትም ፡ ድምፅ ፡ ወደማንሰማባት ፡ ወደማንራብባትም ፡ ወደግብጽ ፡ ምድር ፡ እንኼዳለን ፡ በዚያም ፡ እንቀመጣለን ፡ ብትሉ ፥

15 ፤ እናንተ ፡ የይሁዳ ፡ ቅሬታ ፡ ሆይ ፥ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ትገቡ ፡ ዘንድ ፡ በዚያም ፡ ትቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ ፊታችኹን ፡ ብታቀኑ ፥

16 ፤ የምትፈሩት ፡ ሰይፍ ፡ በዚያ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ያገኛችኋል ፥ ስለ ፡ ርሱም ፡ የምትደነግጡበት ፡ ራብ ፡ በዚያ ፡ በግብጽ ፡ ይደርስባችኋል ፥ በዚያም ፡ ትሞታላችኹ ።

17 ፤ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ በዚያም ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ ፊታቸውን ፡ በሚያቀኑ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ይኾንባቸዋል ፤ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ ይሞታሉ ፤ እኔም ፡ ከማመጣባቸው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ማንም ፡ አይቀርም ፥ ማንም ፡ አያመልጥም ።

18 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ቍጣዬና ፡ መዓቴ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሚኖሩ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ፈሰሰ ፥ እንዲሁ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ በገባችኹ ፡ ጊዜ ፡ መዓቴ ፡ ይፈስባችኋል ፤ እናንተም ፡ ለጥላቻና ፡ ለመደነቂያ ፡ ለመረገሚያና ፡ ለመሰደቢያ ፡ ትኾናላችኹ ፥ ይህንም ፡ ስፍራ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አታዩትም ።

19 ፤ እናንተ ፡ የይሁዳ ፡ ቅሬታ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፦ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አትግቡ ፡ ብሎ ፡ ተናግሮባችኋልና ፥ ዛሬ ፡ እንዳስጠነቀቅኋችኹ ፡ በርግጥ ፡ ዕወቁ ።

20 ፤ እናንተ ፦ ስለ ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልይ ፥ አምላካችንም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚናገርኽን ፡ ኹሉ ፡ ንገረን ፡ እኛም ፡ እናደርገዋለን ፡ ብላችኹ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ አምላካችኹ ፡ ልካችኹኝ ፡ ነበርና ፥ ራሳችኹን ፡ አታላችኋል ።



www.ethiopianorthodox.org

21 ፤ እኔም ፡ ዛሬ ፡ ነግሬያችኋለኹ ፥ ወደ ፡ እናንተም ፡ በላከኝ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የአምላካችኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰማችኹም ።

22 ፤ አኹንም ፡ ኼዳችኹ ፡ እንድትቀመጡ ፡ በወደዳችኹበት ፡ ስፍራ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ እንድትሞቱ ፡ በርግጥ ፡ ዕወቁ ።

__________________ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 43 ። _________________

ምዕራፍ ፡ 43 ፤

1 ፤ የአምላካቸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፥ ለእነርሱ ፡ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ የላከውን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፥ ኤርምያስ ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ መናገርን ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፥

2 ፤ የሆሻያ ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስ ፡ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ ትዕቢተኛዎችም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ኤርምያስን ፦ ሐሰት ፡ ተናግረኻል ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፦ በዚያ ፡ ትቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አትግቡ ፡ ብሎ ፡ አላከኽም ፤

3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከለዳውያን ፡ እንዲገድሉን ፡ ወደ ፡ ባቢሎንም ፡ እንዲማርኩን ፡ በእጃቸው ፡ አሳልፈኽ ፡ ትሰጠን ፡ ዘንድ ፡ የኔርያ ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ በላያችን ፡ ላይ ፡ አነሣሥቶኻል ፡ አሉት ።

4 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎችም ፡ ኹሉ ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ በይሁዳ ፡ ምድር ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰሙም ።

5 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎችም ፡ ኹሉ ፡ በይሁዳ ፡ ምድር ፡ ለመቀመጥ ፡ ከተሰደዱባቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ የተመለሱትን ፡ የይሁዳን ፡ ቅሬታ ፡ ኹሉ ፥

6 ፤ ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ልጆችንም ፡ የንጉሡንም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፥ የዘበኛዎቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ከሳፋን ፡ ልጅ ፡ ከአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ከጎዶልያስ ፡ ጋራ ፡ የተዋቸውን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፥ ነቢዩንም ፡ ኤርምያስን ፡ የኔርያንም ፡ ልጅ ፡ ባሮክን ፡ ወሰዱ ፤

7 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ አልሰሙምና ፡ ወደግብጽ ፡ ምድር ፡ ገቡ ፥ እስከ ፡ ጣፍናስ ፡ ድረስ ፡ መጡ ።

8 ፤ በጣፍናስም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

9 ፤ ታላላቆችን ፡ ድንጋዮች ፡ በእጅኽ ፡ ውሰድ ፥ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ እያዩ ፡ በጣፍናስ ፡ ባለው ፡ በፈርዖን ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ መግቢያ ፡ ሸሽጋቸው ፤

10 ፤ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ልኬ ፡ ባሪያዬን ፡ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾርን ፡ አመጣለኹ ፥ ዙፋኑንም ፡ እኔ ፡ በሸሸግኋቸው ፡ በእነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ ላይ ፡ አኖራለኹ ፤ እርሱም ፡ ማለፊያውን ፡ ድንኳኑን ፡ በላያቸው ፡ ይዘረጋል ።

11 ፤ መጥቶም ፡ የግብጽን ፡ ምድር ፡ ይመታል ፥ ለሞትም ፡ የሚኾነውን ፡ ለሞት ፥ ለምርኮም ፡ የሚኾነውን ፡ ለምርኮ ፥ ለሰይፍም ፡ የሚኾነውን ፡ ለሰይፍ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ።

12 ፤ በግብጽም ፡ አማልክት ፡ ቤቶች ፡ እሳትን ፡ ያነዷል ፡ ያቃጥላቸውማል ፡ ይማርካቸውማል ፤ እረኛም ፡ ደበሎውን ፡ እንደሚደርብ ፡ እንዲሁ ፡ የግብጽን ፡ አገር ፡ ይደርባል ፤ ከዚያም ፡ በሰላም ፡ ይወጣል ።

13 ፤ በግብጽም ፡ ምድር ፡ ያለውን ፡ የሄልዮቱን ፡ ከተማ ፡ ሐውልቶች ፡ ይሰብራል ፥ የግብጽንም ፡ አማልክት ፡ ቤቶች ፡ በእሳት ፡ ያቃጥላል ።

__________________ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 44 ። _________________

ምዕራፍ ፡ 44 ፤

1 ፤ በግብጽ ፡ ምድር ፡ በሚግዶልና ፡ በጣፍናስ ፡ በሜምፎስም ፡ በጳትሮስም ፡ አገር ፡ ስለተቀመጡ ፡ አይሁድ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

2 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ያመጣኹትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አይታችኋል ፤ እንሆ ፥ ዛሬ ፡ ባድማ ፡ ኾነዋል ፥ የሚቀመጥባቸውም ፡ የለም ።



www.ethiopianorthodox.org

3 ፤ ይህም ፡ የኾነው ፡ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፡ ስላደረጉት ፡ ክፋት ፥ ለማያውቋቸውም ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ ያጥኑ ፡
ዘንድ ፡ ያመልኳቸውም ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ኼዱ ፡ ነው ።

4 ፤ በማለዳም ፡ ተነሥቼ ፡ ባሪያዎቼን ፡ ነቢያትን ፡ ኹሉ ፡ ሰደድኹባችኹና ፦ እንደዚህ ፡ እንደ ፡ ጠላኹት ፡ ያለ ፡ ርኩስ ፡
ነገር ፡ አታድርጉ ፡ አልኳችኹ ።

5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አልሰሙም ፡ ከክፋታቸውም ፡ ተመልሰው ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ እንዳያጥኑ ፡ ጆሯቸውን ፡
አላዘነበሉም ።

6 ፤ ስለዚህ ፥ መዓቴና ፡ ቍጣዬ ፡ ፈሰሱ ፥ በይሁዳም ፡ ከተማዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ነደዱ ፤ ዛሬም ፡
እንደኾነው ፡ ፈረሱ ፡ ባድማም ፡ ኾኑ ።

7 ፤ አኹንም ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከይሁዳ ፡ ወገን ፡ ቅሬታ ፡
እንዳይቀርላችኹ ፥ ወንድንና ፡ ሴትን ፥ ብላቴናንና ፡ ሕፃንን ፡ ከመካከላችኹ ፡ ታጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ክፋት ፡
በራሳችኹ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ ታደርጋላችኹ ፧

8 ፤ ሰውነታችኹንም ፡ ታጠፉ ፡ ዘንድ ፡ በምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ መረገሚያና ፡ መሰደቢያ ፡ ትኾኑ ፡
ዘንድ ፥ ለመቀመጥ ፡ በገባችኹባት ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ በማጠናችኹ ፡ በእጃችኹ ፡ ሥራ ፡
ለምን ፡ ታስቈጡኛላችኹ ፧

9 ፤ በእውኑ ፡ በይሁዳ ፡ ምድርና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ያደረጉትን ፡ የአባቶቻችኹን ፡ ክፋት ፥ የይሁዳንም ፡
ነገሥታት ፡ ክፋት ፥ የሚስቶቻቸውንም ፡ ክፋት ፥ የእናንተንም ፡ ክፋት ፥ የሚስቶቻችኹንም ፡ ክፋት ፡ ረስታችኹታልን ፧

10 ፤ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አልተዋረዱም ፡ አልፈሩምም ፥ በእናንተና ፡ በአባቶቻችኹም ፡ ፊት ፡ ባኖርኹት ፡ ሕጌና ፡
ሥርዐቴ ፡ አልኼዱም ።

11 ፤ ስለዚህም ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ይሁዳን ፡ ኹሉ ፡
አጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ፊቴን ፡ ለክፋት ፡ በላያችኹ ፡ አደርጋለኹ ።

12 ፤ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ በዚያም ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ ፊታቸውን ፡ ያቀኑትን ፡ የይሁዳን ፡ ቅሬታ ፡
እወስዳለኹ ፥ ኹሉም ፡ ይጠፋሉ ፥ በግብጽም ፡ ምድር ፡ ይወድቃሉ ፤ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ ይጠፋሉ ፤ ከታናሹም ፡ ዠምሮ ፡
እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ ይሞታሉ ፤ ለጥላቻና ፡ ለመደነቂያ ፡ ለመረገሚያና ፡ ለመሰደቢያ ፡ ይኾናሉ ።

13 ፤ ኢየሩሳሌምንም ፡ እንደ ፡ ቀጣኹ ፥ እንዲሁ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡
እቀጣለኹ ።

14 ፤ በዚያ ፡ ለመቀመጥ ፡ ወደግብጽ ፡ ምድር ፡ ከኼዱ ፥ ወደይሁዳ ፡ አገር ፡ ተመልሰው ፡ በዚያ ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡
ከሚወዱ ፡ ከይሁዳ ፡ ቅሬታ ፡ ወገን ፡ የሚያመልጥና ፡ የሚቀር ፡ ወደዚያም ፡ የሚመለስ ፡ የለም ፤ ከሚያመልጥም ፡ በቀር ፡
ማንም ፡ አይመለስም ።

15 ፤ ሚስቶቻቸውም ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ ማጠናቸውን ፡ ያወቁ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ በዚያም ፡ የቆሙ ፡ ሴቶች ፡
ኹሉ ፥ በግብጽ ፡ ምድር ፡ በጳትሮስ ፡ የተቀመጡ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ኾነው ፡ ለኤርምያስ ፡ መለሱለት ፡
እንዲህም ፡ አሉ ።

16 ፤ አንተ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የነገርኸንን ፡ ቃል ፡ አንሰማኽም ።

17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እኛና ፡ አባቶቻችን ፡ ነገሥታታችንም ፡ አለቃዎቻችንም ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ በኢየሩሳሌም ፡
አደባባይ ፡ እናደርገው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ ለሰማይ ፡ ንግሥት ፡ እናጥን ፡ ዘንድ ፡ የመጠጥንም ፡ ቍርባን ፡ እናፈስላት ፡ ዘንድ ፡
ከአፋችን ፡ የወጣውን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በርግጥ ፡ እናደርጋለን ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ እንጀራ ፡ እንጠግብ ፡
ነበር ፥ መልካምም ፡ ይኾንልን ፡ ክፉም ፡ አናይም ፡ ነበር ።

18 ፤ ለሰማይ ፡ ንግሥት ፡ ማጠንን ፥ ለርሷም ፡ የመጠጥን ፡ ቍርባን ፡ ማፍሰስን ፡ ከተውን ፡ ወዲህ ፡ ግን ፥ እኛ ፡ በኹሉ ፡
ነገር ፡ ተቸግረናል ፥ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ አልቀናል ።

19 ፤ እኛስ ፡ ለሰማይ ፡ ንግሥት ፡ ባጠንላት ፡ የመጠጥንም ፡ ቍርባን ፡ ባፈሰስንላት ፡ ጊዜ ፥ በእውኑ ፡ ያለባሎቻችን ፡



www.ethiopianorthodox.org

ምስሏን ፡ ለማብጀት ፡ ዕንጐቻ ፡ አድርገንላት ፡ ኖሯልን ፥ የመጠጥንም ፡ ቍርባን ፡ አፍሰንላት ፡ ኖሯልን ፥

20 ፤ ኤርምያስም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ለመለሱለት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ ለወንዶቹና ፡ ለሴቶቹ ፡ ለሕዝቡም ፡
ኹሉ ፥ መለሰላቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ።

21 ፤ እናንተና ፡ አባቶቻችኹ ፡ ነገሥታታችኹም ፡ አለቃዎቻችኹም ፡ የምድርም ፡ ሕዝብ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎችና ፡
በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ያጠናችኹትን ፡ ዕጣን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሰበው ፡ በልቡም ፡ ያኖረው ፡ አይደለምን ፥

22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሥራችኹን ፡ ክፋትና ፡ ያደረጋችኹትን ፡ ርኵሰት ፡ ይታገሥ ፡ ዘንድ ፡
አልቻለም ፤ ስለዚህ ፥ ምድራችኹ ፡ ባድማ ፣ መደነቂያም ፣ መረገሚያም ፡ ኾናለች ፥ ዛሬም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የሚኖርባት ፡
የለም ።

23 ፤ ስላጠናችኹ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ በደላችኹ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ስላልሰማችኹ ፥ በሕጉና ፡
በሥርዐቱም ፡ በምስክሩም ፡ ስላልኼዳችኹ ፥ ስለዚህ ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይህች ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አግኝታችኋለች ።

24 ፤ ኤርምያስም ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ለሴቶቹም ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ በግብጽ ፡ ምድር ፡ የምትኖሩ ፡ ይሁዳ ፡
ኹሉ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

25 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እናንተና ፡ ሚስቶቻችኹ ፡
በአፋችኹ ። ለሰማይ ፡ ንግሥት ፡ እናጥን ፡ ዘንድ ፡ የመጠጥንም ፡ ቍርባን ፡ እናፈስላት ፡ ዘንድ ፡ የተሳልነውን ፡
ስእለታችንን ፡ በርግጥ ፡ እንፈጽማለን ፡ አላችኹ ፡ በእጃችኹም ፡ አደረጋችኹት ፤ እንግዲህ ፡ ስእለታችኹን ፡ አጽኑ ፡
ስእለታችኹንም ፡ ፈጽሙ ።

26 ፤ እናንተ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ የምትኖሩ ፡ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፥ ስለዚህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ በግብጽ ፡
ምድር ፡ ኹሉ ፡ በሚኖር ፡ በይሁዳ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ አፍ ፡ ስሜ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ። ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ተብሎ ፡
እንዳይጠራ ፥ እንሆ ፥ በታላቅ ፡ ስሜ ፡ ምያለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

27 ፤ እንሆ ፥ ለመልካም ፡ ሳይኾን ፡ ለክፋት ፡ እተጋባቸዋለኹ ፤ በግብጽም ፡ ምድር ፡ ያሉት ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡
እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ ያልቃሉ ።

28 ፤ ከሰይፍም ፡ የሚያመልጡ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ኾነው ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ወደይሁዳ ፡ ምድር ፡
ይመለሳሉ ፤ ሊቀመጡም ፡ ወደግብጽ ፡ ምድር ፡ የገቡት ፡ የይሁዳ ፡ ቅሬታ ፡ ኹሉ ፡ ከእኔ ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ የማናችን ፡
ቃል ፡ እንዲጸና ፡ ያውቃሉ ።

29 ፤ ቃሌም ፡ በላያችኹ ፡ ለክፋት ፡ እንዲጸና ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ በዚች ፡ ስፍራ ፡ እንድቀጣችኹ ፡ ምልክታችኹ ፡ ይህ ፡
ነው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

30 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስን ፡ ጠላቱ ፡ ለኾነው ፡ ነፍሱንም ፡ ለፈለገው ፡
ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነጾር ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እንደ ፡ ሰጠኹት ፥ እንዲሁ ፥ እንሆ ፥ የግብጹን ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡
ሖፍራን ፡ ለጠላቶቹ ፡ ነፍሱንም ፡ ለሚፈልጉ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠዋለኹ ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 45 ።

ምዕራፍ ፡ 45 ፤

1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ የኔርያ ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ እነዚህን ፡ ቃሎች ፡
ከኤርምያስ ፡ አፍ ፡ በመጽሐፍ ፡ በጻፋቸው ፡ ጊዜ ፥ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

2 ፤ ባሮክ ፡ ሆይ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይልኻል ።

3 ፤ አንተ ፦ እግዚአብሔር ፡ በሕመሜ ፡ ላይ ፡ ሐዘንን ፡ ጨምሮብኛልና ፥ ወዮልኝ! በልቅሶዬ ፡ ጮኽኹ ፡
ደክሜያለኹ ፥ ዕረፍትንም ፡ አላገኘኹም ፡ ብለኻል ።

4 ፤ እንዲህ ፡ በለው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የሠራኹትን ፡ አፈርሳለኹ ፥ የተከልኹትንም ፡
እነቅላለኹ ፤ ይኸውም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

5 ፤ ለራስኽ ፡ ታላቅን ፡ ነገር ፡ ትፈልጋለኽን ፦ በሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥ እንሆ ፥ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አመጣለኹና ፡
አትፈልገው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኼድኽበት ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ ነፍስኽን ፡ እንደ ፡ ምርኮ ፡ አድርጌ ፡
እሰጥኻለኹ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 46 ።

ምዕራፍ ፡ 46 ፤

1 ፤ ስለ ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

2 ፤ ስለ ፡ ግብጽ ፤ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ በከርከሚሽ ፡ ስለነበረው ፥ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡
በኢዮአቄም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ስለመታው ፡ ስለግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ስለፈርዖን ፡
ኒካው ፡ ሰራዊት ።

3 ፤ ጋሻ ፡ ጦር ፡ አዘጋጁ ፡ ወደ ፡ ሰልፍም ፡ ቅረቡ ።

4 ፤ ፈረሰኛዎች ፡ ሆይ ፥ ፈረሶችን ፡ ለጕሙና ፡ ውጡ ፥ ራስ ፡ ቍርንም ፡ ደፍታችኹ ፡ ቁሙ ፤ ጦርንም ፡ ሰንግሉ ፡
ጥሩርንም ፡ ልበሱ ።

5 ፤ ፈርተው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሲመለሱ ፥ ኀያላናቸውም ፡ ሲደበደቡ ፡ ወደ ፡ ኋላቸውም ፡ ሳይመለከቱ ፡ ፈጥነው ፡ ሲሸሹ ፡
ለምን ፡ አየኹ ፦ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ድንጋጤ ፡ አለ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

6 ፤ ፈጣኑ ፡ አያመልጥም ፡ ኀያሉም ፡ አይድንም ፤ በሰሜን ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ በኩል ፡ ተሰናክለው ፡ ወደቁ ።

7 ፤ ይህ ፡ እንደ ፡ ግብጽ ፡ ወንዝ ፡ የሚነሣ ፥ ውሃውም ፡ እንደ ፡ ወንዝ ፡ የሚናወጥ ፡ ማን ፡ ነው ፦

8 ፤ ግብጽ ፡ እንደ ፡ ግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ይነሣል ፡ ውሃውም ፡ እንደ ፡ ወንዙ ፡ ይናወጣል ፤ ርሱም ፦ እነሣለኹ ፡ ምድርንም ፡
ኹሉ ፡ እከድናለኹ ፤ ከተማዎችንና ፡ የሚኖሩባቸውን ፡ አጠፋለኹ ፡ ብሏል ።

9 ፤ ፈረሶች ፡ ሆይ ፥ ውጡ ፤ ሠረገላዎችም ፡ ሆይ ፥ ንጐዱ ፤ ጋሻም ፡ የሚያነግቡ ፡ የኢትዮጵያና ፡ የፉጥ ፡
ኀያላን ፥ ቀስትንም ፡ ይዘው ፡ የሚስቡ ፡ የሉድ ፡ ኀያላን ፡ ይውጡ ።

10 ፤ ያ ፡ ቀን ፡ ጠላቶቹን ፡ የሚበቀልበት ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የበቀል ፡ ቀን ፡ ነው ፤ ሰይፍ ፡ በልቶ ፡
ይጠግባል ፡ በደማቸውም ፡ ይሰክራል ፥ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሰሜን ፡ ምድር ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡
አጠገብ ፡ መሥዋዕት ፡ አለውና ።

11 ፤ ድንግሊቱ ፡ የግብጽ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ገለዓድ ፡ ውጪ ፥ የሚቀባንም ፡ መድኀኒት ፡ ውሰጂ ፤ መድኀኒትን ፡
ያበዛሽው ፡ በከንቱ ፡ ነው ፤ መዳን ፡ የለሽም ።

12 ፤ ኀያሉ ፡ በኀያሉ ፡ ላይ ፡ ተሰናክሎ ፡ ኹለቱ ፡ በአንድነት ፡ ወድቀዋልና ፥ አሕዛብ ፡ ጕስቍልናሽን ፡
ሰምተዋል ፥ ልቅሶሽም ፡ ምድርን ፡ ሞልቷታል ።

13 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ እንዲመጣና ፡ የግብጽን ፡ ምድር ፡ እንዲመታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለነቢዩ ፡
ለኤርምያስ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

14 ፤ በግብጽ ፡ ተናገሩ ፥ በሚግዶልም ፡ አሰሙ ፥ በሜምፎስና ፡ በጣፍናስ ፡ አሰሙ ፤ ሰይፍ ፡ በዙሪያኽ ፡ ያለውን ፡
በልቷልና ፦ ተነሥ ፡ ተዘጋጅም ፡ በሉ ።

15 ፤ ኀይለኛዎችኽ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተወገዱ ፦ እግዚአብሔር ፡ ስላደከማቸው ፡ አልቆሙም ።

16 ፤ ብዛታቸውም ፡ ተሰናከለ ፥ ሰውም ፡ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፤ እነርሱም ፦ ተነሡ ፥ ከሚያስጨንቅ ፡ ሰይፍ ፡
ፊት ፡ ወደ ፡ ወገናችን ፡ ወደተወለድንባት ፡ ምድር ፡ እንመለስ ፡ አሉ ።

17 ፤ በዚያም ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖንን ፦ ሰዓቱን ፡ የሚያሳልፍ ፡ ጕረኛ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ።

18 ፤ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ በተራራዎች ፡ መካከል ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ ታቦር ፥ በባሕርም ፡ አጠገብ ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡
ቀርሜሎስ ፥ እንዲሁ ፡ በእውነት ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባለው ፡ ንጉሥ ።



www.ethiopianorthodox.org

19 ፤ አንቺ ፡ በግብጽ ፡ የምትቀመጪ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ሜምፎስ ፡ ባድማ ፡
ትኾናለችና ፥ ትቃጠልማለችና ፥ የሚቀመጥባትም ፡ አይገኝምና ፡ ለምርኮ ፡ የሚኾን ፡ ዕቃ ፡ አዘጋጂ ።

20 ፤ ግብጽ ፡ የተዋበች ፡ ጊደር ፡ ናት ፤ ጥፋት ፡ ግን ፡ ይመጣል ፥ ከሰሜን ፡ በኩል ፡ ይመጣባታል ።

21 ፤ በርሷም ፡ ያሉ ፡ የተቀጠሩ ፡ ሠራተኛዎች ፡ እንደ ፡ ሰቡ ፡ ወይፈኖች ፡ ናቸው ፤ የጥፋታቸው ፡ ቀንና ፡
የመጐብኘታቸው ፡ ጊዜ ፡ መጥቶባቸዋልና ፥ ተመለሱ ፥ በአንድነትም ፡ ሸሹ ፥ አልቆሙምም ።

22 ፤ ከሰራዊትም ፡ ጋራ ፡ ይኼዳሉና ፥ ድምፅ ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ይተማል ፤ እንደ ፡ ዕንጨት ፡ ቈራጮችም ፡ በምሣር ፡
ይመጡባታል ።

23 ፤ ይቈጠሩ ፡ ዘንድ ፡ የማይቻሉትን ፡ የዱሯን ፡ ዛፎች ፡ ይቈርጣሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ከአንበጣ ፡ ይልቅ ፡
በዝተዋልና ፥ ቍጥርም ፡ የላቸውምና ።

24 ፤ የግብጽ ፡ ልጅ ፡ ታፍራለች ፤ በሰሜን ፡ ሕዝብ ፡ እጅ ፡ ዐልፋ ፡ ትሰጣለች ።

25 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የኖእ ፡
ዐሞንን ፥ ፈርዖንንም ፥ ግብጽንም ፥ አማልክቷንና ፡ ነገሥታቷንም ፥ ፈርዖንና ፡ በርሱም ፡ የሚታመኑትን ፡ እቀጣለኹ ፤

26 ፤ ነፍሳቸውንም ፡ በሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፥ በባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነጾር ፡ እጅ ፥ በባሪያዎቹም ፡ እጅ ፡
አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ዘመን ፡ የሰው ፡ መኖሪያ ፡ ትኾናለች ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ።

27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንተ ፡ ባሪያዬ ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ አትፍራ ፥ አንተም ፡ እስራኤል ፡
ሆይ ፥ አትደንግጥ ፤ እንሆ ፥ አንተን ፡ ከሩቅ ፡ ዘርኽንም ፡ ከተማረከባት ፡ ምድር ፡ አድናለኹ ፤ ያዕቆብም ፡ ተመልሶ ፡
ያርፋል ፡ ተዘልሎም ፡ ይቀመጣል ፥ ማንም ፡ አያስፈራውምም ።

28 ፤ አንተ ፡ ባሪያዬ ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ አትፍራ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ አንተንም ፡
ያሰደድኹባቸውን ፡ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሜ ፡ አጠፋለኹና ፥ አንተን ፡ ግን ፡ ፈጽሜ ፡ አላጠፋኽም ፤ በመጠን ፡
እቀጣኻለኹ ፥ ያለቅጣትም ፡ አልተውኽም ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 47 ።

ምዕራፍ ፡ 47 ፤

1 ፤ ፈርዖንም ፡ ጋዛን ፡ ሳይመታ ፡ ስለ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡
ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

2 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ውሃ ፡ ከሰሜን ፡ ይነሣል ፡ የሚያጥለቀልቅም ፡ ፈሳሽ ፡
ይኾናል ፤ በአገሪቱና ፡ በመላዋ ፡ ኹሉ ፥ በከተማዪቱና ፡ በሚኖሩባት ፡ ላይ ፡ ይጐርፋል ፤ ሰዎቹም ፡
ይጮኻሉ ፥ በምድርም ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ያለቅሳሉ ።

3 ፤ ከኀይለኛዎች ፡ ፈረሶች ፡ ከኰቴያቸው ፡ መጠብጠብ ፡ ድምፅ ፥ ከሠረገላዎቹም ፡ መሸከርከር ፥ ከመንኰራኵሮቹም ፡
መትመም ፡ የተነሣ ፡ አባቶች ፡ በእጃቸው ፡ ድካም ፡ ምክንያት ፡ ፊታቸውን ፡ መልሰው ፡ ወደ ፡ ልጆቻቸው ፡
አይመለከቱም ።

4 ፤ ይህም ፡ የሚኾነው ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ ኹሉ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ የቀሩትንም ፡ ረዳቶች ፡ ኹሉ ፡ ከጢሮስና ፡ ከሲዶና ፡
ይቈርጥ ፡ ዘንድ ፡ ስለሚመጣው ፡ ቀን ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ፍልስጥኤማውያንና ፡ የከፍቶርን ፡ ደሴት ፡ ቅሬታ ፡
ያጠፋልና ።

5 ፤ ቡሓነት ፡ በጋዛ ፡ ላይ ፡ መጥቷል ፤ አስቀሎና ፡ ጠፋች ፤ የዔናቅ ፡ ቅሬታዎች ፡ ሆይ! እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡
ገላችኹን ፡ ትነጫላችኹ ፨

6 ፤ አንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰይፍ ፡ ሆይ ፥ ዝም ፡ የማትለው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፨ ወደ ፡ ሰገባኽ ፡ ግባ ፡ ጸጥ ፡
ብለኽም ፡ ዕረፍ ።



www.ethiopianorthodox.org

7 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአስቀሎናና ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ላይ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቷልና ፥ በዚያም ፡ አዘጋጅቶታልና ፥ እንዴት ፡ ዝም ፡
ትላለኽ ፧

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 48 ።

ምዕራፍ ፡ 48 ፤

1 ፤ ስለ ፡ ሞዐብ ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ናባው ፡ ጠፍታለችና ፡
ወዮላት! ቂርያታይም ፡ ዐፍራለች ፡ ተይዛማለች ፤ ሚሥጋብ ፡ ዐፍራለች ፡ ደንግጣማለች ።

2 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሞዐብ ፡ ትምክሕት ፡ የለም ፤ በሐሴቦን ፡ ላይ ፦ ኑ ፥ ሕዝብ ፡ እንዳትኾን ፡ እናጥፋት ፡ ብለው ፡
ክፉ ፡ ነገር ፡ ዐስበውባታል ። መድሜን ፡ ሆይ ፥ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ ትጠፊያለሽ ፡ ሰይፍም ፡ ያሳድድሻል ።

3 ፤ መፍረስና ፡ ታላቅ ፡ ጥፋት ፡ የሚል ፡ የጩኸት ፡ ቃል ፡ ከሖሮናይም ፡ ተሰማ ።

4 ፤ ሞዐብ ፡ ጠፍታለች ፥ ልጆቿም ፡ ጩኸትን ፡ አሰምተዋል ።

5 ፤ በሉሒት ፡ ዐቀበት ፡ ልቅሶ ፡ እያለቀሱ ፡ ይወጣሉና ፥ በሖሮናይምም ፡ ቍልቍለት ፡ የጥፋትንና ፡ የመባባትን ፡ ጩኸት ፡
ሰምተዋል ።

6 ፤ ሽሹ፡ ፡ ራሳችኹን ፡ አድኑ ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳለ ፡ ቍጥቋጦ ፡ ኹኑ ።

7 ፤ በሥራሽና ፡ በመዝገብሽ ፡ ታምነሻልና ፥ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ ትያዢያለሽ ፤ ካሞሽም ፡ ከካህናቱና ፡ ከአለቃዎቹ ፡ ጋራ ፡
በአንድነት ፡ ይማረካል ።

8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፥ አጥፊ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ኹሉ ፡ ይመጣል ፡ አንዲትም ፡ ከተማ ፡
አትድንም ፤ ሸለቆውም ፡ ይጠፋል ፡ ሜዳውም ፡ ይበላሻል ።

9 ፤ በራ ፡ እንድትወጣ ፡ ለሞዐብ ፡ ክንፍ ፡ ስጧት ፤ ከተማዎቿም ፡ ባድማና ፡ ወና ፡ ይኾናሉ ።

10 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ በቸልታ ፡ የሚያደርግ ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፥ ሰይፉንም ፡ ከደም ፡ የሚከለክል ፡ ርጉም ፡
ይኹን ።

11 ፤ ሞዐብ ፡ ከታናሽነቱ ፡ ዠምሮ ፡ ቅምጥል ፡ ነበረ ፥ በአምቡላውም ፡ ላይ ፡ ዐርፏል ፥ ከዕቃውም ፡ ወደ ፡ ዕቃ ፡
አልተገላበጠም ፥ ወደ ፡ ምርኮም ፡ አልኼደም ፤ ስለዚህ ፥ ቃናው ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ቀርቷል ፥ መዐዛውም ፡
አልተለወጠም ።

12 ፤ ስለዚህ ፥ እነሆ ፥ የሚያገላብጡትን ፡ የምልክበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ እነርሱም ፡
ያገላብጡታል ፤ ጋኖቹንም ፡ ባዶ ፡ ያደርጋሉ ፥ መስቴዎቹንም ፡ ይሰብራሉ ።

13 ፤ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ይታመንባት ፡ ከነበረው ፡ ከቤቴል ፡ እንዳፈረ ፥ እንዲሁ ፡ ሞዐብ ፡ ከካሞሽ ፡ ያፍራል ።

14 ፤ እናንተ ፦ እኛ ፡ ኀያላን ፡ በሰልፍም ፡ ጽኑዓን ፡ ነን ፡ እንዴት ፡ ትላላችኹ ፧

15 ፤ ሞዐብ ፡ ፈርሷል ፥ ከተማዎቹም ፡ ጠፍተዋል ፥ የተመረጡትም ፡ ጕልማሳዎች ፡ ወደ ፡ መታረድ ፡
ወርደዋል ፥ ይላል ፡ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የኾነ ፡ ንጉሥ ።

16 ፤ የሞዐብ ፡ ጥፋት ፡ ሊመጣ ፡ ቀርቧል ፡ መከራውም ፡ እጅግ ፡ ይፈጥናል ።

17 ፤ በዙሪያው ፡ ያላችኹ ፡ ኹሉ ፡ ስሙንም ፡ የምታውቁ ፡ ኹሉ ፦ ብርቱው ፡ በትር ፥ የከበረው ፡ ሽመል ፥ እንዴት ፡
ተሰበረ! ብላችኹ ፡ አልቅሱለት ።

18 ፤ በዲቦን ፡ የምትኖሪ ፡ ሆይ ፥ ሞዐብን ፡ የሚያጠፋ ፡ ወጥቶብሻልና ፥ ዐምባሽንም ፡ ሰብሯልና ፥ ከክብርሽ ፡
ውረጂ ፥ በጥማትም ፡ ተቀመጪ ።

19 ፤ በዐሮዔር ፡ የምትኖሪ ፡ ሆይ ፥ በመንገድ ፡ አጠገብ ፡ ቆመሽ ፡ ተመልከቺ ፤ የሸሸውንና ፡ ያመለጠችውን ፦ ምን ፡
ኾኗል ፧ ብለሽ ፡ ጠይቂ ።

20 ፤ ሞዐብም ፡ ፈርሷልና ፥ ዐፈረ ፤ አልቅሱ ፡ ጩኹም ፤ ሞዐብ ፡ እንደ ፡ ተዘረፈ ፡ በአርኖን ፡ አጠገብ ፡ አውሩ ።



www.ethiopianorthodox.org

21 ፤ በሜዳ ፡ ላይ ፥ በሖሎን ፥ በያሳ ፥ በሜፍዓት ፡ ላይ ፥

22 ፤ በዲቦን ፥ በናባው ፥ በቤት ፡ ዲብላታይም ፡ ላይ ፥

23 ፤ በቂርያታይም ፥ በቤትጋሙል ፥

24 ፤ በቤትምዖን ፡ ላይ ፥ በቂርዮት ፥ በባሶራ ፥ በሞዐብም ፡ ምድር ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ቅርብና ፡ ሩቅ ፡ በኾኑ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ መጥቷል ።

25 ፤ የሞዐብ ፡ ቀንድ ፡ ተቈረጠ ፡ ክንዱም ፡ ተሰበረ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

26 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኰርቷልና ፥ አስክሩት ፤ ሞዐብም ፡ በጥፋቱ ፡ ላይ ፡ ይንከባለላል ፥ ደግሞም ፡ መሳቂያ ፡ ይኾናል ።

27 ፤ እስራኤል ፡ ለአንተ ፡ መሳቂያ ፡ አልኾነምን ፥ ወይስ ፡ በሌባዎች ፡ መካከል ፡ ተገኝቷልን ፥ ስለ ፡ ርሱ ፡ በተናገርኽ ፡ ጊዜ ፡ ራስኽን ፡ ትነቀንቃለኽ ።

28 ፤ እናንተ ፡ በሞዐብ ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ ከተማዎችን ፡ ትታችኹ ፡ በአለት ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ፥ በገደል ፡ አፉፍም ፡ ቤቷን ፡ እንደምትሠራ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ ኹኑ ።

29 ፤ እጅግ ፡ እንደ ፡ ታበየ ፡ ስለሞዐብ ፡ ትዕቢት ፡ ስለ ፡ ትምክሕቱም ፡ ስለ ፡ ኵራቱም ፡ ስለ ፡ መጓደዱም ፡ ስለልቡም ፡ ትዕቢት ፡ ሰምተናል ።

30 ፤ ቍጣው ፡ ምንም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቃለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ፉከራው ፡ ምንም ፡ አልሠራም ።

31 ፤ ስለዚህ ፥ ለሞዐብ ፡ አለቅሳለኹ ፥ ለሞዐብም ፡ ኹሉ ፡ እጮኻለኹ ፤ ለቂርሔሬስ ፡ ሰዎች ፡ አለቅሳለኹ ።

32 ፤ አንቺ ፡ የሴባማ ፡ ወይን ፡ ሆይ ፥ ከኢያዜር ፡ ልቅሶ ፡ ይልቅ ፡ ለአንቺ ፡ አለቅሳለኹ ፤ ቅርንጫፎችሽ ፡ ባሕርን ፡ ተሻግረዋል ፥ ወደኢያዜርም ፡ ባሕር ፡ ደርሰዋል ፤ አጥፊው ፡ በሰብልሽና ፡ በወይንሽ ፡ ላይ ፡ መጥቷል ።

33 ፤ ሐሤትና ፡ ደስታ ፡ ከፍሬያማው ፡ ዕርሻና ፡ ከሞዐብ ፡ ምድር ፡ ጠፍተዋል ፤ ጠጁን ፡ ከመጥመቂያው ፡ አጥፍቻለኹ ፤ ጠማቂውም ፡ በእልልታ ፡ አይጠምቅም ፥ እልልታቸውም ፡ እልልታ ፡ አይኾንም ።

34 ፤ ከሐሴቦን ፡ ጩኸት ፡ እስከ ፡ ኤልያሌና ፡ እስከ ፡ ያሀጽ ፡ ድረስ ፡ ድምፃቸውን ፡ ሰጥተዋል ፤ ከዞዓር ፡ እስከ ፡ ሖሮናይምና ፡ እስከ ፡ ዔግላት ፡ ሺሊሺያ ፡ ድረስ ፡ ይደርሳል ፤ የኔምሬም ፡ ውሃ ፡ ደግሞ ፡ ይደርቃል ።

35 ፤ በኰረብታው ፡ መስገጃ ፡ ላይ ፡ የሚሠዋውን ፡ ለአማልክቱም ፡ የሚያጥነውን ፡ ከሞዐብ ፡ አጠፋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

36 ፤ ያተረፈው ፡ ትርፉ ፡ ጠፍቶበታልና ፤ ስለዚህ ፥ ልቤ ፡ ለሞዐብ ፡ እንደ ፡ እንቢልታ ፡ ይጮኻል ፥ ልቤም ፡ ለቂርሔሬስ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ እንቢልታ ፡ ይጮኻል ።

37 ፤ ራስ ፡ ኹሉ ፡ መላጣ ፡ ጢምም ፡ ኹሉ ፡ የተላጨ ፡ ነውና ፤ በእጅም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ክትፋት ፡ በወገብም ፡ ላይ ፡ ማቅ ፡ አለና ።

38 ፤ ሞዐብን ፡ እንደማይወደድ ፡ ዕቃ ፡ ሰብሬያለኹና ፡ በሞዐብ ፡ ሰገነት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በአደባባዩም ፡ ላይ ፡ በኹሉም ፡ ቦታ ፡ ልቅሶ ፡ አለ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

39 ፤ እንዴት ፡ ተገለበጠ! በዕፍረትም ፡ የተነሣ ፡ ሞዐብ ፡ ዠርባውን ፡ እንዴት ፡ መለሰ! ብላችኹ ፡ አልቅሱ ። ሞዐብም ፡ በዙሪያው ፡ ላሉት ፡ ኹሉ ፡ መሳቂያና ፡ ድንጋጤ ፡ ይኾናል ።

40 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ እንደ ፡ ንስር ፡ ይበራል ፡ ክንፉንም ፡ በሞዐብ ፡ ላይ ፡ ይዘረጋል ።

41 ፤ ከተማዎቹ ፡ ተይዘዋል ፥ ዐምባዎቹም ፡ ተወስደዋል ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ የሞዐብ ፡ ኀያላን ፡ ልብ ፡ ምጥ ፡ እንደ ፡ ያዛት ፡ ሴት ፡ ልብ ፡ ይኾናል ።

42 ፤ ሞዐብም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኰርቷልና ፥ ሕዝብ ፡ ከመኾን ፡ ይጠፋል ።

43 ፤ በሞዐብ ፡ የምትኖር ፡ ሆይ ፥ ፍርሀትና ፡ ጕድጓድ ፡ ወጥመድም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ አለ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።



www.ethiopianorthodox.org

44 ፤ በሞዐብ ፡ ላይ ፡ የመጐብኘትን ፡ ዓመት ፡ አመጣበታለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ በፍርሀት ፡ የሸሸ ፡
በጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ይወድቃል ፥ ከጕድጓድም ፡ የወጣ ፡ በወጥመድ ፡ ይያዛል ።

45 ፤ የሸሹ ፡ ደክመው ፡ ከሐሴቦን ፡ ጥላ ፡ በታች ፡ ቆመዋል ፤ እሳት ፡ ከሐሴቦን ፡ ነበልባልም ፡ ከሴዎን ፡ ወጥቷል ፡
የሞዐብንም ፡ ማእዘን ፡ የሤትንም ፡ ልጆች ፡ ዐናት ፡ በልቷል ።

46 ፤ ሞዐብ ፡ ሆይ ፥ ወዮልኽ! የካሞሽ ፡ ወገን ፡ ጠፍቷል ፤ ወንዶች ፡ ልጆችኽ ፡ ተማርከዋልና ፥ ሴቶች ፡ ልጆችኽም ፡
ወደ ፡ ምርኮ ፡ ኼደዋልና ።

47 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ የሞዐብን ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። የሞዐብ ፡ ፍርድ ፡
እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 49 ።

ምዕራፍ ፡ 49 ፤

1 ፤ ስለዐሞን ፡ ልጆች ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የሉትምን ፧ ወይስ ፡ ወራሽ ፡
የለውምን ፧ ስለ ፡ ምን ፡ ሚልኮም ፡ ጋድን ፡ ወረሰ ፧ ሕዝቡስ ፡ በከተማዎቹ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተቀመጠ ፧

2 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ በዐሞን ፡ ልጆች ፡ ከተማ ፡ በረባት ፡ ላይ ፡ የሰልፍ ፡ ውካታን ፡ የማሰማበት ፡ ዘመን ፡
ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ የፍርስራሽ ፡ ክምርም ፡ ትኾናለች ፥ ሴቶች ፡ ልጆቿም ፡ በእሳት ፡
ይቃጠላሉ ፥ እስራኤልም ፡ የወረሱትን ፡ ይወርሳል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

3 ፤ ሐሴቦን ፡ ሆይ ፥ ጋይ ፡ ፈርሳለችና ፡ አልቅሺላት ፡ እናንተም ፡ የረባት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ሚልኮም ፡ ካህናቱና ፡
አለቃዎቹም ፡ በአንድነት ፡ ይማረካሉና ፡ ጩኹ ፥ ማቅም ፡ ታጠቁ ፥ አልቅሱም ፥ በቅጥሮችም ፡ መካከል ፡ ተሯሯጡ ።

4 ፤ ማን ፡ ይመጣብኛል ፡ ብለሽ ፡ በመዝገብሽ ፡ የታመንሽ ፡ አንቺ ፡ ከዳተኛ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በሸለቆዎችሽ ፥ ውሃ ፡
በሚያረካቸው ፡ ሸለቆዎችሽ ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ትመኪያለሽ ፧

5 ፤ እንሆ ፥ በዙሪያሽ ፡ ካሉት ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ፍርሀትን ፡ አመጣብሻለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡
እግዚአብሔር ፤ እያንዳንዳችኹም ፡ በፊታችኹ ፡ ወዳለው ፡ ስፍራ ፡ ትሰደዳላችኹ ፥ የሚሸሹትንም ፡ የሚሰበስብ ፡ የለም ።

6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የዐሞንን ፡ ልጆች ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

7 ፤ ስለ ፡ ኤዶምያስ ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእውኑ ፡ በቴማን ፡ ጥበብ ፡
የለምን ፧ ከብልኅተኛዎችስ ፡ ምክር ፡ ጠፍቷልን ፧

8 ፤ ጥበባቸውስ ፡ አልቋልን ፧ እናንተ ፡ በድዳን ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ የዔሳውን ፡ ጥፋት ፥ የምጐበኝበትን ፡
ጊዜ ፥ አመጣበታለኹና ፡ ሽሹ ፥ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመለሱ ፥ በጥልቅም ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ።

9 ፤ ወይን ፡ ለቃሚዎች ፡ ቢመጡብኽ ፥ ቃርሚያውን ፡ አይተውልኽምን ፧ ሌባዎችስ ፡ በሌሊት ፡ ቢመጡ ፥ የሚያጠፉት ፡
እስኪበቃቸው ፡ ድረስ ፡ አይደለምን ፧

10 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ዔሳውን ፡ ዐራቈትኹት ፥ የተሸሸጉትንም ፡ ስፍራዎች ፡ ገለጥኹ ፥ ይሸሸግም ፡ ዘንድ ፡
አይችልም ፤ ዘሩም ፡ ወንድሞቹም ፡ ጎረቤቶቹም ፡ ጠፍተዋል ፡ ርሱም ፡ የለም ።

11 ፤ ድኻ ፡ አደጎችኽን ፡ ተው ፥ እኔም ፡ በሕይወት ፡ አኖራቸዋለኹ ፤ መበለቶችኽም ፡ በእኔ ፡ ይታመኑ ።

12 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ ጽዋውን ፡ ያልተገባቸው ፡ ሰዎች ፡ ጠጥተውታል ፤ አንተም ፡ ሳትቀጣ ፡
ትቀራለኽን ፧ በርግጥ ፡ ትጠጣለኽ ፡ እንጂ ፡ ያለቅጣት ፡ አትቀርም ።

13 ፤ ባሶራ ፡ መደነቂያና ፡ መሰደቢያ ፡ መረገሚያም ፡ እንድትኾን ፡ በራሴ ፡ ምያለኹ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ፤ ከተማዎቿም ፡ ኹሉ ፡ ለዘለዓለም ፡ ባድማ ፡ ይኾናሉ ።

14 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወሬ ፡ ሰምቻለኹ ፡ በአሕዛብም ፡ መካከል ። ተሰብሰቡ ፥ በርሷም ፡ ላይ ፡ ኑ ፡ ለሰልፍም ፡
ተነሡ ፡ የሚል ፡ መልእክተኛ ፡ ተልኳል ።

15 ፤ እንሆ ፥ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ የተጠቃኽ ፥ በሰዎችም ፡ ዘንድ ፡ የተናቅኽ ፡ አድርጌኻለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

16 ፤ በአለት ፡ ንቃቃት ፡ ውስጥ ፡ የምትቀመጥ ፥ የተራራውን ፡ ከፍታ ፡ የምትይዝ ፡ ሆይ ፥ ድፍረትኽና ፡ የልብኽ ፡
ኵራት ፡ አታለውኻል ። ቤትኽን ፡ ምንም ፡ እንደ ፡ ንስር ፡ ከፍ ፡ ብታደርግ ፥ ከዚያ ፡ አወርድኻለኹ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ።

17 ፤ ኤዶምያስም ፡ መደነቂያ ፡ ትኾናለች ፥ የሚያልፍባትም ፡ ኹሉ ፡ ይደነቃል ፥ ስለመጣባትም ፡ መቅሠፍት ፡ ኹሉ ፡
ያፏጭባታል ።

18 ፤ ሰዶምና ፡ ገሞራ ፡ በእነርሱም ፡ አጠገብ ፡ የነበሩት ፡ ከተማዎች ፡ እንደ ፡ ተገለበጡ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ፥ እንዲሁ ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ አይቀመጥም ፡ የሰው ፡ ልጅም ፡ አይኖርባትም ።

19 ፤ እንሆ ፥ ከርሷ ፡ ዘንድ ፡ በቶሎ ፡ አባርራቸዋለኹና ፡ በጠነከረው ፡ ዐምባ ፡ ላይ ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ትዕቢት ፡ ውስጥ ፡
እንደ ፡ አንበሳ ፡ ይወጣል ፤ የተመረጠውንም ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ እሾመዋለኹ ፤ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ወይስ ፡
ለእኔ ፡ ጊዜ ፡ የሚወስን ፡ ማን ፡ ነው ፧ ወይስ ፡ ፊቴን ፡ የሚቃወም ፡ እረኛ ፡ ማን ፡ ነው ፧

20 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ በኤዶምያስ ፡ ላይ ፡ የመከረባትን ፡ ምክር ፥ በቴማንም ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ያሰባትን ፡
ዐሳብ ፡ ስሙ ፤ በእውነት ፡ የመንጋ ፡ ትንንሾች ፡ ይጐተታሉ ፤ በእውነት ፡ ማደሪያቸውን ፡ ባድማ ፡ ያደርግባቸዋል ።

21 ፤ ከመውደቃቸው ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ተናወጠች ፥ የጩኸታቸውም ፡ ድምፅ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ተሰማ ።

22 ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ ንስር ፡ ወጥቶ ፡ ይበራል ፡ ክንፉንም ፡ በባሶራ ፡ ላይ ፡ ይዘረጋል ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ የኤዶምያስ ፡
ኀያላን ፡ ልብ ፡ ምጥ ፡ እንደ ፡ ያዛት ፡ ሴት ፡ ልብ ፡ ይኾናል ።

23 ፤ ስለ ፡ ደማስቆ ፤ ክፉ ፡ ወሬ ፡ ሰምተዋልና ፥ ሐማትና ፡ አርፋድ ፡ ዐፈሩ ፥ ቀለጡም ፤ በባሕርም ፡ ላይ ፡ ሐዘን ፡
አለ ፥ ታርፍም ፡ ዘንድ ፡ አትችልም ።

24 ፤ ደማስቆ ፡ ደከመች ፡ ትሸሽም ፡ ዘንድ ፡ ዘወር ፡ አለች ፡ እንቅጥቅጥም ፡ ያዛት ፥ እንደ ፡ ወላድም ፡ ሴት ፡ ጣርና ፡
ምጥ ፡ ያዛት ።

25 ፤ የተመሰገነችው ፡ ከተማ ፥ የደስታዬ ፡ ከተማ ፥ ሳትለቀቅ ፡ እንዴት ፡ ቀረች ፧

26 ፤ ስለዚህ ፥ ጐበዛዝቷ ፡ በአደባባይዋ ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰልፈኞዎች ፡ ኹሉ ፡ ይጠፋሉ ፥ ይላል ፡
የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

27 ፤ በደማስቆም ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ አነዳለኹ ፡ የወልደ ፡ አዴርንም ፡ አዳራሾች ፡ ትበላለች ።

28 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ስለ ፡ መታ ፡ ስለቄዳርና ፡ ስለአሶር ፡ መንግሥታት ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፦ ተነሡ ፡ ወደ ፡ ቄዳርም ፡ ውጡ ፥ የምሥራቅንም ፡ ልጆች ፡ አጥፉ ።

29 ፤ ድንኳናቸውንና ፡ መንጋቸውን ፡ ይወስዳሉ ፤ መጋረጃዎቻቸውንና ፡ ዕቃቸውን ፡ ኹሉ ፡ ግመሎቻቸውንም ፡
ለራሳቸው ፡ ይወስዳሉ ፥ በዙሪያቸውም ፡ ኹሉ ፡ ጥፋትን ፡ ጥሩባቸው ።

30 ፤ እናንተ ፡ በአሶር ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ተማክሮባችኋልና ፥ ዐሳብም ፡
ዐስቦባችኋልና ፥ ሽሹ ፥ ወደ ፡ ሩቅም ፡ ኺዱ ፥ በጥልቅም ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

31 ፤ ተነሡ ፥ ዕርፊት ፡ ወዳለበት ፡ ተዘልሎም ፡ ወደተቀመጠው ፥ ደጅና ፡ መወርወሪያ ፡ ወደሌለው ፡ ብቻውንም ፡
ወደተቀመጠው ፡ ሕዝብ ፡ ውጡ ።

32 ፤ ግመሎቻቸው ፡ ይበዘበዛሉ ፡ የእንስሳዎቻቸውም ፡ ብዛት ፡ ይማረካል ፤ ጠጕራቸውንም ፡ በዙሪያ ፡ የሚላጩትን ፡
ሰዎች ፡ ወደ ፡ ነፋሳት ፡ ኹሉ ፡ እበትናቸዋለኹ ፤ ከዳርቻቸውም ፡ ኹሉ ፡ ጥፋት ፡ አመጣባቸዋለኹ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ።

33 ፤ አሶርም ፡ የቀበሮ ፡ መኖሪያና ፡ የዘለዓለም ፡ ባድማ ፡ ትኾናለች ፤ በዚያም ፡ ሰው ፡ አይኖርም ፥ የሰው ፡ ልጅም ፡
አይቀመጥባትም ።

34 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሴዴቅያስ ፡ መንግሥት ፡ መዠመሪያ ፡ ስለ ፡ ዔላም ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡
የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦



www.ethiopianorthodox.org

35 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ዋና ፡ የኀይላቸው ፡ መሣሪያ ፡ የኾነውን ፡ የዔላምን ፡ ቀስት ፡ እሰብራለኹ ።

36 ፤ ከአራቱም ፡ ከሰማይ ፡ ማእዘናት ፡ አራቱን ፡ ነፋሳት ፡ በዔላም ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ፥ ወደ ፡ እነዚያም ፡ ነፋሳት ፡ ዅሉ ፡ እበትናቸዋለኹ ፤ ከዔላም ፡ የተሰደዱ ፡ ሰዎች ፡ የማይደርሱበት ፡ ሕዝብ ፡ አይገኝም ።

37 ፤ በጠላቶቻቸውና ፡ ነፍሳቸውን ፡ በሚሿት ፡ ፊት ፡ ዔላምን ፡ አስደነግጣለኹ ፤ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ርሱም ፡ ጽኑ ፡ ቍጣዬን ፡ አመጣባቸዋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እስካጠፋቸውም ፡ ድረስ ፡ በኋላቸው ፡ ሰይፍ ፡ እሰድባቸዋለኹ ፤

38 ፤ ዙፋኔንም ፡ በዔላም ፡ አኖራለኹ ፥ ከዚያም ፡ ንጉሡንና ፡ አለቃዎቹን ፡ አጠፋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

39 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ የዔላምን ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 50 ።

ምዕራፍ ፡ 50 ፤

1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለከለዳውያን ፡ ምድር ፡ ስለ ፡ ባቢሎን ፡ በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

2 ፤ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ተናገሩ ፡ አውሩም ፥ ዐላማውንም ፡ አንሡ ፤ አውሩ ፥ አትደብቁ ። ባቢሎን ፡ ተወሰደች ፥ ቤል ፡ ዐፈረ ፥ ሜሮዳክ ፡ ደነገጠ ፤ ምስሎቿ ፡ ዐፈሩ ፥ ጣዖታቷ ፡ ደነገጡ ፡ በሉ ።

3 ፤ ሕዝብ ፡ ከሰሜን ፡ ወጥቶባታል ፡ ምድሯንም ፡ ባድማ ፡ ያደርጋል ፥ የሚቀመጥባትም ፡ አይገኝም ፤ ከሰው ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ድረስ ፡ ሸሽተው ፡ ኼደዋል ።

4 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ በዚያም ፡ ጊዜ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ በአንድነት ፡ ኾነው ፡ ይመጣሉ ፥ እያለቀሱም ፡ መንገዳቸውን ፡ ይኼዳሉ ፥ አምላካቸውንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈልጋሉ ።

5 ፤ ፊታቸውንም ፡ ወደዚያ ፡ አቅንተው ፦ ኑ ፥ ከቶ ፡ በማይረሳ ፡ በዘለዓለም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጠጉ ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ጽዮን ፡ መንገድ ፡ ይጠይቃሉ ።

6 ፤ ሕዝቤ ፡ የጠፉ ፡ በጎች ፡ ኾነዋል ፤ እረኞዎቻቸው ፡ አሳቷቸው ፥ በተራራዎችም ፡ ላይ ፡ የተቅበዘበዙ ፡ አደረጓቸው ፤ ከተራራ ፡ ወደ ፡ ኰረብታ ፡ ዐለፉ ፥ በረታቸውንም ፡ ረሱ ።

7 ፤ ያገኟቸው ፡ ዅሉ ፡ በሏቸው ፥ ጠላቶቻቸውም ፦ በጽድቅ ፡ ማደሪያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፥ በአባቶቻቸው ፡ ተስፋ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ እኛ ፡ አልበደልንም ፡ አሉ ።

8 ፤ ከባቢሎን ፡ መካከል ፡ ሽሹ ፥ ከከለዳውያንም ፡ ድር ፡ ውጡ ፥ በመንጋዎችም ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፡ ኹኑ ።

9 ፤ እንሆ ፥ ከሰሜን ፡ ምድር ፡ የታላላቅ ፡ አሕዛብን ፡ ጉባኤ ፡ አስነሣለኹ ፡ በባቢሎንም ፡ ላይ ፡ አመጣቸዋለኹ ፤ በርሷም ፡ ላይ ፡ ይሰለፋሉ ፥ ከዚያም ፡ ትወሰዳለች ፤ ፍላጻዎቻቸውም ፡ ባዶውን ፡ እንደማይመለስ ፡ እንደ ፡ ብልኅ ፡ ዠግና ፡ ፍላጻ ፡ ናቸው ።

10 ፤ የከላውዴዎንም ፡ ምድር ፡ ትበዘበዛለች ፥ የሚበዘብዟትም ፡ ዅሉ ፡ ይጠግባሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

11 ፤ ርስቴን ፡ የምትበዘብዙ ፡ እናንተ ፡ ሆይ ፥ ደስ ፡ ብሏችኋልና ፥ ሐሤትንም ፡ አድርጋችኋልና ፥ በመስክ ፡ ላይም ፡ እንዳለች ፡ ጊደር ፡ ኾናችኹ ፡ ተቀናጥታችኋልና ፥ እንደ ፡ ብርቱዎችም ፡ ፈረሶች ፡ አሽካክታችኋልና ፥

12 ፤ እናታችኹ ፡ እጅግ ፡ ታፍራለች ፥ የወለደቻችኹም ፡ ትጐስቍላለች ፤ እንሆ ፥ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ኋለኛዪቱ ፡ ትኾናለች ፤ ምድረ ፡ በዳና ፡ ደረቅ ፡ ምድር ፡ በረሓም ፡ ትኾናለች ።

13 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ የተነሣ ፡ ባድማ ፡ ትኾናለች ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ አይቀመጥባትም ፤ በባቢሎንም ፡ በኩል ፡ የሚያልፍ ፡ ዅሉ ፡ ይደነቃል ፡ በመጣባትም ፡ መቅሠፍት ፡ ዅሉ ፡ ያፏጫል ።

14 ፤ እናንተ ፡ ቀስትን ፡ የምትገትሩ ፡ ሰዎች ፡ ዅሉ ፥ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ በዙሪያዋ ፡ ተሰለፉ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርታለችና ፡ ወርውሩባት ፡ ፍላጻዎችንም ፡ አትንፈጉ ።



www.ethiopianorthodox.org

15 ፤ የእግዚአብሔር ፡ በቀል ፡ ነውና ፥ በዙሪያዋ ፡ ጩኹባት ፤ እጇን ፡ ሰጠች ፤ ግንቦቿ ፡ ወደቁ ፡ ቅጥሮቿም ፡
ፈረሱ ፤ ርሷን ፡ ተበቀሉ ፡ እንደ ፡ ሠራችውም ፡ ሥሩባት ።

16 ፤ ዘሪውንና ፡ በመከር ፡ ጊዜ ፡ ማጭድ ፡ የሚይዘውን ፡ ከባቢሎን ፡ አጥፉ ፤ ከሚያስጨንቅ ፡ ሰይፍ ፡ ፊት ፡ እያንዳንዱ ፡
ወደ ፡ ወገኑ ፡ ይመለሳል ፡ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይሸሻል ።

17 ፤ እስራኤል ፡ የባዘነ ፡ በግ ፡ ነው ፤ አንበሳዎች ፡ አሳደዱት ፤ መዠመሪያ ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ በላው ፥ በመጨረሻም ፡
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ዐጥንቱን ፡ ቈረጠመው ።

18 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የአሶርን ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡
ቀጣኹ ፡ እንዲሁ ፥ እንሆ ፥ የባቢሎንን ፡ ንጉሥና ፡ ምድሩን ፡ እቀጣለኹ ።

19 ፤ እስራኤልንም ፡ ወደ ፡ ማሰማሪያው ፡ እመልሳለኹ ፥ በቀርሜሎስና ፡ በባሳንም ፡ ላይ ፡ ይሰማራል ፥ ሰውነቱም ፡
በኤፍሬም ፡ ተራራና ፡ በገለዓድ ፡ ላይ ፡ ትጠግባለች ።

20 ፤ እነዚህን ፡ ያስቀረኋቸውን ፡ ይቅር ፡ እላቸዋለኹና ፡ በዚያን ፡ ወራት ፡ በዚያም ፡ ዘመን ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ፥ የእስራኤል ፡ በደል ፡ የይሁዳም ፡ ኀጢአት ፡ ይፈለጋል ፡ ምንም ፡ አይገኝም ።

21 ፤ በምራታይም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በፋቁድም ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ ውጣ ፤ ግደላቸው ፡ ፈጽመኽም ፡ አጥፋቸው ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ፥ እንዳዘዝኹኽም ፡ ኹሉ ፡ አድርግ ።

22 ፤ የሰልፍና ፡ የታላቅ ፡ ጥፋት ፡ ውካታ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አለ ።

23 ፤ የምድር ፡ ኹሉ ፡ መዶሻ ፡ እንዴት ፡ ደቀቀ ፥ እንዴትስ ፡ ተሰበረ! ባቢሎንስ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ እንዴት ፡
ባድማ ፡ ኾነች!

24 ፤ ባቢሎን ፡ ሆይ ፥ አጥምጄብሻለኹ ፥ አንቺም ፡ ሳታውቂ ፡ ተይዘሻል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ተዋጋሽ ፡
ተገኝተሻል ፥ ተይዘሽማል ።

25 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በከለዳውያን ፡ ምድር ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ሥራ ፡ አለውና ፥ እግዚአብሔር ፡ ዕቃ ፡
ቤቱን ፡ ከፍቶ ፡ የቊጣውን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ አውጥቷል ።

26 ፤ ከየበኩሉ ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ውጡ ፥ ጐተራዎቿንም ፡ ክፈቱ ፤ እንደ ፡ ክምርም ፡ አድርጓት ፥ ፈጽማችኹም ፡
አጥፏት ፥ አንዳችም ፡ አታስቀሩላት ።

27 ፤ ወይፈኖቿን ፡ ኹሉ ፡ ዕረዱ ፥ ወደ ፡ መታረድም ፡ ይውረዱ ፤ ቀናቸው ፣ የመጐብኘታቸው ፡ ጊዜ ፡
ደርሷልና ፥ ወዮላቸው!

28 ፤ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በቀል ፡ የመቅደሱንም ፡ በቀል ፡ በጽዮን ፡ ይነግሩ ፡ ዘንድ ፥ ሸሽተው ፡
ከባቢሎን ፡ አገር ፡ ያመለጡት ፡ ሰዎች ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቷል ።

29 ፤ ቀስትን ፡ የሚገትሩትን ፡ ቀስተኛዎችን ፡ ኹሉ ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ጥሯቸው ፤ በዙሪያዋ ፡ ስፈሩባት ፡ አንድም ፡
አያምልጥ ፤ በእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኰርታለችና ፥ እንደ ፡ ሥራዋ ፡ መጠን ፡
መልሱላት ፥ እንዳደረገችም ፡ ኹሉ ፡ አድርጉባት ።

30 ፤ ስለዚህ ፥ ጕበዛዝቷ ፡ በአደባባይዋ ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰልፈኛዎቿ ፡ ኹሉ ፡ ይጠፋሉ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ።

31 ፤ ትዕቢተኛው ፡ ሆይ ፥ የመጐብኘትኽ ፡ ጊዜ ፥ ቀንኽ ፡ ደርሷልና ፥ እንሆ ፥ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

32 ፤ ትዕቢተኛው ፡ ተሰናክሎ ፡ ይወድቃል ፡ የሚያነሣውም ፡ የለም ፤ በከተማዎቹም ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡
አነዻለኹ ፥ በዙሪያውም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ትበላለች ።

33 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ በአንድነት ፡
ተገፍተዋል ፥ የማረኳቸውም ፡ ኹሉ ፡ በኀይል ፡ ይይዟቸዋል ፥ ይለቋቸውም ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ብለዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

34 ፤ ተቤዢያቸው ፡ ብርቱ ፡ ነው ፥ ስሙም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ ምድርንም ፡ ያሳርፍ ፡ ዘንድ ፥ በባቢሎንም ፡ የሚኖሩትን ፡ ያውክ ፡ ዘንድ ፥ ሙግታቸውን ፡ ፈጽሞ ፡ ይሟገታል ።

35 ፤ ሰይፍ ፡ በከለዳውያንና ፡ በባቢሎን ፡ በሚኖሩ ፡ ላይ ፥ በአለቃዎቿና ፡ በጥበበኞዎቿ ፡ ላይ ፡ አለ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

36 ፤ ሰይፍ ፡ በሚንደዱት ፡ ላይ ፡ አለ ፡ ሰነፎችም ፡ ይኾናሉ ፥ ሰይፍም ፡ በኀያላኗ ፡ ላይ ፡ አለ ፡ እነርሱም ፡ ይደነግጣሉ ።

37 ፤ ሰይፍ ፡ በፈረሶቻቸውና ፡ በሠረገላዎቻቸው ፡ ላይ ፡ በመካከሏም ፡ ባሉት ፡ በልዩ ፡ በልዩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አለ ፥ እነርሱም ፡ እንደ ፡ ሴቶች ፡ ይኾናሉ ፤ ሰይፍም ፡ በመዝገቧ ፡ ላይ ፡ አለ ፡ ለብዝበዛም ፡ ይኾናል ።

38 ፤ ርሷ ፡ የተቀረጹ ፡ ምስሎች ፡ ምድር ፡ ናት ፥ እነርሱም ፡ በጣዖታት ፡ ይመካሉና ፥ ድርቅ ፡ በውሃዎቿ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፥ እነርሱም ፡ ይደርቃሉ ።

39 ፤ ስለዚህ ፥ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፡ ከተኵላዎች ፡ ጋራ ፡ ይቀመጡባታል ፥ ሰጐኖችም ፡ ይቀመጡባታል ፤ ሰውም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ለዘለዓለም ፡ አይቀመጥባትም ፥ እስከልጅ ፡ ልጅም ፡ ድረስ ፡ የሚኖርባት ፡ የለም ።

40 ፤ ሰዶምንና ፡ ገሞራን ፡ በአጠገባቸውም ፡ የነበሩትን ፡ ከከተማዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ገለበጣቸው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ እንዲሁ ፡ ሰው ፡ በዚያ ፡ አይቀመጥም ፡ የሰውም ፡ ልጅ ፡ አይኖርባትም ።

41 ፤ እንሆ ፥ ሕዝብ ፡ ከሰሜን ፡ ይመጣል ፤ ታላቅ ፡ ሕዝብና ፡ ብዙ ፡ ነገሥታትም ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ይነሣሉ ።

42 ፤ ቀስትንና ፡ ጦርን ፡ ይይዛሉ ፤ ጨካኞች ፡ ናቸው ፥ ምሕረትም ፡ አያደርጉም ፤ ድምፃቸው ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ይተማል ፥ በፈረሶችም ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ ። የባቢሎን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ለሰልፍ ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ሰው ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ተሰለፉ ።

43 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወሬያቸውን ፡ ሰምቷል ፥ እጁም ፡ ደክማለች ፥ ጭንቀትም ፡ ይዞታል ፥ ምጥ ፡ ወላድ ፡ ሴትን ፡ እንደሚይዛት ፡ ጭንቀት ፡ ይዞታል ።

44 ፤ እንሆ ፥ ከርሷ ፡ ዘንድ ፡ በቶሎ ፡ አባርራቸዋለኹና ፥ በጠነከረው ፡ ዐምባ ፡ ላይ ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ትዕቢት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ይወጣል ፤ የተመረጠውንም ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ እሾመዋለኹ ፤ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ለእኔ ፡ ጊዜ ፡ የሚወስን ፡ ማን ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ፊቴን ፡ የሚቃወም ፡ እረኛ ፡ ማን ፡ ነው ፡

45 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ የመከረባትን ፡ ምክር ፥ በከለዳውያንም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ያሰባትን ፡ ዐሳብ ፡ ስሙ ፤ በእውነት ፡ የመንጋ ፡ ትናንሾች ፡ ይጐተታሉ ፤ በእውነት ፡ ማደሪያቸውን ፡ ባድማ ፡ ያደርግባቸዋል ።

46 ፤ ከባቢሎን ፡ መያዝ ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ተናወጠች ፥ ጩኸትም ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ዘንድ ፡ ተሰማ ።

____________________ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 51 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 51 ፤

1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በባቢሎን ፡ ላይና ፡ በከለዳውያን ፡ ምድር ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ አጥፊውን ፡ ነፋስ ፡ አስነሣለኹ ።

2 ፤ በባቢሎንም ፡ ላይ ፡ የሚያዘሩትን ፡ ሰዎች ፡ እሰዳለኹ ፤ እነርሱም ፡ ያዘሯታል ፥ ምድሯንም ፡ ባዶ ፡ ያደርጋሉ ፤ በመከራም ፡ ቀን ፡ በዙሪያዋ ፡ ይከቧታል ።

3 ፤ በወርዋሪው ፡ ላይ ፡ በጥሩርም ፡ በሚነሣው ፡ ላይ ፡ ቀስተኛው ፡ ቀስቱን ፡ ይገትር ፤ ለጐበዛዝቷ ፡ አትዘኑ ፡ ሰራዊቷንም ፡ ኹሉ ፡ አጥፉ ።

4 ፤ በከለዳውያንም ፡ ምድር ፡ ተገድለው ፥ በሜዳዋም ፡ ላይ ፡ ተወግተው ፡ ይወድቃሉ ።

5 ፤ ምድራቸው ፡ በእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ በተሠራው ፡ በደል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የተሞላች ፡ ብትኾን ፥ እስራኤልም ፡ ኾነ ፡ ይሁዳ ፡ በአምላኩ ፡ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አልተጣለም ።

6 ፤ ከባቢሎን ፡ ውስጥ ፡ ሽሹ ፥ እያንዳንዳችኹም ፡ ነፍሳችኹን ፡ አድኑ ፤ በበደሏ ፡ አትጥፉ ፥ የእግዚአብሔር ፡ በቀል ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፥ ርሱም ፡ ብድራቷን ፡ ይከፍላታልና ።



www.ethiopianorthodox.org

7 ፤ ባቢሎን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ውስጥ ፡ ምድርን ፡ ኹሉ ፡ ያሰከረች ፡ የወርቅ ፡ ጽዋ ፡ ነበረች ፥ አሕዛብም ፡ ከጠጁ ፡ ጠጥተዋል ፤ ስለዚህ ፥ አሕዛብ ፡ አብደዋል ።

8 ፤ ባቢሎን ፡ በድንገት ፡ ወድቃ ፡ ጠፍታለች ፤ አልቅሱላት ፥ ትፈወስም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለቍስሏ ፡ መድኀኒት ፡ ውሰዱላት ።

9 ፤ ባቢሎንን ፡ ፈወስናት ፥ ርሷ ፡ ግን ፡ አልተፈወሰችም ፤ ፍርዷ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ደርሷልና ፥ እስከ ፡ ደመናም ፡ ድረስ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ፥ ትታችኋት ፡ እያንዳንዳችን ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ እንኺድ ።

10 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጽድቃችንን ፡ አውጥቷል ፤ ኑ ፥ በጽዮን ፡ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ እንናገር ።

11 ፤ ፍላጻዎችን ፡ ሳሉ ፡ ጋሻዎችንም ፡ አዘጋጁ ፤ እግዚአብሔር ፡ ያጠፋት ፡ ዘንድ ፡ ዐሳቡ ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ነውና ፥ የሜዶንን ፡ ነገሥታት ፡ መንፈስ ፡ አስነሥቷል ፤ የእግዚአብሔር ፡ በቀል ፡ የመቅደሱ ፡ በቀል ፡ ነውና ።

12 ፤ በባቢሎን ፡ ቅጥር ፡ ዐላማውን ፡ አንሡበት ፥ ጥበቃን ፡ አጽኑ ፥ ተመልካቾችን ፡ አቁሙ ፥ ድብቅ ፡ ጦር ፡ አዘጋጁ ። እግዚአብሔር ፡ በባቢሎን ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ የተናገረውን ፡ ዐስቧልና ፥ አድርጓልምና ።

13 ፤ አንቺ ፡ በብዙ ፡ ውሃ ፡ አጠገብ ፡ የተቀመጥሽ ፥ በመዝገብም ፡ የበለጠግሽ ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡ ሥሥትሽ ፡ መጠን ፡ ፍጻሜሽ ፡ ደርሷል ።

14 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በራሱ ፡ ምሏል ፦ በእውነት ፡ ሰዎችን ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፡ እሞላብሻለኹ ፥ እነርሱም ፡ ጩኸት ፡ ያነሡብሻል ።

15 ፤ ምድርን ፡ በኀይሉ ፡ የፈጠረ ፥ ዓለሙን ፡ በጥበቡ ፡ የመሠረተ ፥ ሰማያትንም ፡ በማስተዋሉ ፡ የዘረጋ ፡ ርሱ ፡ ነው ።

16 ፤ ድምፁን ፡ ባሰማ ፡ ጊዜ ፡ ውሃዎች ፡ በሰማይ ፡ ይታወካሉ ፥ ከምድርም ፡ ዳር ፡ ደመናትን ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፤ ለዝናብም ፡ መብረቅን ፡ ያደርጋል ፥ ነፍስንም ፡ ከቤተ ፡ መዛግብቱ ፡ ያወጣል ።

17 ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ዕውቀት ፡ ዐጥቶ ፡ ሰንፏል ፥ አንጥረኛም ፡ ኹሉ ፡ ከቀረጸው ፡ ምስል ፡ የተነሣ ፡ አፍሯል ፤ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምስሉ ፡ ውሸት ፡ ነውና ፥ እስትንፋስም ፡ የላቸውምና ።

18 ፤ እነርሱም ፡ ምናምንቴና ፡ የቀልድ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ፤ በተጐበኙ ፡ ጊዜ ፡ ይጠፋሉ ።

19 ፤ የያዕቆብ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ እነዚህ ፡ አይደለም ፥ ርሱ ፡ የኹሉ ፡ ፈጣሪ ፡ ነውና ፤ እስራኤልም ፡ የርስቱ ፡ ነገድ ፡ ነው ፥ ስሙም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

20 ፤ አንቺ ፡ መዶሻዬና ፡ የጦር ፡ መሣሪያዬ ፡ ነሽ ፤ ባንቺ ፡ አሕዛብን ፡ እሰባብራለኹ ፤ ባንቺም ፡ መንግሥታትን ፡ አጠፋለኹ ፤

21 ፤ ባንቺ ፡ ፈረሱንና ፡ ፈረሰኛውን ፡ እሰባብራለኹ ፤

22 ፤ ባንቺም ፡ ሠረገላውንና ፡ በላዩ ፡ የሚቀመጠውን ፡ እሰባብራለኹ ፤ ባንቺም ፡ ወንድንና ፡ ሴትን ፡ እሰባብራለኹ ፤ ባንቺም ፡ ሽማግሌውንና ፡ ብላቴናውን ፡ እሰባብራለኹ ፤ ባንቺም ፡ ጕልማሳውንና ፡ ቈንጆዪቱን ፡ እሰባብራለኹ ፤

23 ፤ ባንቺም ፡ እረኛውንና ፡ መንጋውን ፡ እሰባብራለኹ ፤ ባንቺም ፡ አራሹንና ፡ ጥማጁን ፡ እሰባብራለኹ ፤ ባንቺም ፡ አለቃዎችንና ፡ ሹማምቶችን ፡ እሰባብራለኹ ።

24 ፤ በጽዮን ፡ በዐይናችኹ ፡ ፊት ፡ ስለሠሩት ፡ ክፋታቸው ፡ ኹሉ ፡ በባቢሎንና ፡ በከለዳውያን ፡ ምድር ፡ በሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ፍዳቸውን ፡ እከፍላለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

25 ፤ አንተ ፡ ምድርን ፡ ኹሉ ፡ የምታጠፋ ፡ አጥፊ ፡ ተራራ ፡ ሆይ ፥ እነሆ ፥ እኔ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እጄንም ፡ እዘረጋብኻለኹ ፥ ከድንጋዮችም ፡ ላይ ፡ አንከባልልኻለኹ ፥ የተቃጠለም ፡ ተራራ ፡ አደርግኻለኹ ።

26 ፤ ከአንተም ፡ ለማእዘንና ፡ ለመሠረት ፡ የሚኾን ፡ ድንጋይ ፡ አይወስዱም ፥ ለዘለዓለምም ፡ ባድማ ፡ ትኾናለኽ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።



www.ethiopianorthodox.org

27 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ዐላማን ፡ አንሡ ፡ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ መለከት ፡ ንፉ ፥ አሕዛብንም ፡
አዘጋጁባት ፤ የአራራትንና ፡ የሚኒን ፡ የአስከናዝንም ፡ መንግሥታት ፡ ሰብስቡባት ፡ አለቃንም ፡ በላይዋ ፡ አቁሙ ፤ እንደ ፡
ጠጕራም ፡ ኵብኵባ ፡ ፈረሶችን ፡ በላይዋ ፡ አውጡ ።

28 ፤ አሕዛብን ፡ የሚዶንንም ፡ ነገሥታት ፡ አለቃዎችንም ፡ ሹማምቶችንም ፡ ኹሉ ፡ የግዛታቸውንም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡
አዘጋጁባት ።

29 ፤ ማንም ፡ እንዳይቀመጥባት ፡ የባቢሎንን ፡ ምድር ፡ ባድማ ፡ ያደርጋት ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዐሳብ ፡ በባቢሎን ፡
ላይ ፡ ጸንቷልና ፥ ምድር ፡ ተናውጣለች ፡ ታመመችም ።

30 ፤ የባቢሎን ፡ ኀያላን ፡ መዋጋትን ፡ ትተዋል ፡ በዐምባዎቻቸውም ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠዋል ፤ ኀይላቸውም ፡ ጠፍቷል ፡
እንደ ፡ ሴቶችም ፡ ኾነዋል ፤ ማደሪያዎቿም ፡ ነደዋል ፡ መወርወሪያዎቿም ፡ ተሰብረዋል ።

31–32 ፤ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ከተማው ፡ እንደ ፡ ተያዘች ፡ መልካሞቿም ፡ እንደ ፡ ተያዙ ፥ ቅጥሯም ፡ በእሳት ፡
እንደ ፡ ተቃጠለ ፥ ሰልፈኛዎችም ፡ እንደ ፡ ደነገጡ ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ይነግር ፡ ዘንድ ፡ ወሬኛው ፡ ወሬኛውን ፡
መልእክተኛውም ፡ መልእክተኛውን ፡ ሊገናኝ ፡ ይሮጣል ።

33 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ዐውድማ ፡ እንደ ፡ ተረገጠ ፡
ጊዜ ፥ እንዲሁ ፡ የባቢሎን ፡ ልጅ ፡ ናት ፤ ጥቂት ፡ ቈይታ ፡ የመከር ፡ ጊዜ ፡ ይደርስባታል ።

34 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ በላኝ ፥ ከፋፈለኝም ፥ እንደ ፡ ባዶ ፡ ዕቃም ፡ አደረገኝ ፥ እንደ ፡ ዘንዶም ፡
዗ጠኝ ፥ ከሚጣፍጠውም ፡ ምግቤ ፡ ሆዱን ፡ ሞላ ፥ እኔንም ፡ ጣለኝ ።

35 ፤ በጽዮን ፡ የምትቀመጥ ፦ በእኔና ፡ በሥጋዬ ፡ የተደረገ ፡ ግፍ ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ይኹን ፡
ትላለች ፤ ኢየሩሳሌምም ፦ ደሜ ፡ በከለዳውያን ፡ ምድር ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ ይኹን ፡ ትላለች ።

36 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ እሟገትልሻለኹ ፡ በቀልሽንም ፡ እበቀልልሻለኹ ፤ ባሕሯንም ፡
ድርቅ ፡ አደርገዋለኹ ፡ ምንጯንም ፡ አደርቀዋለኹ ።

37 ፤ ባቢሎንም ፡ የድንጋይ ፡ ቊልልና ፡ የቀበሮ ፡ ማደሪያ ፡ መደነቂያም ፡ ማፏጫም ፡ ትኾናለች ፥ የሚቀመጥባትም ፡
ሰው ፡ አይገኝም ።

38 ፤ በአንድነትም ፡ እንደ ፡ አንበሳዎች ፡ ያገሣሉ ፥ እንደ ፡ አንበሳም ፡ ደቦሎች ፡ ያጕረመርማሉ ።

39 ፤ በሞቃቸው ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ እንዲላቸው ፡ ለዘለዓለምም ፡ አንቀላፍተው ፡ እንዳይነቁ ፡ የመጠጥ ፡ ግብዣ ፡
አደርግላቸዋለኹ ፡ አሰክራቸውማለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

40 ፤ እንደ ፡ ጠቦቶችና ፡ እንደ ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ እንደ ፡ አውራ ፡ ፍየሎችም ፡ ወደ ፡ መታረድ ፡ አወርዳቸዋለኹ ።

41 ፤ ሼሻክ ፡ እንዴት ፡ ተያዘች! የምድርም ፡ ኹሉ ፡ ምስጋና ፡ እንዴት ፡ ተወሰደች! ባቢሎንም ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡
መደነቂያ ፡ እንዴት ፡ ኾነች!

42 ፤ ባሕር ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ በሞገዱም ፡ ብዛት ፡ ተከደነች ።

43 ፤ ከተማዎቿ ፡ ባድማና ፡ ደረቅ ፡ ምድር ፡ ምድረ ፡ በዳም ፥ ሰውም ፡ የማይቀመጥበት ፡ የሰውም ፡ ልጅ ፡ የማያልፍበት ፡
ምድር ፡ ኾኑ ።

44 ፤ በባቢሎንም ፡ ውስጥ ፡ ቤልን ፡ እቀጣለኹ ፡ የዋጠውንም ፡ ከአፉ ፡ አስተፋዋለኹ ፤ አሕዛብም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡
ወደ ፡ ርሱ ፡ አይሰበሰቡም ፥ የባቢሎንም ፡ ቅጥር ፡ ይወድቃል ።

45 ፤ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ ከመካከሏ ፡ ውጡ ፡ እያንዳንዳችኹም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ራሳችኹን ፡ አድኑ ።

46 ፤ በምድርም ፡ ከሚሰማ ፡ ወሬ ፡ የተነሣ ፡ አትፍሩ ፡ ልባችኹም ፡ የዛለ ፡ አይኹን ፤ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ወሬ ፡
ይመጣል ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በሌላው ፡ ዓመት ፡ ወሬ ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ ይመጣል ፥ አለቃም ፡ በአለቃ ፡ ላይ ፡
ይነሣል ።

47 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ የተቀረጹትን ፡ የባቢሎን ፡ ምስሎች ፡ የምቀጣበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ምድሯም ፡ ኹሉ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ታፍራለች ፤ ተወግተውም ፡ የሞቱት ፡ ኹሉ ፡ በመካከሏ ፡ ይወድቃሉ ።

48 ፤ አጥፊዎች ፡ ከሰሜን ፡ ይመጡባታልና ፥ ሰማይና ፡ ምድር ፡ በእነርሱም ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ባቢሎን ፡ እልል ፡ ይላሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

49 ፤ ባቢሎንም ፡ ከእስራኤል ፡ ተወግተው ፡ የሞቱት ፡ እንዲወድቁ ፡ እንዳደረገች ፥ እንዲሁ ፡ በባቢሎን ፡ ከምድሩ ፡ ኹሉ ፡ ተወግተው ፡ የሞቱት ፡ ይወድቃሉ ።

50 ፤ ከሰይፍ ፡ ያመለጣችኹ ፡ ሆይ ፥ ኺዱ ፥ አትቁሙ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከሩቅ ፡ ዐስቡ ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡ በልባችኹ ፡ ዐስቡ ።

51 ፤ ስድብን ፡ ስለ ፡ ሰማን ፡ ዐፍረናል ፤ ባዕዳን ፡ ሰዎችም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብተዋልና ፥ ነውር ፡ ፊታችንን ፡ ከድኖታል ።

52 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ የተቀረጹትን ፡ ምስሎቿ ፡ የምቀጣበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ በምድሯም ፡ ላይ ፡ ኹሉ ፡ የተወጉት ፡ ያንቋርራሉ ።

53 ፤ ባቢሎን ፡ ምንም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ብትወጣ ፥ የኀይሏንም ፡ ከፍታ ፡ ብታጸና ፥ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ አጥፊዎች ፡ ይመጡባታል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

54 ፤ ከባቢሎን ፡ ጩኸት ፥ ከከለዳውያንም ፡ ምድር ፡ የታላቅ ፡ ጥፋት ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቷል ።

55 ፤ እግዚአብሔር ፡ ባቢሎንን ፡ አጥፍቷታልና ፥ ከርሷም ፡ ታላቁን ፡ ድምፅ ፡ ዝም ፡ አሠኝቷልና ፤ ሞገዳቸውም ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሃዎች ፡ ይተማል ፥ የድምፃቸውም ፡ ጩኸት ፡ ተሰምቷል ።

56 ፤ አጥፊው ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ መጥቶባታልና ፥ ኀያላኗ ፡ ተያዙ ፥ ቀስታቸውም ፡ ተሰባበረ ፤ እግዚአብሔር ፡ ፍዳን ፡ የሚከፍል ፡ አምላክ ፡ ነውና ፥ ፍዳንም ፡ በርግጥ ፡ ይከፍላል ።

57 ፤ መሳፍንቷንና ፡ ጥበበኞዎቿንም ፥ አለቃዎቿንና ፡ ሹማምቷን ፡ ኀያላኗንም ፡ አሰክራለኹ ፥ ለዘለዓለምም ፡ አንቀላፍተው ፡ አይነቁም ፥ ይላል ፡ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባለው ፡ ንጉሥ ።

58 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰፊው ፡ የባቢሎን ፡ ቅጥር ፡ ፈጽሞ ፡ ይፈርሳል ፡ ረዣዥሞችም ፡ በሮቿ ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላሉ ፤ የወገኖችም ፡ ድካም ፡ ከንቱ ፡ ትኾናለች ፥ የአሕዛብም ፡ ሥራ ፡ ለእሳት ፡ ትኾናለች ፤ እነርሱም ፡ ይደክማሉ ።

59 ፤ የመሕሤያ ፡ ልጅ ፡ የኔርያ ፡ ልጅ ፡ ሰራያ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በነገሠ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ያዘዘው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። ሰራያም ፡ የቤት ፡ አዛዥ ፡ ነበረ ።

60 ፤ በባቢሎንም ፡ ላይ ፡ የሚመጣውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ ስለ ፡ ባቢሎን ፡ የተጻፈውን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፥ ኤርምያስ ፡ በመጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ጻፈው ።

61 ፤ ኤርምያስም ፡ ሰራያን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ በገባኽ ፡ ጊዜ ፡ እይ ፥ ይህንም ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ አንብና ፦

62 ፤ አቤቱ ፥ ከሰው ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ እንዳይቀመጥባት ፥ ለዘለዓለምም ፡ ባድማ ፡ እንድትኾን ፡ ታጠፉት ፡ ዘንድ ፡ በዚች ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተናግረኻል ፡ በል ።

63 ፤ ይህንም ፡ መጽሐፍ ፡ ማንበብ ፡ ከፈጸምኽ ፡ በኋላ ፥ ድንጋይን ፡ እሰርበት ፡ በኤፍራጥስም ፡ ውስጥ ፡ ጣለው ፤

64 ፤ አንተም ፦ እኔ ፡ ከማመጣባት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ የተነሣ ፡ እንዲሁ ፡ ባቢሎን ፡ ትሰጥማለች ፡ አትነሣምም ፡ በል ። የኤርምያስ ፡ ቃል ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

## ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 52 ።

ምዕራፍ ፡ 52 ፤

1 ፤ ሴዴቅያስ ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ዐሚጣል ፡ የተባለች ፡ የሊብና ፡ ሰው ፡ የኤርምያስ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።



www.ethiopianorthodox.org

2 ፤ ኢዮአቄምም ፡ እንዳደረገ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

3 ፤ ከፊቱም ፡ አውጥቶ ፡ እስኪጥላቸው ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡
ኾኗልና ፤ ሴዴቅያስም ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ።

4 ፤ ሴዴቅያስም ፡ በነገሠ ፡ በዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ በዐሥረኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥረኛው ፡ ቀን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡
ናቡከደነጾርና ፡ ሰራዊቱ ፡ ኹሉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ መጥተው ፡ ከበቧት ፡ በዙሪያዋም ፡ ዕርድ ፡ አደረገ ።

5 ፤ ከተማዪቱም ፡ እስከ ፡ ንጉሡ ፡ እስከ ፡ ሴዴቅያስ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ተከባ ፡ ነበር ።

6 ፤ በአራተኛውም ፡ ወር ፡ በዘጠነኛው ፡ ቀን ፡ በከተማዪቱ ፡ ራብ ፡ ጸንቶ ፡ ነበር ፥ ለአገሩም ፡ ሰዎች ፡ እንጀራ ፡ ታጣ ።

7 ፤ ከተማዪቱም ፡ ተሰበረች ፥ ሰልፈኛዎችም ፡ ኹሉ ፡ ሸሹ ፥ በኹለቱም ፡ ቅጥር ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ በር ፡ ወደንጉሡ ፡
አትክልት ፡ በሚወስደው ፡ መንገድ ፡ በሌሊት ፡ ከከተማዪቱ ፡ ወጡ ። ከለዳውያንም ፡ በከተማዪቱ ፡ ዙሪያ ፡
ነበሩ ፤ በዐረባም ፡ መንገድ ፡ ኼዱ ።

8 ፤ የከለዳውያንም ፡ ሰራዊት ፡ ንጉሡን ፡ ተከታተሉት ፥ በኢያሪኮም ፡ ሜዳ ፡ ሴዴቅያስን ፡ ያዙ ፤ ሰራዊቱም ፡ ኹሉ ፡
ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተበትነው ፡ ነበር ።

9 ፤ ንጉሡንም ፡ ይዘው ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወዳለባት ፡ በሐማት ፡ ምድር ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ሪብላ ፡
አመጡት ፤ ርሱም ፡ ፍርድን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተናገረ ።

10 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ የሴዴቅያስን ፡ ልጆች ፡ በፊቱ ፡ ገደላቸው ፥ የይሁዳንም ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ደግሞ ፡ በሪብላ ፡
ገደላቸው ።

11 ፤ የሴዴቅያስንም ፡ ዐይኖች ፡ አወጣ ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በሰንሰለት ፡ አሰረው ፡ ወደ ፡ ባቢሎንም ፡
ወሰደው ፥ እስኪሞትም ፡ ድረስ ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አኖረው ።

12 ፤ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነጾር ፡ በዐሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ በዐምስተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥረኛው ፡
ቀን ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ፊት ፡ የቆመው ፡ የዘበኛዎቹ ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ።

13 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ አቃጠለ ፤ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቤቶች ፡ ኹሉ ፥ ታላላቆችን ፡ ቤቶች ፡
ኹሉ ፥ በእሳት ፡ አቃጠለ ።

14 ፤ ከዘበኛዎቹም ፡ አለቃ ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ የከለዳውያን ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ቅጥር ፡ ኹሉ ፡ ዙሪያዋን ፡
አፈረሱ ።

15 ፤ የዘበኛዎቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ የሕዝቡን ፡ ድኻዎች ፥ በከተማም ፡ ውስጥ ፡ የቀረውን ፡ ሕዝብ ፥ ሸሽተውም ፡
ወደባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የተጠጉትን ፥ የሕዝቡንም ፡ ቅሬታ ፡ አፈለሰ ።

16 ፤ የዘበኛዎቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፥ ከአገሩ ፡ ድኻዎች ፥ ወይን ፡ ተካዮችና ፡ ዐራሾች ፡ እንዲኾኑ ፥ አስቀረ ።

17 ፤ ከለዳውያንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የነበሩትን ፡ የናስ ፡ ዐምዶች ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የነበሩትን ፡
መቀመጫዎችና ፡ የናሱን ፡ ኵሬ ፡ ሰባበሩ ፥ ናሱንም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰዱ ።

18 ፤ ምንቸቶቹንና ፡ መጫሪያዎችንም ፡ መኰስተሪያዎችንና ፡ ድስቶችን ፡ ጭልፋዎችንም ፡ የሚያገለግሉበትንም ፡ የናስ ፡
ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ወሰዱ ።

19 ፤ የዘበኛዎቹም ፡ አለቃ ፡ ጽዋዎቹንና ፡ ማንደጃዎቹን ፡ ድስቶቹንና ፡ ምንቸቶችን ፡ መቅረዞችንና ፡ ጭልፋዎቹን ፡
መንቀሎችንም ፥ የወርቁን ፡ ዕቃ ፡ በወርቅ ፥ የብሩንም ፡ ዕቃ ፡ በብር ፡ አድርጎ ፥ ወሰደ ።

20 ፤ ንጉሡ ፡ ሰሎሞንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ያሠራቸውን ፡ ኹለቱን ፡ ዐምዶች ፥ አንዱንም ፡
ኵሬ ፥ ከመቀመጫዎቹም ፡ በታች ፡ የነበሩትን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ የናስ ፡ በሬዎች ፡ ወሰደ ፤ ለእነዚህ ፡ ዕቃዎች ፡ ኹሉ ፡
ናስ ፡ ሚዛን ፡ አልነበረም ።

21 ፤ ዐምዶቹም ፥ የአንዱ ፡ ዐምድ ፡ ቁመት ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የዙሪያውም ፡ መጠን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡
ክንድ ፡ ነበረ ፤ ውፍረቱም ፡ አራት ፡ ጣት ፡ ያኽል ፡ ነበረ ፥ ባዶም ፡ ነበረ ።



www.ethiopianorthodox.org

22 ፤ የናሱም ፡ ጕልላት ፡ በላዩ ፡ ነበረ ፤ የአንዱም ፡ ጕልላት ፡ ቁመት ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ በጕልላቱም ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ኹሉ ፡ ከናስ ፡ የተሠሩ ፡ መረበብና ፡ ሮማኖች ፡ ነበሩበት ፤ በኹለተኛውም ፡ ዐምድ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገርና ፡ ሮማኖች ፡ ነበሩበት ።

23 ፤ በስተውጭም ፡ ዘጠና ፡ ስድስት ፡ ሮማኖች ፡ ነበሩ ። በመረበቡም ፡ ዙሪያ ፡ የነበሩ ፡ ሮማኖች ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

24 ፤ የዘበኞዎቹም ፡ አለቃ ፡ ታላቁን ፡ ካህን ፡ ሰራያን ፡ ኹለተኛውንም ፡ ካህን ፡ ሶፎንያስን ፡ ሦስቱንም ፡ በረኞዎች ፡ ወሰደ ፤

25 ፤ ከከተማዪቱም ፡ በሰልፈኞዎች ፡ ላይ ፡ ተሾመው ፡ ከነበሩት ፡ አንዱን ፡ ጃን ፡ ደረባ ፥ በከተማዪቱም ፡ ከሚገኙት ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ከሚቆሙት ፡ ሰባቱን ፡ ሰዎች ፥ የአገሩንም ፡ ሕዝብ ፡ የሚያሰልፈውን ፡ የሰራዊቱን ፡ አለቃ ፡ ጸሓፊ ፥ በከተማዪቱም ፡ ከተገኙት ፡ ከአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ስድሳ ፡ ሰዎች ፡ ወሰደ ።

26 ፤ የዘበኞዎቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ወስዶ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ራብላ ፡ አመጣቸው ።

27 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ መታቸው ፥ በሐማትም ፡ ምድር ፡ ባለችው ፡ በራብላ ፡ ገደላቸው ። እንዲሁ ፡ ይሁዳ ፡ ከአገሩ ፡ ተማረከ ።

28 ፤ ናቡከደነጾር ፡ የማረከው ፡ ሕዝብ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ፡ አይሁድ ፤

29 ፤ ናቡከደነጾርም ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ነፍስ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ማርኳል ፤

30 ፤ በናቡከደነጾር ፡ በኻያ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የዘበኞዎቹ ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ከአይሁድ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡ ነፍስ ፡ ማርኳል ፤ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

31 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ዮአኪን ፡ በተማረከ ፡ በሠላሳ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በኻያ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፥ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ዮርማሮዴክ ፡ በነገሠ ፡ በአንደኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የዮአኪንን ፡ ራስ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ፡ ከወህኒም ፡ አወጣው ፤

32 ፤ በመልካምም ፡ ተናገረው ፥ ዙፋኑንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በባቢሎን ፡ ከነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ዙፋን ፡ በላይ ፡ አደረገለት ።

33 ፤ በወህኒም ፡ ውስጥ ፡ ለብሶት ፡ የነበረውን ፡ ልብስ ፡ ለወጠለት ፥ ዮአኪንም ፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ በፊቴ ፡ ኹልጊዜ ፡ እንጀራ ፡ ይበላ ፡ ነበር ።

34 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ የዘወትር ፡ ቀለብ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ❖



www.ethiopianorthodox.org